# የስርቻው መጣጥፍ



ትርጉም ፋሲል ይትባረክ

t.me/OLDBOOKSPDF

# የስርቻው መጣጥፍ

# "Notes from Underground"

በፊዮዶር ዶስቶየቭስኪ ተፅፎ

DONATED BY CODESTATION
NOT FOR SALE

በፋሲል ይትባረክ ተተረጎመ

ሰኔ 1991

t.me/OLDBOOKSPDF

# መግቢያ

ሩሲያ ካፈራቻቸው ታላላቅ ደራሲዎች አንዱ ፊዮዶር ዶስቶየቭስኪ ነው:: ከአስራዘጠነኛው ክፍለዘመን በፊት የነበሩት ብዙዎች እውቅ ደራሲያን የበቀሉት ከከበርቴው የህብረተሰብ ወገን ነበርና ጽሁፋቸው የሚመለከተው ሐብት የደለበበትን የጥቂቶች የፈንጠዝያ አኗኗር ነበር:: ይህን መሳይ መጻህፍት የዘመናችንን እውነታ:- ያገር ሙሉ ድሆች፣ የገባሮችና የለፍቶ አደሮች ከጅወዳፍ የመታከት ኑሮን ከነስቃዩ ወዲያ ብለው፤ ነገስታቱ፣ መሳፍንቱና ሹማምንቱ የወረሱትንና የሚያወርሱትን የቅንጦት ሕይወት ነበር የሚያወሱት::

ዶስቶየቭስኪን ታላቅ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ የዘመኑን የተለመደ የሥነጽሁፍ ፈለግ ለቅቆ፤ ከመባዘንና ከብሶታቸው በቀር ሌላ ሊያወሱት የሚበቃ ነገር በህይወታቸው የሌለ ይመስል በርካታ ደራሲያን ችላ ብለዋቸው ስለነበሩ ጎስቋሎች ለመፃፍ መድፈሩ ሲሆን፤ ልዩ የሚያደርገው ደግሞ፣ በዘመኑና ከእርሱ በፊት የነበረው ስነጽሁፍ ከተጥለቀለቀበት የሰውን ልጅ ክቡር ባህሪ ብቻ የሚያወድስ የምኞት ትዕይንት ወጥቶ፣ እነዚያን መኖራቸውን ስናውቅ በአደባባይ የማናወጣቸው፣ በሃፍረት ማቅ ጠቅልለን ከህሊና ጓዳችን አርቀን የምንቀብራቸው ጎደሎ የተፈጥሮ ገፅታዎችን አራቁቶ ማሳየት መቻሉ ነው:: ይህን ከመሳሰሉ ጽሁፎች የሚገኘው አንዱ ፍሬነገር ታዲያ፣ ሰው ማንነቱን ሳያውቅና የመላ ተፈጥሮውን አስገራሚ ስንክሳር፣ የመልካምና የርኩሱ መዓዛና ክርፋቱ ተጣምሮ ከህሊናው እንደሚኖር መርምሮና አውቆ ሳይቀበለው መሻሻል እንደማይቻለው ሲሆን፣ ከመፃህፍቱ መካከል በተለይ ይህኛው ያን መልዕክቱን አጉልቶ ያሳየናል::

እንደዶስቶየቭስኪ የሰውን ልጅ ውሰጣዊ ምንነት በውል የተረዱና፣ ያወቁትንም በረቀቀ የስነፅሁፍ ጥበብ ማስተላለፍ የቻሉ ደራሲዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥቂቶች ናቸው:: ምንም እንኳን ሁሉም የዶስቶየቭስኪ መጻህፍት የህያውነቱ ምስሶዎች መሆናቸው ባይካድም፣ " የስርቻው መጣጥፍ " በተሰኘው መጽሐፉ የተወለን የባህሪያችን ጥልቅ ትንተና ያስደንቀናል፣ ያስቀይመናል፣ ያስቆጣናል፣ ያስቀናል፣ ያሳፍረናል፣ ያሳዝነናል፣ ያናድደናል፣ የድብቅ ማንነታችንን ምንነት ሳያድበሰብስ ያሳየናል::

" የስርቻው መጣጥፍ " ወግና ልማድ ባልገሩት ስለታም ብዕሩ አማካይነት ዶስቶየቭስኪ ከህሊና ማህደራችን ሰተት ብሎ ገብቶ ስሜቶቻችንን የሚያማስልበት ድንቅ ስራው ስለሆነ ይህንን መፅሐፍ በተቻለኝ ጥንቃቄ ተርጉሜ ለአንባቢያን ማቅረቤ ደስ ያሰኘኛል::

ፋሲል ይትባረክ

1991

t.me/OLDBOOKSPDF

ርጉም ሰዉ ነኝ:: እኩይ፣ መልከ ጥፉ:: ጉበቴ የታወከ ይመስለኛል:: በዕውነቱ ግን ስለሕመሜ ምንም አላውቅም:: የሚያመኝ ምን እንደሆነ እንጃ:: ለዶክተሮችና ለመድኃኒት የላቀ ግምት ቢኖረኝም ቅሉ ለሕክምና ሂጄ አላውቅም:: በዚያ ላይ ደግሞ የከንቱ ዕምነት ተገዥ ነኝ:: ባልሆን ኖሮ በመድኃኒት ዕምነት ባልኖረኝም ነበር:: ለነገሩማ ከከንቱ እምነት ትብታብ ለመፈታት ያበቃኝ ያህል ተምሬአለሁ፣ ብዙም አልበጀኝ እንጂ:: ግና ሐኪም ዘንድ እንዳልሄድ በከፋቴ ታስሬ ተቀምጫለሁ:: ከዶክተር ቀየ እንዳልደርስ ጠፍሮ በያዘኝ ክፋቴ ማንን እንድጎዳበት መግለጽ ያቅተኛል:: ሐኪምን በሩቁ ብዬ መቀመጤ ለዶክተሮቹ ምናቸውም እንዳልሆነ ይገባኛል:: ብጎዳ እኔው ራሴ ነኝ እንጂ ማንም አይደል:: እና ባጭሩ ለሕመሜ አዋቂ ፍለጋ ያልሄድኩት ከከፋቴ የተነሳ ነው:: ጉበቴን ያመኛል? እሰየው ! አጥፎ፣ ደርቦ ይመመኝ::

እንዲህ ከሆንኩ ቆየሁ:: አንድ ሃያ ዓመታት:: ዕድሜዬም አርባ ሞልቷል:: ቀድሞ የመንግሥት ተቀጣሪ ሆኜ ሰርቻለሁ:: ያኔ ታዲያ መናጢ ነበርኩ:: ጉቦና ልምጃ በመቀበል ፋንታ ባለጉዳዮችን ከማጉላላትና ከማዋረድ ነበር ርካታ የማገኘው:: (ይቺ ጣዕመ ቢስ ቀልድ ነች አይደል? ብትሆንም ከዚህ ገጽ አልፍቃትም:: ስጽፋት ድንቅ ነገር መስላኝ ነበር:: አሁን ግን ተራ የተመፃደቀ ለሃጭ እንደሆነች አወቅሁት:: ለዚህም ብቻ ስል አልሰርዛትም::)

ይግባኝ ባዮች ጥያቄያቸውን ይዘው ከኔ ዘንድ በቀረቡ ቁጥር ጥርሴን አፋጭባቸውና ሲሸማቀቁ አንጀቴ ይርስ ነበር:: ባለጉዳዮችን በማሳቀቅ ከመካኔ የተነሳ፣ ነፍሳቸው ከርጉምነቴ ጥላ ሸልካ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚያመልጡ ሰዎች እጅግ ጥቂት ነበሩ:: በዚያ ላይ ደግሞ ይግባኝ ባዮች ሲባሉ ስጉዎች ናቸው:: አልፎ አልፎ ግን አንዳንድ ውጥሮች ያጋጥሙኝ ነበር:: ከነኚህ መሐል አንድ የጠመድኩት ወታደር፣ ከወጥመዱ አልገባ ብሎኝ ጭራሹን እየተጀነነና ጎራዴውን እያንኳኳ ሰላም ነሳኝ:: እኔስ መች ልተኛለት፣ አንከርፍፎት ይመጣ በነበረው በዚህ ጎራዴ የተነሳ ዓመት ተኩል ተሟግቼ ከረታሁት በኋላ ማቅጨልጨሉን አቆመ:: ይህ ሁሉ የሆነው ታዲያ ወጣት ሳለሁ ነበር:: የዚህ ሁሉ ክፉቴ ምስጢር ምን እንደሆነ ያውቃሉን? የሚገርመውና የሚያፀይፈው ነገር፣ የርግማን መርዜን ግራና ቀኝ እየረጨሁ ሳለሁ እንኳን፣ በውስጤ መጥፎ ሰው እንዳልሆንኩ አውቀው ነበር:: አዎ መጥፎም ሆነ ነፍሰመራር ሰው አልነበርኩም:: እንዲያው በከንቱ በቅሎ እያስደነበርኩ ራሴን ማጫወቴ ነበር:: የምሬት አረፋ ስደፍቅ የምጫወትበት አሻንጉሊት ቢሰጡኝ፣ ወይም ደግሞ ሻይ ብጤ በስኳር አቅርበው ቢደልሉኝ፣ እፎይ ብዬ እንደምቀመጥና ልቤ በሃሴት ቀልጣ እንደምትፈስ አልጠራጠርም:: ኋላ ግን ይህን በማድረጌ በቁጭት ጥርሴን እያፋጨሁ፣ ለሳምንታት እንቅልፍ ማጣቴ የማይቀር ነው:: እንዲህ ነው ተፈጥሮዬ::

ቅድም መናጢ የመንግሥት ሠራተኛ ነበርኩ ያልኩት ስዋሽ ነበር፤ እንዲሁ ለተንኮል ስወሸክት ከይግባኝ ባዮቹም ሆነ ከወታደሩ ጋር አምባጓሮ እገጥም የነበረው ስቧልት ነው እንጂ ከይሲ ሆኜ አይደለም:: መናጢነትን ብፈልገውም የሚሳካልኝ ጉዳይ አልነበረም:: ዘወትር በውስጤ የሚተራመሱ፣ ግራ የተጋቡ፣ ቅጥ አልባ ባህሪዎች አሉኝ:: ዕድሜዬ ልኬን ከነፍሴ ውስጥ እየተራኮቱ፣ እባክህ ፍታን እያሉ ሲማፀኑኝ፣ በክፋቴ አምቄ አልለቅም አልኳቸው:: ተኮልኩለው

t.me/OLDBOOKSPDF

በሃፍረት አለንጋ እየገረፉ ጨርቄን ጥዬ ላብድ ጥቂት እስቲቀረኝ አሰቃዩኝ:: ይህን ስልዎ ምናልባት በባህሪዬ ተፀዕኜ የእርስዎን ይቅርታ መጠየቅ መሻቴ ይመስልዎ ይሆናል:: ይህን እንደሚያስቡ በእርግጥ አውቃለሁ:: ያሻዎትን ቢያስቡ እኔ መች ደንታ ሊሰጠኝ::

የለዬለት መናጢ መሆን አልተቻለኝም:: መልካም ወይም መጥፎ፣ ወስላታ ወይም ቅን፣ ትልቅ ሰው ወይም ተባይ አልነበርኩም:: ካንዱ መስፈር የተሳነኝ:: አሁን ታዲያ ከስርቻዬ ውስጥ ተወትፌ፣ ብልህ ሰው መች ለእንሴነት ይበቃል እያልኩ በከንቱ ዕድሜዬን እቆጥራለሁ:: እንሴነት የየዋሆች ነው:: አዎ የዘመናችን ብልህ ሰው ሞላጫ ይሆን ዘንድ በኅሊናው ይገደዳል:: ባኅሪው የሰከነ የምግባር ሰው ደግሞ አእምሮ ስንኩል፣ ውስን ፍጡር መሆን አለበት:: ይህ በአርባ ዓመታት እድሜዬ የደረስኩበት እምነቴ ነው:: አርባ ዓመት ሞላኝ? . . . . እንዴ! አርባ ዓመት እኮ የሽምግልና ዳርቻ ነው:: ከአርባ በላይ መኖር ትልቅ ነውር ነው፤ የብልግና መጨረሻ:: እስቲ ልጠይቅዎት፤ሳይዋሹ ይመልሱልኝ:: ከአርባ ዓመት በላይ መኖር የሚደፍሩት እነማን ናቸው? እኔው እመልስልዎታለሁ፡- ቂሎችና ወስላቶች:: ከፈለጉ ደግሞ ይህን ለእኒያ የሽበት ቆብ የደፉ አረጋውያን እነግራቸዋለሁ:: ይህን የማለት መብት አለኝ፤ ምክንያቱም እኔ ራሴ እስከስድሳ መኖር እስባለሁ:: እስከ ሰባ! እስከ ሰማኒያ. . . አንዳፍታ፤ ትንፋሼን ልሰብስብ::

ይህን የማጫውትዎ ቢስቁልኝ ብዬ ይመስልዎት ይሆናል:: እንደገና ተሳስተዋል:: እንደሚያስቡት ቀልደኛ ሰው አይደለሁም:: መነባንቤ ሰላም ከነሳዎ (እንደረበሸዎት አውቃለሁ) ለመሆኑ አንተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማንህ ብለው ሊጠይቁኝ ይከጅላሉ:: እመልስልዎታለሁ:: የመዝገብ ቤት ሠራተኛ ነኝ:: ስራ ለመያዝ ዋነኛ ምክንያቴ ሆዴን እሞላ ዘንድ ነበር:: ኋላ ግን አምና፣ አንድ የሩቅ ዘመዴ ስድስት ሺህ ብር በኑዛዜ ሲተውልኝ ወዲያው ስራዬን ለቅቄ ስርቻዬ ውስጥ ገባሁ:: ወትሮም እዚሁ ነበር የምኖረው፤ አሁን ግን አንድያዬን ጠቅልዬ ሰፍሬያለሁ:: ዕዳት የናፈቃት ድንግዝግዝ ጎጆዬ ከመንደር ዳርቻ ትገኛለች::

የፒተርስበርግ አየር ለጤናዬ እንደማይስማማኝና የቋጠርኳትም ጥሪት ለከተማ ኑሮ እንደማትበቃ ተነግሮኛል:: ይህን እኔ ራሴ ከእነዚያ የልምድ ባለፀጋ አዋቂዎችና አማካሪዎች የበለጠ አውቀዋለሁ:: ይሁንና ፒተርስበርግን ለቅቄ አልሄድም:: ከዚህ ንቅንቅ አልልም፤ ሄድኩ አልሄድኩ ምን ሊፈጠር:: ወደ ጀመርኩት ልመለስና፣ ጨዋ ሰው በደስታ ማውጋት የሚወደው ስለምንድን ነው? መልስ:- ስለራሱ:: እና እኔም ስለራሴ አወጋለሁ::



መስማት ፈለጉም አልፈለጉ ተባይ እንኳን መሆን ለምን እንደተሳነኝ ልነግርዎ እሻለሁ:: አዎ የተባይን ያህል እንኳን ማንነት ይኖረኝ ዘንድ እመኝ ነበር:: ግን ያም አልተፈቀደልኝ:: ከልክ ያለፈ ዕውቀት እኮ በውኑ በሽታ ነው - የለየለት ጥኑ በሽታ:: እያንዳንዱ ሰው በምድር ለመኖር ይችል ዘንድ በፒተርስበርግ እንዲኖሩ የተረገሙት የዘመናችን ስልጡኖች ከታደሉት ዕውቀት ግሚሱ ወይም ዕርቦው ይበቃዋል:: ፒተርስበርግ:- ታልማ የተወለደች ከተማ ለአንዳንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከተሞች ታልመው ይፈጠራሉ::) ሥልጡን ነኝ ባዩ የሰው ልጅ እኒያ ተራ የምግባር ሰዎች ካላቸው እውቀት በላይ አያስፈልገውም:: ይህን ሁሉ ስቀባጥር በከንቱ ጉራዬን እየነፋሁ እንደሚመስልዎት አውቃለሁ:: እንደዚያ ወታደር ጎራዴዬን እያንኳኳሁ በምግባር ሰዎች ላይ የማፌዝ አድርገው ይቆጥሩኛል:: ግን በውነቱ ማነው በበሽታው ደስ የሚሰኝና ተውሳኩን አደባባይ አውጥቶ የሚመፃደቅ?

እንዴ? ምን ማለቴ ነው? ይህን ሁሉስ ያደርጉት የለም? በሕመማቸው የሚኩራሩ ብዙ ሰዎች አሉ:: በበኩሌ ከሌሎች ይልቅ በበሽታዬ እኩራራለሁ:: እሺ በዚህ አንከራከር:: ምናልባት ተሳስቼ ይሆናል:: የሆነ ሆኖ ግን አነሰም በዛም የአእምሮ ንቃት በሽታ ነው:: በዚህ ጥርጥር የለኝም:: ይህን በዚህ እንተወውና እስቲ ይንገሩኝ:- ለምን ይመስልዎታል ከልቤ ውስጥ ባለው የላቀ የመልካም ምግባር ስሜት መመራት በምችልባቸው ወቅቶች፣ ለተንኮል ይመስል ብዙዎች ከሚለወሱበት የርካሽ ገቢር ማጥ ውስጥ እያወቅኩ የምዘፈቀው? የመልካምነትንና የቅንነትን ምንነት ይበልጥ በተረዳሁት ቁጥር ከጥፋት ረግረግ ውስጥ ገብቼ የምጨማለቀው ለምንድን ነው? ይህ ታዲያ ያጋጣሚ ጉዳይ አይምሰልዎ፤ እንዲሆን የታዘዘበት ነገር ነው:: በውርደት የመልከስከስ በሽታዬ አንዳች ልክፍት ሳይሆን ተፈጥሮ የሰፈረልኝ ጠባይ እስቲመስለኝ ድረስ እያደር ልዋጋውና ልቋቋመው ተሳነኝ:: በመጨረሻም የማልሸሸው ዕጣዬ አድርጌ ተቀበልኩት::

ተረትቼ፣ እጄን አጣጥፌ ከመቀመጤ በፊት ግን እሸሸው ብዬ ስታገል ስቃዬን አየሁ:: የኔ ልክፍት የተጠናወታቸው ሌሎችም

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳሉ ባለማወቄ በሽታዬን በማቅ ጠቅልዬ ደብቄ ዓመታት አሳለፍኩ:: በሃፍረት ተቀጣሁ፤ እስካሁንም እሸማቀቅበታለሁ:: እያደር ግን አንድ ፀያፍ ድርጊት ከፈፀምኩ በኋላ፣ በጨለማ ወደ ስርቻዬ ተንሿክኬ ገብቼ፣ ከርካሽ ምግባሬ ጭራሹን ደስታ ማግኘት ጀመርኩ:: መጀመሪያ የሆነው ሆኗል፣ የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ እያልኩ ራሴን ሳፅናና እቆይና፣ ምሬቴ ሳላውቀው ቀስ በቀስ በጣዕመ ደስታ ይበረዛል:: ከዚያም የለየለት ሃሴት ሆኖ ቁጭ! አዎን የሚፍለቀለቅ ሃሴት! እውነቴን ነው:: ይህን ያነሳሁበት ዋነኛው ምክንያት ሁሌ ሳውቀው ለምፈልገው ነገር መልስ አገኝ ብዬ ነው:: እውን ይህ ዓይነቱን ደስታ የሚያውቁ ሌሎችም ይኖሩ ይሆን?

የዚህ አይነቱን ደስታ ምንነት እኔው ላስረዳዎት:: ይህ ሃሴት የሚወለደው ወራዳነትዎን በውል ሲያውቁት ነው:: ነፍስዎ በርክሰት ማጥ ከመዘቀጥ በቀር ሌላ አማራጭ እንደሌላት፣ ከመግማማት ማምለጥ እንደተሳነዎትና ራስዎን መለወጥ እንደማይችሉ፣ ከርግማን ሊታደግዎ የሚያበቃ ጊዜና እምነት ቢኖርዎም የመለወጥ ፈቃዱ እንደሌለዎት፣ ፈቃዱ ቢኖርዎትም እንኳን መሞከር እንደማይሹ ሲያውቁት ነው:: ይህን ትተው ወደምን ሊለወጡ?

እዚህ ላይ ሊገነዘቡት የሚገባው ነገር ቢኖር ይህ ሁሉ የሚመነጨው ከልክ ያለፈ የአእምሮ ንቃት ከሚመራበት ሕግጋትና የዚህ ሕግጋት ውጤት ከፈጠረው ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ነው:: ስለዚህም ራስዎን መለወጥ ቀርቶ መሞከርም አይችሉም:: ማድረግ የሚችሉት ነገር በሰላው የማሰብ ችሎታዎ አማካይነት ራስዎን የማይረባ ወስላታ አድርገው መቁጠር ብቻ! ወሮበላነትዎን ማወቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያዕናናዎ ይመስል:: ኤጭ ! ይህ በዚህ ይብቃን . . . ይህን ሁሉ ዘብዝቤ ምን መግለፅ ቻልኩ? የዚያ አንጉል ደስታስ መንስኤውና ፍጥረቱ ምንድነው? ይታገሱኝ፣ እገልፅልዎታለሁ:: ብዕሬን ያነሳሁት ለዚሁ ነውና፣ ብልት በብልት አውጥቼ አሳይዎታለሁ::

ለምሳሌ የራስ ግምቴ እንደብራና የሳሳ ነው:: እንደድንክ ሰው ተነካሁ ባይነት ያጠቃኛል:: እንደጎባጣ በሆነ ባልሆነው የተዘለፍኩ ይመስለኛል:: ያም ሆኖ ታዲያ አንድ ሰው ተነስቶ በጥፊ ቢያላትመኝ የከጀልኩባቸው ጊዜዎች ነበሩ:: እውነቴን ነው! ከዚህ ዓይነቱ ሃፍረት ቀየ እንኳን ትርጉም የሚገኝ ይመስለኝ ነበር:: በርግጥ ይህ ከተስፋቢስነት የሚመጣ ነገር ነው:: ግን ሰው በሃሴት ሰረገላ የሚስግረው ተስፋቢስነትን ተላብሶ መድረሻ ማጣቱን ሲያውቀው አይደለምን? ሰው በጥፊ ሲመታዎት መረገጥዎን አውቀው ይሰቃያሉ:: ይሁንና ግን ከየትም ቢመለከቱት ሲጀመር ለጥፊ ያበቃዎት ስህተት የራስዎ ነው::

የሚያሳዝነው የሰው ልጅ ከስህተት የሚገባው በራሱ ጥፋት ሳይሆን በተፈጥሮ ህግ የተነሳ ነው:: ምክንያቱም፣ ለምሳሌ የእኔን ስህተት ቢመለከቱ የጥፋቴ መንስኤ በዙሪያዬ ያሉት ሰዎች ከታደሉት የላቀ አእምሮዬ ነው:: ( በነገራችን ላይ ከሌሎች የላቀ አእምሮ እንዳለኝ አድርጌ ነው ዘወትር ራሴን የምመለከተው:: አያምኑኝ ይሆናል እንጂ፣ በዚህ የበላይነቴ ሐፍረት ብጤ እየተሰማኝ የሰዎችን ዓይን አትኩሬ ማየት ይሳነኛል):: የስህተቴ ሌላው ምክንያት ደግሞ፣ የቱንም ያህል ብሩክ ሰው ብሆንም፣ የብሩክነቴን ከንቱነት ተረድቼ ከመሰቃየት በቀር ሌላ ሳደርገው የምችለው ነገር

t.me/OLDBOOKSPDF

አልነበረም:: ምን ልፈይድበት? ይቅርታዬን እንዳልለግስበት ሰውየው በጥፊ ያላጋኝ ወዶ ሳይሆን በተፈጥሮው ተገዶ ነው:: ተፈጥሮ ደግሞ ለይቅርባይነት ደንታ የላትም:: ብሩክነቴ የበደሌን ትውስታ መፋቅ አይቻለውም:: ሁሉም ነገር ተፈጥሮ የደነገገው መሆኑን ባውቅም፣ ጥፊ ካለፈ በኋላ በመከፋት አለንጋ ማብከንከኑ አይቀርምና:: በሌላ በኩል ደግሞ ለጋስነቴን ወዲያ ብዬ፣ ባቀለለኝ ሰው ላይ ልበቀል ብፈልግም አይሳካልኝም፤ ቢሳካልኝም ሳደርገው አልሞክርም:: ለምን? በዚህ ላይ ቀጥዬ አወጋዎታለሁ::

- 3 -

ለምሳሌ ብቀላ የሚሆንላቸውና ለራሳቸው መቆም የሚችሉ ሰዎችን እንመልከት:: እንዴት ይሳካላቸዋል? በብቀላ ስሜት ሲጠመዱ ከዚያ በቀር ሌላ ነገር ማሰብ ይሳናቸውና፣ ሊወጋ ቀንዱን ቁልቁል ቀስሮ እንደሚንደረደር በሬ ወደ ዓላማቸው ከመገስገስ ፍንክች አይሉም:: የሚገታቸው ግትር ግድግዳ ብቻ ነው:: ( በነገራችን ላይ ቀጥተኛ የምግባር ሰዎች ግድግዳ ሲጋረጥባቸው አምርረው ይመለሳሉ:: እነርሱ እንደኛ ግድግዳን የማምለጫ ሰበብ አድርገው አያዩትም:: እኛ የሃሳብ ባለፀጎችና የገቢር ድሆች ግን፣ የግድግዳን ግድግዳነት ሳናምንበት በእፎይታ እንቀበለዋለን:: ለምግባር ሰዎች ግድግዳ የሚያረጋጋ፣ የሩጫ ፍፃሜ አብሳሪ ነው፤ ኀሊናን አፅድቶ የሚያረጋጋ ምሥጢር . . . በተረፈ ስለግድግዳዎች በኋላ እንጫወታለን::)

በእኔ አስተያየት ይህን የመሰለ ቀጥተኛ የገቢር ሰው በውኑ የተስተካከለ ጤነኛ ሰው ነው፤ እናት ተፈጥሮ በምድር ልታየው


t.me/OLDBOOKSPDF

የምትሻው እንከን አልባ ፍጡር:: ይህን በመሰለ ሰው እቀናለሁ፤ ቅናቴ ድንበር ጥሶ ጥላቻ እስከሚሆን ድረስ:: በርግጥ ይህ ፍጡር ደደብ እንደሆነ አምናለሁ፤ ግና ደነነኘነት ከደደብነት ጋር የተቆራኘስ ቢሆን? ምናልባት የሚያምረውስ እንዲያ ሳይሆን ይቀራል? ይህን ጥርጣሬዬን የሚያረጋግጥልኝ ነገር አለ:: ለምሳሌ የደህነኛውን ሰው ተፃራሪ፣ ማለትም ከተፈጥሮ አብራክ ሳይሆን ከጀርባዋ የዘለቀ፣ ከፍተኛ የአእምሮ ንቃት ያለውን ሰው ቢያስተውሉ፤ ይህ የጓሮ ሰው ከተቃራኒው ተጋፍጦ መቋቋም ባቃተው ቁጥር በላቀ አስተሳሰቡ ራሱን ከአይጥ እንጂ ከሰው አይቆጥርም:: ምናልባት ግንዛቤው የላቀ ዓይጥ ሊሆን ይችላል፤ ግን ያም ከአይጥነት አያድነውም:: ተቃራኒው ግን ሰው ነው::

ዋናው ነገር ግን እርሱ ራሱ፣ ማንም ሳይፈርጀው ነው ራሱን ከአይጥ የሚቆጥረው:: እስቲ የዚህን አይጥ ምግባር እናስተውል:: ተበድሏል እንበል፣ (ለነገሩ ዘወትር እንደተበደለ ነው):: ስለተበደለም መበቀል ይፈልጋል:: በዚህ ጊዜ በውስጡ የሚታመቀው ምሬት ሰው በምሉዕ ተፈጥሮው መቋጠር ከሚቻለው በላይ ነው:: የገፋውን በሰፈረበት ቁና ሰፍሮ ሊመልስለት ከሌሎች ይልቅ አጥብቆ ይቋምጥ ይሆናል፤ ምክንያቱም ምሉዕ ስብዕናውን የያዘ ሰው ከተጠናወተው ደደብነት የተነሳ የበቀላ ፍላጎቱን ከሚዛናዊ ፍትህ የመነጨ ጉዳይ አድርጎ ሲያየው፣ አይጡ ግን በላቀ አመለካከቱ ነገር አለሙን ከፍትህ ማዶ አሻግሮ ያስቀምጠዋል::

ከዚያም ወደ ድርጊቱ እንደርሳለን:- ማለትም ከበቀላው:: ርጉሙ አይጥ፣ ከመጀመሪያው ጉድ አልፎ ተርፎ፣ በጥያቄና

t.me/OLDBOOKSPDF

በጥርጣሬ መልክ በፈጠረው የጉድ አጥር ተከቦ፣ ከበፊቱ ጥያቄው ላይ ሌሎች ብዙ መልስ አልባ ጥያቄዎች ደራርቦ፣ መውጫ ከሌለው፣ በራሱ ጥርጣሬና ሽብር በከረፋው መቀመቅ ውስጥ ወርዶ ይቀበራል:: ዙሪያውን ሆነው፣ ዳኝነት ተቀምጠው የሚወቅሱት የምግባር ሰዎች ሲስቁና ሲሳለቁበት ከአፋቸው በሚዘንበው ለሃጭ ታጥቦ ሳለ፣ አንድ ሊያደርግ የሚችለው ነገር ነፍሱ በምሬት ተመርዛ፣ ውርደቱን ተከናንቦ፣ ራሱ እንኳ በማያምንበት የንቀት መሣይ ፈገግታ ከናፍሩን ጠምዝዞ ወደ ጉድባው ማዝገም ብቻ ነው::

የኛው አይጥ ከአፀያፊው የጉድባው ክርፋት ውስጥ ተወትፎ ወዲያው ከውርደቱ ከመዘለፉና ከመረገጡ የተነሳ በእድሜ ልክ የክፋትና የቂመኛነት ቆፈን ይመረዛል:: ለዓርባ ዓመታት ሳያሰልስ ከልቡ የቀበረውን ብሶትና ቂም ቆፍሮ እያወጣ፣ በየጊዜው ውርደትና ጉዱን በትጋት እየተረተረና በራሱ እየተሳለቀ ነፍሱን ይቀጣታል:: ብሶቱን አልሞ፣ ፀንሶ የወለደው እሱ ራሱ መሆኑ ሲያሳፍረውም፣ የዚህ የሃሳብ ውላጅ ጥቃቱን ሥራስር በመፈልፈል ደጋግሞ እያሰላሰለ ከመቆጨት አይታቀብም:: ያልነበረ በደል ቢኖርስ እያለ፣ በምህረት አልባ ኅሊናው ያውጠነጥናል:: ከዚህም አልፎ ብቀላውን ለመሠንዘር እንደነገሩ ከተረሳበት የምድጃ ዳር ሲውተፈተፍ ሳለ እንኳ፣ በመበቀል መብቱም ሆነ ችሎታው እምነት የለውም:: የብቀላ ጥረቱም ከበዳዩ ይልቅ እርሱ ራሱን መቶ እጥፍ እንደሚያስቃየው ጠንቀቆ ያውቀዋል:: በዳዩ የእንዲህ አይነቱን ሰው የብቀላ ሙከራ መች ከቁንጫ ንክሻ ሲቆጥረው:: ከጊዜ በኋላ፣ አይጡ በሞት ጥላ ስር ተኝቶ እያጣጣረ፣ በደሉን በዓመታት ከተጠራቀመ ወለዱ ጋር ሰብስቦ እያስታወሰ . . . ያለመደምደሚያ::


t.me/OLDBOOKSPDF

ግን በዚህ በቀዝቃዛ የሰቀቀን ጓዳ፣ የከፊል ተስፋቢስነትና የከፊል እምነት ቀዩ፣ከሥቃይ ብዛት ራስዎን ለአርባ ዓመታት ከተበሩበት ዋሻ፣ በዚህ በትጋት ከተገነባ ድንግዝግዝ መድረሻቢስነትና ከፍሬ ለመብቃት ያልታደሉ ፍላጎቶች የፈጠሩት መርዝ ከሚፈልቅበት የመዋዠቅ ሕመም፣ ለዘላለም የተተከሉ ውሳኔዎች ከሚገዙበትና፣ የፀፀት ጥርስ ከሚፋጭበት መንደር ነው ቀድም የነገርኩዎ ሃሴተ እርግማን የሚፈልቀው:: ይህ ዓይነቱ ደስታ እጅግ በመርቀቁና በቀላሉ ሊጨበጥ በጅ ባለማለቱ፣ ጥቂት አእምሯቸው የደበዘዘና ልባቸው የደነደነ ሰዎች ቅንጣቱን እንኳን ሊረዱት አይችሉም:: ታዲያ እርስዎ "ጥፊ ያልቀመሰው ሰው በየት በኩል

እንዲህ አይነቱ ደስታ ይገባዋል?" ብለው በፈገግታ ድድዎን ይገልጡ

ይሆናል፣ ጥፊ ቀምሼ እንደማውቅና የምናገረው ከልምድ እውቀቴ እንደሆነ መረዳትዎን ሊያሳዩኝ:: ለነገሩ ይህን እንደሚያስቡ ጥርጣሬ የለኝም:: ረጋ ይበሉ:: እርስዎ የሚያስቡት ደንታ ባይሰጠኝም፣ በጥፊ ተመትቼ አላውቅም:: እንዲያውም በህይወት ዘመኔ በርካታ ጥፊዎች ባለመሠንዘሬ ይፀፀተኛል እንጂ:: ይሁንና፣ በዚህ ጉዳይ ላይ እንድቀጥል እጅግ መፈለግዎን እያወቅኩት፣ እስቲ በዚህ ይብቃን እላለሁ::

ረጋ ብዬ ከልበደንዳናነታቸው የተነሳ አንዳንድ የረቀቁ የደስታ ዓይነቶችን መረዳት ስለሚሳናቸው ሰዎች ማውሳት ልቀጥል:: እንዲህ ያሉ ሰዎች የሚከበሩት በመሠላቸው ጊዜ አፋቸውን ከፍተው ከማናፋት ወደኋላ ስለማይሉ ብቻ ነው:: ሆኖም ግን ቀድሜ እንደነገርኩዎ የማይቻል ነገር ሲያጋጥማቸው ጥለው መፈርጠጣቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

አይቀርም:: ታዲያ የማይችሉት ነገር የድንጋይ አጥር ነው ማለት ነውን? እንዴት ያለ የድንጋይ አጥር? የተፈጥሮ ሕግ፣ የማይሽሩት የሳይንስ ውጤት፣ ማትማቲክስ ነዋ! ለምሳሌ እርስዎ የመጡት ከጦጣ እንደሆነ ቢያረጋግጡልዎ፣ በጥሞና መቀበል እንጂ ፊትዎን በቁጣ ማኮሳተሩ ለምን ይበጃል? የፊሙማዎ አንዷ ጠብታ ከመቶ ሺህ ሰዎች ሕይወት እንደምትበልጥብዎ ቢያሳዩዎትና፣ የሰውም ልጅ ሥነምግባር፣ ኃላፊነትና ይህን የመሳሰለው ዝባዝንኬ ሁሉ በዚህ ሕግ እንደሚወሰን ቢያውቁት ሊፈጥሩት የሚችሉት አንዳችስ ነገር የታለ? ነገር የለም:: ምክንያቱም ሁለት ጊዜ ሁለት የማትማቲክስ ውጤት ነው፡ የማይገሰሱት፣ የማይገፉት::

" ኧረ ስለፈጠረህ ! " ብለው ይጮሁብኛል:: " ይህን ልትከራከረው አትችልም ! ሁለት ጊዜ ሁለት አራት ነው:: ተፈጥሮ አንተን አታማክርም:: ለአንተ ፈቃድ ደንታ የላትም:: ሁሉንም እንዳለ ተቀብለህ ከውጤቱ ብትላመድ ይሻልሃል:: ግድግዳ በርግጥ ግድግዳ ነው . . . " ወዘተ . . . ወዘተ:: ቸሩ ፈጣሪ ! እኔስ በመሰለኝ ምክንያት እኚህን ሕግጋት ካልወደድኳቸው፣ ለተፈጥሮና ሁለት ጊዜ ሁለት አራት ነው ለሚለው አሪትሜቲክስ መች ግድ ሊሰጠኝ:: ልደረምስበት የሚያስችለኝ ጉልበቱ ከሌለኝ ይህን የድንጋይ ግድግዳ እንዳልጋፋው አውቃለሁ:: ቢሆንም ግን ቋጥኝ ከፊቴ ስለተደነቀረና፣ ላፈርስበት የሚያስችለኝ አቅም ስላነሰኝ ብቻ፣ እጄን አጣጥፌ ልቀበለው ማለት ነው? አይደረግም!

ሁለት ጊዜ ሁለት አራት ቢሆንም የድንጋዩ አጥር የሚያባብለኝ፣ ወይም ደግሞ ታርቄው እንድቀመጥ የሚጋብዘኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

ይመስል በርጋታ አልቀበለውም:: ቢስቁብኝም ይሳቁብኝ እንጂ፣ ሁሉን ከተረዱ፣ እንዳይችሉት ካወቁና የድንጋይ አጥርን ግትርነት ከተገነዘቡ በኋላ፣ የአንዳቸውንም ፍፃሜነት የማይቀበሉት ከሆነ፣ እጅ አልሰጥም ብሎ መስጠትና አሻፈረኝ ማለትን የመሠለ ነገር የለም:: በማያከሽፉት የሎጂክ ውስብስብ ተጠቅልለው፣ ለድንጋዩ ግድግዳ መፈጠር እራስዎን በሚወነጅል ዕልባት ይህን ጉዳይ መደምደም ይሻላል፤ ምንም እንኳን እርስዎ ያጠፉት ነገር እንደሌለ ግልፅ ቢሆንም:: ይህን ካደረጉ በኋላ እጅዎን ሰብስበው፣ የሚወቅሱትና የሚደነፉበት ሰውም ሆነ ነገር አጥተው፣ በፋይዳቢስነትዎ ትብታብ ተጠላልፈው፣ በዝምታ ጥርስዎን እያፋጩ መቀመጥ:: ሁሉም ነገር የአስማተኛ ምትሓት፣ ራስና ጅራቱ ያልለየ ምሥቅልቅል እንጂ ውል ያለው ጉዳይ አይደለም ብለው ማረፍ ይሻላል:: ግና በዚህ ትርምስምስ፣ ጥርጣሬና ቅጥ አልባነት መሐል ስቃይዎ የሚያባራ አይምሰልዎ:: ‹ጥርጣሬዎ በበዛም ቁጥር መከራዎም በዚያው ልክ ይደልባል::›

- 4 -

" ሃ . . ሃ . . ሃ !" ቆይተህ ደግሞ ከጥርስ ሕመም ደስታ ይገኛል ትላለህ !" ብለው ሲስቁብኝ:- " ለምን አላገኝ ? ሳወቀበት የጥርስ ሕመምም ጣዕም አለው !" ብዬ እመልስልዎታለሁ:: ለአንድ ወር ያህል ጥርሴን አሞኝ ስለነበር አውቀዋለሁ:: በጥርስ ሕመም ጊዜ ሰዎች ስቃያቸውን በዝምታ አይውጡትም:: ሎሎ'ሽ ብለው ያቃስታሉ:: ግን የሲቃ ለቅሶአቸው የምር አይደለም:: የብልጠት



t.me/OLDBOOKSPDF

አይነት ክፋት የተቀላቀለበት ነው:: ማቃሰትና ማንቋረር የበሽተኛውን ምርጫ ነው የሚገልፁት:: ባይፈልገው ኖሮ አለማቃሰት ይችል ነበር:: ይህ ጥሩ ምሳሌ ስለሆነ በይበልጥ ልመለከተው እወዳለሁ::

ማንቋረርዎ የሚገልፀው የሕመምዎን አቃላይ ፋይዳቢስነት መረዳትዎንና ደንታ በማይሰጡዋቸው አእላፍ የተፈጥሮ ህግጋት ምክንያት ከስቃይ እንደወደቁ መገንዘብዎን ነው:: ተፈጥሮ ግን ይህ ሁሉ ምናም እንዳልሆነ ያውቁታል:: ማቃሰትዎ የሚለፍፈው የሚወነጅሉት ጠላት አለመኖሩንና፣ ሙያውን የተካኑ የጥርስ ሐኪሞች ሳሉ እርስዎ በጥርስ ሕመም ባርነት መላሸቅዎን፣ አንዳች ነገር ስቃይዎ ያከትም ዘንድ ቢያግዝዎ ቀጥ እንደሚልና፣ ይህ እስኪሆን ድረስ ግን ሕመምዎ ለሌላ ሁለት ወይም ሦስት ወራት እንደሚቀጥል ነው:: ይህን መቀበል አልሻም ብለው ቢያምፁ፣ ማድረግ የሚችሉት ራስዎን መቅጣትና፣ እናትዎን ከግድግዳ ጋር ማጋጨት ብቻ ነው::

እና ይህ ውርደት፣ ይህ መምጫው ያልታወቀ ዝቅጠት ነው ቀስ በቀስ ከመለመድ አልፎ፣ ይጥምዎትና፣ በመጨረሻ ስሜትዎን የሚያስክር ሃሴት ሆኖ የሚያርፈው:: ለመሆኑ ያን የተማረ የዘመናችን ሰው በጥርስ ሕመም ተይዞ ሲያቃስት ሰምተውት ያውቃሉ? ሕመሙ በጀመረው በሁለተኛው ወይም በሦስተኛው ቀን ከቀድሞው በተለየ ሁኔታ ሲያንቋርር አዳምጠውታል? የሚያሳዝነው እንደጥፍራም ገጠሬ ጥርሱ ስለነዘነዘው ብቻ አይደለም:: ሲያቃስት እንኳን በደረጃው ነው፤ ምድር ከመጫር በስልጣኔው ተፋቶ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

ከተራነት መጥቆ እንደወጣ ምሁር:: ማቃሰቱን ከከይሲነት ያዋህደዋል፤ እያደር ክፋትና ተንኮሉ ይሰርግበትና ቀንና ሌሊት ሳያባራ ይቀጥላል:: ማላዘኑ ለምንም እንማይበጅና፣ በፌጩኸቱ ራሱንና ሌሎችን ሰላም እየነሳ እንደሚቀጣ ከማንም በላይ ይረዳዋል:: ለነርሱ ሲል የሚደክምላቸው አዳማጮቹና ቤተሰቦቹ የሱን ማቃሰት መስማት እንዳንገፈገፋቸውና እንደማያምኑት፣ ከዚያም በላይ ከፊለገ የጨመራትን ቅላፄና እንጉርጉሮ ብጤ ዜማ ትቶ በወጉ ማንቋረር እንደሚችልና፣ እንዲሁ ለክፋት በከንቱ እየጮኸ ራሱን ማጫወቱ መሆኑን ማወቃቸው አይጠፋውም::

የዚህ አይነቱ ሰው የሚያገኘው የስሜት እርካታ የሚመነጨው ይህን ከማወቁና ከከይሲነቱ ነው:: "እየረበሽኳችሁ ነው ! እየቀጣኋችሁ ! እኔ ታምሜ እዚህ ቤት ማንም ሰው ባይኑ እንቅልፍ ዝር አይልም! የጥርስ ሕመሜን ስቃይ እያንዳንዷን ደቂቃ በግዳችሁ እግታችኋለሁ:: ቀድሞ ነኝ ያልኳችሁ ጀግና አይደለሁም:: ተራ፣ አልባሌ ሰው ነኝ፣ መሆኔንም እንኳን አወቃችሁ:: ማቃሰቴን መስማት ከመረራችሁም እሰየው! ይብሱን ያንገፍግፋችሁ! እንዲያውም ከማንቋረሬ ላይ አንዲት አስቀያሚ ቅላፄ እጨምርባታለሁ::"

አሁንም አልገባዎትም? ይህንን መሣይ የረቀቀ ርካታ ጣዕም ደስታ ለመረዳት የላቀ እድገትና ጥልቅ የአእምሮ ብስለት ይጠ ይቃል:: እየሳቁብኝ ነው? መልካም፣ ደስ ይለኛል:: ቀልዶቼ ለዛቢስ እንደሆኑ አውቀዋለሁ:: የተጣመሙ፣ ግራ የተጋቡና ራስን በመጠራጠ ር እሾህ የተበሳሱ ናቸው:: የዚህም ምክንያቱ የራስ አክብሮት



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሚያንሰኝ ነው:: የአእምሮ ንቃቱን ከፍተኛነት የተገነዘበ ሰው ራሱን ማክበር አይቻለውምና::

- 5 -

ለመሆኑ ከውርደት ደጃፍ ደስታን አገኛለሁ ብሎ የሚያስብ ሰው በውኑ ቅንጣት እንኳን የራስ አክብሮት አለው? ይህን ስልዎ በምግባሬ ለመፀፀት ዳር ዳር ማለቴ እንዳይመስልዎ:: በበኩሌ ፀፀት አይሳካልኝም:: " ይቅር በለኝ አባዬ፣ ሁለተኛ ይህን አላደርግም ! " ማለት አልችልም:: የማልችለው ተስኖኝ አይደለም:: ከፈለግኩ አሳምሬ ልለው እችላለሁ:: ሳውቅበትስ! ስንት ጊዜ ነበር ሳላጠፋ አውቄ ራሴን ችግርና ጣጣ ውስጥ የከተትኩት:: የሚገርመው ታዲያ ባልፈፀምኩት ጥፋት ራሴን ደልዬ፣ እያዘንኩና እያለቀስኩ ነፍሴን አሸማቅቃት ነበር:: ሳስበው ከእንዲህ አይነቱ በሽታ የጣለኝ ልቤ ይመስለኛል:: ይህ ታዲያ የተፈጥሮ ሕግ ውጤት አልነበረም፤ ምንም እንኳን የተፈጥሮ ሕጋጋት ዘወትር ቢበድሉኝም ቅሉ:: ይህን ታዲያ አሁን እንኳን ሳስታውሰው ያቅለሸልሸኛል:: ያኔም ሳደርገው እጅግ ያስጠላኝ ነበር፤ ምክንያቱም ካደረግኩት ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቅጥፈቴ፣ ሃፍረተቢስ አስመሳይነቴ ይታዩኝና በራስ ጥላቻ እላሽቃለሁ:: ሁሉም መወሻከት ነበር:- ፀፀቴ፣ በሃዘን የሚቀልጥ ልቤ፣ የመሻሻል መሃላዬ፣ ሁሉም::

ለምን በዚህ ሁኔታ ራሴን እቀጣ እንደነበር ይጠይቁኝ ይሆናል:: መልሱም:- ምንም ሳልሰራ እጆቼን አጣጥፌ መቀመጥ እጅጉን ይሰለቸኝና አልባሌ ነገር ማድረግ ያምረኛል:: እውነቴን

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው:: ራስዎን በውል ቢመለከቱ የዚህን እውነትነት ያዩታል:: በሌሉበት ጀብዱዎችን እየፈጠርኩና፣ ሕይወትን ቀድጄ እየሰፋሁ እንደምንም ለመኖር ተጣጣርኩ:: ስንት ጊዜ ነበር ያለምክንያት ከምድር ተነስቼ ተንካሁ ያልኩት? ምንም ለቁጣ የሚያበቃኝ ነገር አለመኖሩንና፣ ድንፋታዬ ማስመሰል መሆኑን እያወቅሁት፣ ስንት ጊዜ ነበር በቁጣ ነበልባል ተንገብግቤ፣ ኋላም በራሴ ቅኝት አምኜ፣ ብስጭቴ ተገቢ መስሎኝ ያረፍኩት ! ዕድሜ ልኬን ይህን በመሳሰሉ ልክፍቶች ነፍሴን አስጠምጄ ኖርኩና፣ በስተኋላ ራሴን መቆጣጠር ጭራሹን ተሳነኝ::

አንዳንዴ ደግሞ በፍቅር እንድያዝ ራሴን አስገድደው ነበር:: ይህን ሁለት ጊዜ አድርጌዋለሁ:: እንዴት እንደተሰቃየሁ አይጠይቁኝ! እየቀለድኩ እንደነበር ውስጤ እያወቀው፣ ባውቀውም፣ በፍቅር አለንጋ ልቤን አምርሬ ከመጥበስ አልዳንኩም:: ከዚያም ይባስ ብዬ ቅናት ጨመርኩበትና ጨርቄን ጥዬ ማበድ ቃጣኝ:: ይህን ሁሉ ያደረግኩት የማደርገው ከማጣትና ከተጫነኝ የድብርት ቋጥኝ የተነሳ ነው:: የአእምሮ ንቃት ውጤቱ፣ እንዲሁ እጅን አጣጥፎ መቀመጥና፣ ኋላም ከመሰልቸት ብርታት የባጥ የቆጡን ማሰብና ማድረግ ነው:: ስለዚህ ቀደም ብዬ አውግቻለሁ:: እደግመዋለሁ:: ቅን የምግባር ሰዎች የሚተጉት አእምሮ ደብዛዛና ውስን ስለሆኑ ነው:: ውስን በመሆናቸውም ተራው ነገር ሁሉ ጠቃሚ ይመስላቸውና ትጋታቸው በተገቢ ምክንያት የተደገፈ መሆኑን አይጠራጠሩም:: በዚህም ኅሊናቸው እረፍት ያገኛል:: የኅሊና እረፍት ደግሞ ዋና ነገር ነው:: እንዴት ቢሉም፣ ሰው ለሚያደደርገው ነገር ተገቢነት አንዳችም ጥርጣሬ እንዳይኖረው ያስፈልጋል:: ታዲያ የኔ ኅሊና

t.me/OLDBOOKSPDF

ከወዴት እረፍት ያግኝ? ከድርጊት የሚያሰማራኝ ዋነኛ ምክንያት ከየት ይምጣ? አቢይ የምግባር መመሪያየስ የት አለ? እነዚህን ከየት ላግኛቸው? ቁጭ ብዬ በሃሳብ ስታክት፣ እጅግ አስፈላጊ የምለው ዓላማ ከኋላው ሌሎች ይበልጥ ጠቃሚ የሆኑ ዓላማዎች አግተልትሎ ይመጣና፣ አእምሮዬ በፍፃሜ አልባ የአስፈላጊነት ደረጃ ልዩነት ይተራመሳል:: የአእምሮ ንቃትና የማሰብ ማሰላሰል ምንነቱ ይህ ነው:: በዚህም ወደ ተፈጥሮ ሕግ ስንክሳር እንመለሳለን:: የዚህ ሁሉ ምሥጢሩ ምንድነው?

ቀደም ስል ስለብቀላ የነገርኩዎትን ያስታውሳሉ? (መረዳትዎን እጠራጠራለሁ):: ሰው የሚበቀለው ብቀላው በፍትህ የተገባ ነው ብሎ ስለሚያምን ነው ብዬ ነበር:: እምነቱ ለድርጊቱ ግልፅ ዓላማና መንስኤ ይሆንለትና ጥርጥር ሳይገባው ብቀላውን በንፁህ ልቦናው ይፈፅማል:: እኔ ግን ከብቀላዬ ፍትህም ሆነ ተገቢነት አላይበትም:: ስበቀል ከክፋት የተነሳ ነው:: ክፋቴ ደግሞ ከጥርጣሬዬና ከሌላው ነገር አብልጦ የሚያመዝንበት ጊዜ አለ:: ያ ሲሆን፣ ክፋት ተገቢ የምግባር ምክንያት ባይሆንም ራሱ የዓቢይ መንሥኤን ቦታ ይዞ ቁጭ ይላል:: ክፋት በውስጤ ባይኖር ኖሮ ምን ይውጠኛል? እኔ ዘንድ፣ (እንደገና በንቃተ አእምሮ ሕግጋት ምክንያት) ክፋት እንኳን በነገሮች መፈራረራስ ሂደት ያልፍና በድንገት የምበቀልበት ይጠፋል፣ ምክንያቶቹ ይተናሉ፣ የምወነጅለውን አጣለሁ፣ ቁጣዬ ቁጣ መሆኑ ይቀርና የዕድል ጉዳይ ይሆናል፤ ልክ ማንም እንደማይጠየቅበት የጥርስ ሕመም:: ከዚያም አንድ ላደርገው የቀረኝ ነገር ቢኖር ግድግዳውን አክርሬ መውገር ብቻ!

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደዚሁ የድርጊት ምክንያት ማግኘት ሲቸግርዎ፣ እጆችዎን ሰብስበው፣ ሁሉን እርግፍ አድርገው ይተዋሉ:: ግን እንዲሁ በደፈናው የስሜትዎን ፈረስ ጋልበው ሳያስተውሉና፣ የምግባርዎን መንሥኤ ሳይጨብጡ ቢከንፉ፤ ስራ ፈተው ቁጭ ከማለት ለማምለጥ ብለው ቢጣሉ ወይም ቢያፈቅሩ፣ ቢቆይ ቢዘገይ ከነገወዲያ፣ እያወቁ ለራስዎ ስለዋሹ ራስዎን ይንቃሉ::

• እኔ ራሴን አዋቂ አድርጌ የማይበት ምክንያት በሕይወቴ አንዳችም ነገር ጀምሬ መጨረስ ባለመቻሌ ይሆናል:: ከፊሉን፣ አውደልዳይ ቀላማጅ ይበሉኝ፣ ጠንቀቢስ ረባሽ፣ ወሬኛ (እንደሌሎቻችንም) :: ግን የእእምሮ ብቃት ያላቸው ሰዎች ዋነኛ ትጋት መቀላመድና እያወቁ በወንፊት ውሃ ማፈስ ከሆነ ምን ዋጋ አለው?



በስንፍና ምንም ማድረግ ባልችል ኖሮ ምንኛ መልካም ነበር! ያ ቢሆን ኖሮ የቱን ያህል ራሴን ባከበርኩት! አዩ ሌላው ቢቀር አንድ በውል የማውቀው ችሎታ ኖረኝ ማለት ነበር:: ጥያቄ:- አንተ ማነህ? መልስ:- ሰነፍ ሰው:: ይህን ስለራሴ መስማት ምንኛ ባስደሰተኝ፣ በወጉ ተለይቼ ታውቄ፣ እገሌነት አገኘሁ ማለት ነበር:: " ሰነፍ ሰው::" ይህ እኮ ስም ነው፤ ሥራና ማዕረግ:: እውነቱን ነው:: የምርጦች ክበብ አባል ሆኜ፣ ዋና ዓላማዬና ምግባሬ ሳላሰልስ ራሴን ማክበር

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሆናል:: አንድ የማውቀው ሰው የውድ መጠጦች ስም አዋቂ በመሆኑ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ይኩራራ ነበር:: በሙያው ታላቅነት አንድም ቀን ጥርጣሬ ሳይገባው ኖሮ፣ ነሊናው የሰላምና የድል አክሊል ደፍታ ነበር ነፍሱ ከስጋው የተለየችው:: ይህ ሰው ታዲያ ግብዝ ነው ብለው ያስባሉ? አልነበረም:: ትክክለኛ ሰው ነበር:: በበኩሌ ቢሳካልኝ ሙያዬን እመርጥ ነበር:: አውደልዳይ፣ ከርሳም:: ተራ ወሮበላ ሳይሆን የመልካሙና የከበረው ነገር ሁሉ ተቆርቋሪ:: ምን ይመስልዎታል? ይህን ለረጅም ጊዜ ተመኝቼዋለሁ:: ይህ "መልካምና የከበረ" የሚሉት ነገር በአርባ ዓመቴ እየነካካ ሰላም ይነሳኛል:: አዩ፣ አሁን የአርባ አመት ሰው ነኝ:: ቀድሞ ቢሆን ኖሮ ሌላ ታሪክ ነበር:: አሁን ያኔ ቢሆን ኖሮ፣ ለራሴ የሚሆነኝ ስራ ፈልጌ አገኝ ነበር:: ለምሣሌ:- ለመልካሙና ለከበረው ነገር ሁሉ ፅዋዬን እያነሳሁ መጨለጥ:: ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ የእንባ ዘለላዬን ከመጠጤ እየቀላቀልኩ መጎንጨት:: ከልክስክሱና ከአልባሌው ምናምንነቴ መሐል መልካምና ክቡር ነገር መመልከት መቻል:: ዕንባ እንደጅረት ከዓይኖቼ ማፍሰስ:: ሥዕል ባየሁ ቁጥር ለሠዓሊው፣ መፅሐፍ በታተመ ቁጥር ለደራሲው ጤንነት ፅዋዬን እያነሳሁ መጨለጥ:: መልካምና ክቡር ነገር ስለምወድ::

ከዚያም ለዚህ ብቻ እንዲያከብሩኝ እጠይቅና፣ ተገቢውን ክብር የነፈጉኝን አሳድዳቸዋለሁ:: ቦርጭ ሆዴ ላይ አንጠልጥዬና ሦስት ድርብ አገጭ ኮልኩዬ፣ በመንገድ ያየኝ ሁሉ " ሰው ማለት እንዲህ ነው ! እንዲህ ነው እንጂ ታላቅ ሰው ! " እያለኝ ኖሬ በሰላም መሞት:: እርስዎ ያሻዎትን ይበሉ እንጂ በዚህ የከፋ ዘመን ይህን መስማት ያስደስታል:: ግና ይህ ሁሉ እንዲሁ ጣፋጭ ምኞት



t.me/OLDBOOKSPDF

ነው:: ማን ነበር ለመሆኑ ሰው ርጉም ድርጊት የሚፈፅመው በዕውነት የሚፈልገውን ነገር ስለማያውቅ ነው እንጂ፣ ሊበጀው የሚችለውን ነገር ያይ ዘንድ ዓይኖቹ ቢገለጡ ኖሮ፣ ከርኩሰት መዘፈቁን ትቶ በቅን መንገድ ይጓዝ ነበር ብሎ መጀመሪያ የተናገረው? ማን ነበር "የሰው እውቀቱ ከላቀ፣ በእውን የሚጠቅመውን ስለሚያውቅ ከሚጎዳው ነገር ይርቅ ነበር" ያለው? ይህ ከሆነማ ያወቀ ሰው መልካም ነገር ብቻ ያደርጋል ማለት አይደለምን? ይህን ያለው ሰው እንዱንም የማያውቅ፣ ጥሬ ነው:: ማነው እስቲ ባለፉት ሺህ ዓመታት የሰው ልጅ የሚበጀውን ብቻ ሲያደርግ ያየው? ስንት ጊዜ ነው ሰዎች እያወቁ፣ የሚጠቅማቸውን ነገር በፈቃዳቸው ገለል አድርገው፣ ቀናውን መንገድ እያዩት እምቢ ብለው፣ ማንም ሳያስገድዳቸው፣ ከሚበጃቸው ሸሽተው በጨለማ የጥፋት መንገድ ፍለጋ የሄዱት?

ይህ የሚያሳየው ታዲያ፣ ሰዎች ከጥቅም የበለጠ የሚያጓጓቸው የራሳቸውን ፈቃድ በግትርነት መፈፀም መሆኑን ነው:: ጥቅም! ለመሆኑ ጥቅም ማለት ምንድነው? ለሰው የሚበጀው ምን እንደሆነ በትክክል ሊገልፁልኝ ይችላሉን? አልፎ አልፎ የሚበጅ ነገር የሚገኘው በሚጎዳ መንገድ ቢሆንስ? " ጎዳህ " ሲሉኝ " ጠቀመኝ " ብዬ ካሰብኩ፣ የምናውቀው የጥቅምና የጉዳት ምንነት ተንኮታኮተ ማለት አይደለም? እርስዎ ምን ያስባሉ? እንዲህ ያለ አጋጣሚ የሚኖር ይመስልዎታል? ይስቁብኛል? እንዳሻዎት፣ ይሳቁ:: ግን ይህን ይመልሱልኝ:- ለሰው የሚበጀው ነገር በውል ተለይቶ ይታወቃል? እኛ ይበጃል ከምንለው ክልል የማይመደቡ ጥቅሞች ይኖሩ ይሆን? እርስዎ ለሰው ይበጃሉ የሚሏቸው ነገሮች ከስታቲስቲክስ ስሌትና ከሳይንሳዊ የምጣኔ ሃብት ቀመር የሚስማሙ

t.me/OLDBOOKSPDF

ናቸው:: እርስዎ የሰውን ጠቀሜታ የሚመለከቱት በብልፅግና፣ በሃብት፣ በነፃነት፣ በዓዕምሮ እረፍትና በመሣሠሉ ነገሮች መነፅር ነው:: ስለዚህ እነኚህን በሚፃረር መንገድ የሚጓዝ ሰው በእርስዎም ሆነ በእኔ ዓይን ግራ የገባው፣ ወይም ጨርቁን ጥሎ ያበደ ሰው ይሆናል ማለት ነው:: አይደል? የሚገርመው ነገር፣ ሊቃውንቱ ለሰው የሚጠቅመውን ሲያውጠነጥኑና ሲያስሉ ሁሉም አንድ ነገር ለምን ይዘነጋሉ? የስሌቱና የግምቱ ሁሉ ምሰሶ ሆኖ ሳለ፣ ይህን ነገር ከቦታው የማያስቀምጡት ለምንድነው? ችግሩ ግን፣ ይህ ዓይነቱ ጥቅም ካንዱም ሠፈር ይመደብ ዘንድ ያዳግታል::

ለምሣሌ አንድ ጓደኛ አለኝ:: ሰው ሁሉ ያውቀዋል:: እርስዎም ያውቁታል:: ጓደኛዬ አንድ ነገር ለማድረግ ሲያቅድ ነገሩ እንዴት በትክክል፣ በደንቡ መደረግ እንዳለበት ግልፅ አድርጎ በርቱዕ አንደበት ይነግርዎታል:: ከዚያም አልፎ ለሰው በርግጥ የሚያዋጣውን ነገር ተንትኖ ያስረዳዎታል:: የሚበጃቸውን የማያውቁ ቂሎችንና የቅንነትን ምንነት ያልተገነዘቡ፣ እርቆ ማስተዋል የተሳናቸውን ሰዎች ያንቋሽሻቸዋል:: ይህ ሰው ታዲያ አንድ አስራአምስት ደቂቃ ያህል ቆይቶ፣ ምንም ነገር ሳያስገድደው፣ ከሚበጀው ነገር ሁሉ በበለጠ፣ ከውስጡ በመነጨ ነገር ተገፋፍቶ፣ ቀደም ሲል ስለአግባብ ሲለፍፍ የነበረውን የሚፃረር ነገር ያደርጋል:: ጓደኛዬን የሚመስሉ ብዙ ሰዎች ስላሉ እሱን ብቻ አይፍረዱበት::

አዎ እንግዲህ ይኸው ነው:: ለሰው ከሌላ ፍላጎቱና ጥቅሙ ሁሉ የሚበልጥበት፣ ለርሱም ሲል ሕግን ጥሶ፣ አግባብን ረግጦ፣ ሰላምና ብልፅግናን ወዲያ ብሎ የሙጥኝ የሚለው፣ የጥቅሙና

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚበጀው ነገር ሁሉ ቁንጮ የሆነውና ሊቃውንቱ የዘነጉት የሰው ምርጫው ሌላ ነው::

" ታዲያ እርሱስ ቢሆን የጥቅም አይነት አይደል? " ብለው ያቋርጡኝ ይሆናል:: ረጋ ይበሉ:: የዚህን ስር ፈልፍለን እናገኘዋለን:: ደግሞ የቃላት ጨዋታ አይምሰልዎ:: የሚያስገርመው፣ ይህ ዓይነቱ ጠቀሜታ በወጉ የተነተንናቸውን የሚበጁና የሚጎዱ ነገሮች ድንበር አፍርሶ፣ በሰው ወዳድ ሊቃውንት ለደኅንነት የተቀየሱ መስመሮችን የሚያናጋ ነው:: ባጭሩ እዚህ ግባ የማይሉት ነው::

የዚህን ጥቅም ምንነት ከማውጣቴ በፊት ግን ሳልፈራ ልናገር የምፈልገው ነገር ቢኖር:- እነኚህ ሁሉ ድንቅ ፈለጎችና የሰውን ልጅ ስለሚበጀው ነገር አስተምሮ ከጥፋት ለማዳን የታለሙት ዕቅዶች በሙሉ፣ ለጊዜው በኔ አስተያየት ከንቱ የሎጂክ ጨዋታ ናቸው:: ሰው የሚበጀውንና የሚያዋጣውን ተከትሎ የመሄድ ዕውቀቱ ቢኖረው ሕይወት እንከን አልባ ትሆን ነበር ብሎ ማሰብ፣ ስልጣኔ ሰውን የበለጠ ሩኅሩኅ አድርጎ፣ የደም ማፍሰስና የጦርነት ዝንባሌውን ያጠፋል እንደማለት ይቆጠራል:: ነገር ግን ሰው ነገሮችን በዕንስ ሃሳብ ምላጭ የመተልተልና በፍልስፍና ድር የመቋጠር በሽታ የተጠናወተው ፍጡር ስለሆነ፣ ሆን ብሎ እውነቱን አጣሞ፣ ዓይንና_ጆሮውን ደፍኖ የገዛ ራሱን እምነት የትም ገብቶ ለማረጋገጥ ዝግጁ ነው::

ይህን ምሣሌ የወሰድኩበት ምክንያት ግልፅ በመሆኑ ነው:: እስቲ ዞር ብለው ይመልከቱ:- ደም እንደጅረት ይፈሳል:: ስልጣኔ

t.me/OLDBOOKSPDF

በምን ስልጣኑ ነው የሚያለዝበን? ሥልጣኔ የሚያደርገው ነገር ቢኖር፣ ሰው ለስሜታዊ ደስታ ያለውን ጥማት ማብዛትና ማጎልበት ነው:: ይህን ታሪካችን ውስጥ ያገኙታል:: የነጠሩት ደም አፍሳሾች ሁሉ ሥልጡን የተባሉ ነበሩ::

የሆነው ሆኖ ግን፣ ሰው በስልጣኔ ምክንያት የደም ጥማቱ ባሰበት ማለት ቢያጠራጥርም፣ የደም ማፍሰስ ሁኔታው እጅግ ፀያፍና አስቃቂ እየሆነ መምጣቱ አይካድም:: የድሮ ሰው መግደልን የፍትህ ጉዳይ አድርጎ ስላየው መጥፋት አለባቸው ብሎ ሲያምን ነበር በንፁህ ልቡናው የሚገድለው:: የመግደልን ምንነት ከርሱ ይበልጥ አጣርተን የምናውቀው እኛ ግን ያለገደብ እንጨፈጭፋለን:: የትኛው ይከፋል? መልሱን ለእርስዎ እተዋለሁ:: የሮማዋ ክሊዎፓትራ ከገረዶቿ ጡት የወርቅ መርፌ እየተከለች፣ ሲያለቅሱና ሲወራጩ ማየት ትወድ ነበር ይባላል:: ይህ የሆነው ታዲያ ካሁኑ ጋር ሲነፃፀር በኋላ ቀርነት ዘመን ነው ይሉኝ ይሆናል:: ካስተዋሉ ግን አሁንም ቢሆን ክሰዎች አካል መርፌ ይሰነቀራል:: ምንም እንኳን ሰው ነገሮችን አጣርቶ ማየት የቻለ ቢሆንም፣ ሳይንስና ሐቅ በሚጠቁሙበት መንገድ ከመጓዝ ርቆ ይገኛል:: እርስዎ ግን ሰው በትምህርት አማካይነት ካረጁ ልምዶቹ ተላቅቆ፣ በሳይንስና በቀና አስተሳሰብ ተመርቶ ሊታረም እንደሚችል አይጠራጠሩም:: ሰው በገዛ እጁ ከስህተት ታቅቦ፣ ፈቃዱን ከሚበጀው ነገር ጋር ማቃቃሩን እርግፍ አድርጎ እንደሚተው እርግጠኛ ነዎት:: ወይም ደግሞ ሰው የራሱ ነፃ ፈቃድ ያልነበረውና የሌለው የፒያኖ ቁልፍ ስለሆነና የሚኖረውም በተፈጥሮ ሕግጋት በሚገዛ ዓለም ውስጥ ነውና የሚያደርገው ነገር ሁሉ ከግል ፈቃዱ የመነጨ ሳይሆን በነዚህ ሕግጋት መሠረት እንዲሁ የሚከሠት ነገር



t.me/OLDBOOKSPDF

መሆኑን ሳይንስ ያስተምረዋል ይሉኝ ይሆናል:: እኔ ግን አልስማማም::

ምስጢሩ ይህ ከሆነ፣ መደረግ የሚኖርበት ነገር ቢኖር እነኚህን የተፈጥሮ ሕግጋት ፈልጎ ማግኘት ነው:: ያም ሲሆን ሰው ለድርጊቱ ተጠያቂ መሆኑ ይቀርና የሕይወት ጥያቄዎች መልስ ያገኛሉ:: የሰው ድርጊቶች ሁሉ በእነዚህ ሕግጋት መሠረት ተሰልተው ይወሰኑና በልዩ መዝገብ ተቀምረው ይቀመጣሉ:: እንዲያውም መዝገበቃላትና ኢንሳይክሎፒዲያ የመሳሰሉ፣ ሁሉ ነገር በቅድሚያ ታልሞና ተሰልቶ የሚሰፍርባቸው መፃሕፍት ይታተሙና ከዚያ ወዲያ ምንም ግራ የሚያጋባ፣ ያልተጠበቀ እንግዳ ነገር በሰው መታየቱ ያከትማል::

ከዚያም (ይህን የሚሉት እርስዎ ነዎት) ሁሉ ነገር ያሳንዳች ስህተት ተሰልቶ የተዘጋጀበት፣ እንከን አልባ የሆነ የኢኮኖሚ ግንኙነት ይፈጠርና ጥያቄዎች ሁሉ ከመወለዳቸው በፊት መልስ ያገኛሉ:: የሰው ልጅ የድል አክሊል ይቀዳጅና የብልፅግና ጎህ ይቀዳል:: ታዲያ የዚህ አይነቱ ሕይወት እጅግ አሰልቺ አይሆንም? (ይህን የምለው እኔ ነኝ) :: ሁሉ ነገር በሠንጠረዥና በሂሳብ አማካይነት በቅድሚያ ተቀምሮ ከታወቀ፣ ሁሉ ስሙር ቢሆንም እንኳን የሥራ ፋይዳው ምን ይሆናል?

ሰውስ ከመሰልቸት የተነሳ ምን ማሰብ እንደሚጀምር ማን ያውቃል? የወርቅ መርፌ ከሰው አካል የተሰነቀረው ከድብርት ብዛት አይደል? ያ ብቻ አይደለም:: ሰዎች ደግሞ በወርቅ መርፌ መወጋት



t.me/OLDBOOKSPDF

ይከጅሉ ይሆናል (ይህ የኔ ሃሳብ ነው):: ምክንያቱም ሰው ሲባል ደደብ ነው:: ከእግር እስከራሱ ድድብና የወረሰው:: ምናልባትም ደደብ ባይሆን እንኳን የለየለት ምሥጋና ቢስ፣ በውለታቢስነቱ ተወዳዳሪ የሌለው ፍጡር:: ለምሣሌ በዚያ ቅድም ባወሳነው፣ ሁሉ በሠመረበት ምሉዕ የነገው ሥርዓት አንድ ርጉም ሰው ከመሬት ብድግ ብሎ፣ እጆቹን ወገቡ ላይ አድርጎ፣ " ይህን እንከን አልባ ሥርዓት በርግጫ ብለን እንኮታኩተን፣ ላንዳፍታ እንደቅጥያጣ ፈቃዳችን ብንኖር ምናለበት? " ቢል አይገርመኝም:: ቢልም ባልከፋም ነበር:: የሚያሳዝነው ግን ይህ ሰው ወዲያው ተከታዮች ያገኛል፤ የሰው ፍጥረቱ እንዲህ ነውና:: የዚህ ሁሉ መሠረቱ ታዲያ አንዲት ነገር ናት:: ሰው ሲባል፣ የትም ሆነ መቼም በሚበጀውና በአግባብ መንገድ ከመመራት ይበልጥ፣ የራሱን ፈቃድ መከተል ይመርጣል:: ይህ ፈቃዱ ከጥቅሙ ጋር የሚቃረን ሊሆን ይችላል:: አንዳንዴ እንዲያውም ማድረግ የሚሻው ነገር ከሚበጀው ጋር መቃረን ይኖርበታል::

የአንድ ሰው ያልተረገጠ የራሱ ፈቃድ፣ የራሱ ጋጠወጥ ቅዥት፣ የራሱ እብደት የነካካው ምኞትና ፍላጎት ነው ቅድም ተዘነጋ ያልነው፣ ከዚህ ስፈር ሊሉት የሚያስቸግር አጉል ነገር፣ ሥርዓትና አግባብን ገደል የሚከታቸው፣ የጥቅምና የሚበጅ ነገር ሁሉ ቁንጮ:: እንያስ አዋቂዎች የሰው ፍላጎት ጤነኛና ክቡር ነው የሚለውን ሃሳብ ከየት ነው ያመጡት? ሰው በእውን የሚበጀውን ብቻ የሚሻ ይመስላቸዋልን? ሰው የሚሻው የግል ፈቃዱን መፈፀም ብቻ ነው፤ ለዚህ የገዛ ራሱ ነፃ ፍላጎት የሚከፍለው ዋጋ ቢበዛም ሆነ፣ የቀየሰው መንገድ የትም ቢያደርሰው::

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሃ . . . ሃ . . . ሃ " ብለው እየተንከተከቱ ያቋርጡኛል:: "ግን ይቅርታህንና ምኞት የሚባል ነገር የታለ? ሳይንስ ሰውን አብጠርጥሮ ከማወቁ የተነሳ ይህ ምኞትህና ነፃ ፈቃድህ ሁሉ . . . . " አንድ ጊዜ ይጠብቁኝ እባክዎን:: እኔም የምለው እሱን ነው:: ያሰብኩትን ነው የነገሩኝ:: የሰው ምኞት ከምን እንደሚመጣ ማንም አለማወቁ ጥሩ ነገር ነው ለማለት ስዘጋጅ ሳይንስ ትውስ አለኝና ንግግሬን ገታሁ:: ወዲያው ታዲያ እርስዎ አነሱት:: ወደፊት የሰው ፈቃድና ምኞትን የሚፈጥረው ምክንያት፣ የሚከተለው ሥርዓት፣ የሚያድግበት መንገድና አካሄዱ ቢታወቅና ጥንቅቅ ባለ የሂሳብ ስልት ተቀምሮ ቢቀመጥ፣ ሰው ወዲያውኑ መመኘቱን የሚተው አይመስልዎትም? ማን በሠንጠረዥአማካይነት ማለምና መመኘት ይፈልጋል? ይህ ሲሆን ሰው የፒያኖ ቁልፍ ሆነ ማለት አይደል? ግን ሰው ያለፍላጎቱ፣ ያለምኞቱና ያለነፃነቱ ምኑን ሰው ሆነው? ምን ያስባሉ?

አብዛኛውን ጊዜ የምንከጅለው በድንቁርናችን ምክንያት ይጠቅመን በሚመስለን ነገር ላይ ተመስርተን ስለሆነ ስህተት ነው:: ዘወትር ከንቱ ነገር የምንሻው፣ ባለማወቅ ከምኞታችን ዘንድ በቀላሉ ያደርሰን እየመሰለን ነው:: ግን ይህ ሁሉ ተብጠርጥሮ ሲገለፅና በደንብ ተዘጋጅቶ ከወረቀት ላይ ሲቀመጥ ( ይህ ደግሞ አስቸጋሪ አይደለም:: ሰው ሊካነው የማይችለው የተፈጥሮ ሕግ አለ ብሎ መገመት ነውር ነው)፣ ያኔ መከጀል የሚባል ነገር አይኖርም:: ለምን ቢሉም፣ አንድ ቀን የሰው ክጀላው ከሚሆነው ጋር ከተጋባ፣ ሰው መከጀሉን ትቶ በአግባቡ ማሰብ ይጀምራል:: ካላበዱ በቀር የማይረባ ነገር ተመኝተውና የሚሆነውን ወዲያ ብለው የሚጎዳዎን አይመርጡምና::

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደፊት ምኞትና ቀና አእምሯዊ አስተሳሰብ በግልፅ ስለሚብራሩና፣ ነፃ ፈቃዳችን የምንለውን ነገር የሚገዙት ሕግጋት ስለሚከሰቱ፣ ቀልዴን አይምሰልዎ፣ በዚሁ መሠረት ልንፈቅድ የሚያስችለን ሠንጠረዥ ይዘጋጃል:: ለምሳሌ ምላሴን በሰው ላይ ባወጣና፣ ይህን ያደረግኩት ልቆጣጠረው በማልችለው ኃይል ተገፍቼ እንደሆነ፣ ምላሴንም የቱን ያህል ልጎለጉል እንደተገደድኩ በስሌት አድርገው ሊቃውንት ቢያረጋግጡልኝ ከነፃነቴ ምን ተረፈኝ ሊባል ነው? በተለይም ደግሞ የተማርኩ፣ ጥቂት ያነበብኩ ሰው ከሆንኩ? የወደፊት ሕይወቴን እስከ ሰላሳ ዓመት አስልቼ ቁጭ! ይህ እውን ሲሆን ማድረግ የሚያሻን ነገር አይኖርም:: የሚመጣውን ዝም ብለን መቀበል ብቻ:: የሚሆነው ሁሉ እንደፈቀደው እንጂ እንዳሰብነው እንደማይሆንና፣ ተፈጥሮ ዕቅዷን ለኛ መግለጥ እንደማይገዳት ሳንታክት መገንዘብ ይኖርብናል:: ያ ነው ዋጋው!

ይቅርታ፣ ብዙ ተፈላሰፍኩ:: ምን ላድርግ? አርባ ዓመታት ለራሴ በፈጠርኩት ስርቻ ስለኖርኩ ነው:: የልቤን አደርስ ዘንድ ይፍቀዱልኝ:: አዎ፣ አርቆ አስተዋይነት መልካም ነገር ነው:: የሰውን የማሰብ ችሎታ ከተግባር ላይ ያውላል:: መሻት፣ መከጀል ግን የሕይወት ሁሉ ድምር ውጤት ነው፤ ሕይወት ከነጥማትና ርካታዋ:: ሕይወት ቅጥ ያጣች ምስቅልቅል ብትሆንም እንኳን፣ የምኖረው የኑሮን ፅዋ እስከአተላው ልጨልጥ እንጂ፣ የሕይወቴ ቁራጭ አካል የሆነውን የማሰብ ችሎታዬን ለመኮትኮት ብቻ አይደለም:: አእምሮ ከተማረው ውጭ ምን ያውቃል? የሰው ተፈጥሮ ግን፣ የሃሳብም ሆነ የጭፍን ሂደት ሙሉ ሕይወት ነው:: ቢሳሳትም እንኳን ሕያውነቱ አይካድም::

ያሳዘንኩዎት ይመስለኛል:: የተማረና የተመራመረ የወደፊት ሰው እያወቀ ከንቱውንና ጎጂውን የሚከጅልበት አንድ ሁኔታ መኖሩን ለመቶኛ ጊዜ እነግርዎታለሁ:: ይህን የሚያደርገውም



t.me/OLDBOOKSPDF

በአግባቡ የመሻት ግዴታው ሳይታሰር፣ የመከጀል መብቱን ለመጠበቅ ሲል ነው:: ይህ ቂልነት፣ ይህ የወፈፌ ፍላጎታችን አንዳንዴ ከሚበጀን ነገር በላይ ይልቅብናል:: ጥፋት እንደሚያመጣብንና ቀና አስተሳሰባችን ከሚመክረን ጋር እንደማይጣጣም ስናውቀው እንኳን:: ምክንያቱም፣ ይህ ጋጠወጥ ከጀላ ውዱን ሐብታችንን፣ ግለሰባዊ ባኅሪያችንን ይጠብቅልናል::

ግለሰባዊነት የፀጋ ሁሉ ጫፍ ነው ብለው የሚከራከሩ አሉ:: በርግጥ ከተፈለገ የሰው መሻት በውን ከሚበጅ ነገር ጋር ሊስማማ ይችላል፤ አልፎ አልፎ እንዲህ ሲሆንም ሰውዬውን ጠቅሞ ያስሞግሰዋል:: መሻት ግን ይበልጡኑ ጊዜ እምቢ ብሎ ይጣመማል:: ያም ሆኖ ግን ለሚሻው ይበጀዋል:: አንዳንዴም ውዳሴ ይገባዋል::

ለምሣሌ ያህል ሰው ደደብ አይደለም እንበል:: (በውነቱ ደደብ ነው ማለት አይቻልም:: ሰው ደደብ ከሆነ ብልሁ ማን ሊሆን?) ደደብ ባይሆንም እንኳን ግን ምሥጋና ቢስነቱ አይካድም:: አንገት የለሽ፣ ምሥጋና ቢስ! ሰው የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ ሁለት እግር ወሮታቢስ እንስሳ ነው ብዬ አስባለሁ:: ግን ይህም አይደለም የሰው ዋነኛ እንከን:: ዋና በሽታው የዘላለም ልክስክስነቱ ነው:: ከኖኅ ዘመን የጥፋት ውሃ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያላሰለሰ ልክስክስነቱና ቅጥአልባነቱ:: ልክስክስነት ከአስተዋይነት ጉድለት እንደሚመነጭም ይታወቃል:: እስቲ የሰውን ታሪክ ይቃኙት:: ምንድነው የሚያዩት? ድንቅና ታላቅ ትዕይንት? የሰው ልጅ የፈጠራና የሕብረት ሥራ ተዓምር? የጦር ሠራዊቱን የደንብ ልብስና መሣሪያ ብቻ እንኳን ቢመለከቱ እሱ ብቻ ግሩም አይደል! ይሰለቻል:- ውጊያ፣ ጦርነት:: ትናንት፣ ዛሬ፣ ነገ መተላለቅ:: እጅ እጅ ይላል::



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለዓለማችን ታሪክ ምንም ማለት ይቻላል:: ደህነኛ ቀርቶ ያበደ ሰው የሚለው እንኳ እውነት አይጠፋበትም:: ታሪካችን በአጠቃላይ ቅንና መልካም ነው ልንል ብንሻ ግን ቃሉ ከገሮሮችን እንደሞራ ይጣበቃል::

በሌላ በኩል ዘወትር የምናየው የሚገርም ነገር አለ:: ልብ ብለው ከሆነ እኒያ እንኳን አስተዋይ ሰዎች፣ ሳይታክቱ በወግና በሥርዓት ነገሮችን ማድረግን እንደሕይወታቸው ዋና ዓላማ የሚቆጥሩ፣ ነፍሳቸው ለሰው ልጅ ቀና ፈለግ የምታሳይ ብርሃን መሥላ የምትታያቸው፣ በምድር ላይ ያለስህተት መኖር የሚቻል የሚያስመስሉና በሰው ማፍቀር የተጠመዱ ሰዎች በስተኋላ ታላቅ የሕይወት መመሪያቸው ላይ ተፍተው፣ ጉድ የወረሰው ቅሌት ውስጥ ሲከተቱ ተመልክተናል::

እና እስቲ አሁን ልጠይቅዎ:- ይህን በመሣሠሉ እንግዳ ባህሪዎች ከተሞላው የሰው ዘር ምን ይጠበቃል? በምድር ፀጋ ቢያከናንበትም ሆነ፣ በደስታው የባህር ውሃ ውስጥ የሚታየው የትንፋሹ አረፋ ብቻ እስኪሆን ድረስ እስተራስ ፀጉሩ በሐሴት ቢዋኝ፣ በፍፃሜ አልባ ብልፅግና ተባርኮ ኑሮው እየተንደላቀቀ ያሻውን መብላት፣ መንፈላሰስና የዓለምን ታሪክ መመዝገብ ብቻ ቢሆንም እንኳን፣ በሰፈረበት የምስጋናቢስነት መጋኛ ተገፋፍቶ ጥፋት መፈፀሙ አይቀርም:: ፀጋውን አደጋ ላይ ጥሎ እጅግ ፀያፍ የሆነ ምግባር ማድረግ ይከጅላል:: ይህን የሚያደርገው ታዲያ ከመልካሙ በረከት ላይ የግሉን መርዛም ሰንኮፍ እተክል ብሎ ነው:: ከገዛ ራሱ ቅዠት፣ ከብልግናው የሙጥኝ ብሎ ተጣብቆ፣ ሰው ሰው እንጂ የፒያኖ ቁልፍ እንዳልሆነ ለራሱ ለማረጋገጥ ይጥራል (ይህ የሕይወትና የሞት ምሥጢር የሆነ ይመስል)::



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን የሚያደርግበት አቅም ባይኖረው እንኳ ጥፋትና ትርምስምስን ፈጥሮ ስቃይ ይዘራል:: የሆነው ሆኖ ያሻሁት ይፈፀም ይላል:: ምድርን ይረግማታል:: (በነገራችን ላይ ሰው ብቻ ነው የመርገም ችሎታ ያለው፣ ከእንስሳትም ተለይቶ የታደለው መርገም በመቻሉ ነው) :: ይህ ሁሉ ሁካታ፣ ትርምሥምስና እርግማን በቅድሚያ ታልሞና ተሰልቶ ሊታወቅ ስለሚችል በዚህ ምክንያት ጥፋትና ሽብር ከመፈጠራቸው በፊት ይቀጩና፣ አግባብና አስተዋይነት ይነግሳሉ ይሉኝ ይሆናል:: ያ ከሆነ ግን፣ ሰው ሲያውቅ እእምሮውን ስቶ ያብድና የማሰብና የማስተዋልን ሸክም ከትከሻው አውርዶ የድርጊቱን ጠንቀኛነት ዕውቀቱን በአውቆ አበድነቱ ጥሎ ሽፍኖ የፈቀደውን ያደርጋል:: በዚህ ጥርጥር የለኝም:: ምክንያቱም የሰው ዋና ፍላጎቱ የፈቀደውን ማድረግ የሚችል ፍጡር መሆኑን ዘወትር ለራሱ ማረጋገጥ ነውና:: ለዚህ ሲል ሕይወቱን ቢያጣ፣ ወይም ሁሉን ትቶ ከዋሻ ቢኖር አይገደውም:: ከዚህ ሁሉ በኋላ ታዲያ ሰው በሰውነቱ መመፃደቁና በፈቃዱ አልበለጤነት መኩራራቱ እንዴት ይቀራል?

ፈቃድህን ማን ነጠቀህ ብለው ይጮሁብኛል (አሁንም ሊጮሁብኝ ከፈለጉ) :: መሻቴ በተፈጥሮ ሕግ አማካይነት በፈቃዱ ከሚጠቀመኝ ነገር ጋር የሚስማማበትን መንገድ ስለመፈለግ ነው የምንወያየው ይሉኛል:: ግን እስቲ ይመልከቱ:: ሠንጠረዥና ሒሳብ ባሉበት እንዴት አይነት ያልተረገጠ ፈቃድ ነው የሚኖረው? ሌላው ሁሉ ቁምነገር ቀርቶ ዋናው ጉዳይ 'ሁለት ጊዜ ሁለት አራት ' ብቻ ሲሆን:: ባልፈልግስ ሁለት ጊዜ ሁለት አራት መሆኑ ይቀራል? ይህን ነው የሰው ነፃ ፈቃድ የሚሉት?

t.me/OLDBOOKSPDF

አዎ ስባልት ነው:: ቀልዴም እንደማይጥም ራሴ አውቀዋለሁ:: ሁሉን ግን ከቀልድ አይቁጠሩት:: እየቀለድኩ ጥርሴን አፋጭ ይሆናል:: በጥያቄዎቼ እየተሰቃየሁ ነውና እርስዎ ይመልሱልኝ:: ለምሳሌ እርስዎ ሰውን ከጥንት ልማዱ ለማላቀቅና ጠማማ ፈቃዱን በሳይንስ ለማቃናት ይሞክራሉ:: ነገር ግን ሰው እንደዚህ መቃናት እንደሚችልም ሆነ ሊቃና እንደሚገባው እርግጠኛ ነዎት? የሰው ፍላጎቱ መታረም እንዳለበትስ ያውቃሉ? ባጭሩ፣ የዚህ ዓይነቱ እርማት ለሰው እንደሚበጀው ማን ነገረዎት? እንዲያውስ በቀና አስተሳሰብና በስሌት ከተረጋገጠው ትክክለኛ ፍላጎቱ የሚፃረር ነገር አለማድረግ ለሰው ልጅ ሁሉ መቼም እንደሚበጀው ምን ሹክ አለዎት? ይህ የእርስዎ ምኞት ብቻ ቢሆንስ? ቅን ሓሳብና አግባብ የሰውን ልጅ መግዛት ባይቻላቸውስ? ያበድኩ ይመስልዎት ይሆናል:: ቢሆንም ሃሳቤን እገልፅልዎታለሁ:: ሰው ከምንም በላይ የፈጠራ ችሎታ ያለው እንስሳ መሆኑን እስማማለሁ:: ወደ አቀደው ዓላማ ይደርስ ዘንድ እንዲጣጣር የታዘዘበት፣ በግንባታ ሙያው ሊተጋ የተሳለ ፍጡር ነው:: ዕድሜ ልኩን ሳያቋርጥ መንገድ ይሠራል፤ የትም ይሁን አድራሽ መንገድ::

ይህን መንገድ እንዲሰራ ስለታዘዘበትም ብቻ አንዳንዴ መሥመሩን ለቆ ይባክናል:: እንደየዋሁ የምግባር ሰው ሁሉን እንዳመጣጡ በመቀበል ፋንታ፣ አልፎ አልፎ ይጠይቃል፣ ያሰላስላል:: ይህ መንገድ የትም ቢሆን ወሳጅ መሆኑን ቢያውቅም፣ "ዋናው ነገር መድረሻው ይሆን ወይስ የመንገዱ አድራሽነት? እያለ በሀሳቡ ያውጠነጥናል::

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰው መፍጠርና መንገድ መስራት ይወዳል:: ይህ አያጠያይቅም:: ታዲያ ለምንድነው ማፍረስና ማተረማመስንም እጅግ አድርጎ የሚወደው? ይህን ይመልሱልኝ:: ምናልባት ሰው ለጥፋትና ለትርምስ የሚታክተው እቅዱን አሳክቶ፣ የሚገነባውን ሕንፃ ማጠናቀቅ ፈርቶ ይሆን? የሚለፋበትን ሕንፃ የሚያፈቅረው እንዲሁ ከሩቁ ብቻ ቢሆንስ? ግንባታውን ብቻ ወዶ አጠናቆ በውስጡ መኖሩን ግን ባይፈልግስ?

ጉንዳኖች ግንባታ የጀመሩት በኩይሳ ነው:: የሚጨርሱትም በዚሁ ይሆናል:: ይህ ታዲያ የታማኝነታቸውና የቋሚነታቸው ምሥክር ነው:: ሰው ግን ወፈፌ ነው:: ስንጠረዥ ተጫዋች ይመስል ከፍፃሚው ሂደቱ ያስደስተዋል:: ሰው በምድር ላይ ሊያየው የሚወደው ፍሬ የዚህን ለፍፃሜ የሚያደርስ ሂደትን መቀጠል ብቻ ይመስለኛል አዎ፣ የሂደቱን መቀጠል፣ " ሁለት ጊዜ ሁለት አራት ነው " ከማለት ሌላ ምሥጢር ያልያዘው ፍፃሜውን ሳይሆን፣ የሂደቶች እናት የሆነችውን ሕይወትን ብቻስ ከሆነ ሰው የሚሻው? ሁለት ጊዜ ሁለት ደግሞ ሕይወት አይደለም፣ የሞት መጀመሪያ እንጂ::

ሆኖም ግን ሁለት ጊዜ ሁለት አራት ነው የሚለውን ነገር ሰው ዘወትር እንደፈራው ነው:: እኔም እፈራዋለሁ:: የሰው ስራው ይህን " ሁለት ጊዜ ሁለት አራት ነው " ለማግኘት መጫር እስከሆነ ድረስ ውቅያኖስን ሰንጥቆ ይጓዛል፣ ሕይወቱን ለዚህ ዓላማ ይሰዋል:: ማግኘቱን ግን ይፈራል:: ለምን ቢሉ፣ ማግኘቱ ፍለጋውን እንደሚያቆምበትና፣ የጥረትና የልፋቱን ፍፃሜ እንደሚያበስር ያውቀዋል:: ለፍቶአደሮች ስራቸውን ፈፅመው ደሞዛቸውን ሲቀበሉ፣ ከመሸታ ቤት ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደው ያርፉታል:: እዚያም የሳምንት ስራ አገኙ ማለት ነው:: ሰው ግን ወዴት ይሄዳል? ሁሉ ነገር ተሳክቶለት ያቀደውን በፈፀመ ቁጥር ሰው ሃፍረት የመሰለ ነገር

t.me/OLDBOOKSPDF

ይታይበታል። ወደግቡ ለመድረስ መታገል እጅጉን ይወዳል፤ ከግቡ መድረሱን ግን እምብዛም አይፈልገውም። ባጭሩ የሰው ተፈጥሮ አስቂኝ ነው። ፣ ሁለት ጊዜ ሁለት አራት ማለት ደግሞ አስቀያሚ ነገር ነው፤ የድፍረት ድፍረት። እጁን ወገቡ ላይ አድርጎ ጢቅ እያለ ከመንገድ የሚጋረጥ ይሉኝታ ቢስ ባለጌ። ሁለት ጊዜ ሁለት አራት ነው ማለት መልካም እንኳን ቢሆንም፣ ፍላጎታችን ውዳሴ ማዜም ከሆነ፣ ሁለት ጊዜ ሁለት አምስት ነው ማለትም አንዳንዴ ውብ ነገር ናት።

ለሰው የሚበጀው ደህነኛውና ገንቢው ነገር ብቻ ነው ብለው አጥብቀው በአርምሞ የሚለፍፉትስ ለምንድን ነው? አእምሮ ይበጃል ብሎ በሚገምተው ነገር ሊሳሳት አይችልም? ሰው የሚወደው ደኅንነትን ብቻ ሳይሆን መከራን ጭምር ቢሆንስ? ስቃይም እንደደህነት ይበጃል ብሎ ቢያስብስ? አንዳንዴ እኮ ሰው መከራን እጅግ ይወደዋል። ይህን ስላልኩዎ የዓለምን ታሪክ መመርመር አያስፈልግዎትም። በእርግጥ ሰው ከሆኑና ከኑሮ ፅዋ ከቀመሱ፣ ራስዎን ይጠይቁት። እንደኔ ከሆነ ግን ደህንነትን ብቻ መውደድን ከነውረኝነት እቆጥረዋለሁ። ቢበጅም ቢከፋም አልፎ አልፎ ሆን ብሎ መስታወት ማድቀቅና የክት ለብሶ ከጭቃ መርመጥመጥም ድንቅ ነገር ነው።

በውነቱ ለመከራ ጠበቃነት አልቆምም፤ የደኅንነትም አፈቀላጤ አይደለሁም፣ የምቆምለት ነገር የራሴ ቅዕበታዊ ፈቃድና ፍላጎት፣ እሱንም ለማድረግ ያለኝን የግል መብት ነው። ሁሉ ነገር በስመረበት አገር ለምሣሌ መከራ ዝር አይልም። በእንከን አልባው የመስታወት ቤት ስቃይ ጭራሹን አይታሰብም። ስቃይ ማለት ጥርጣሬ ነው፤ አፍራሽ ኃይል። ጥርጣሬና እንከን አልባነት ደግሞ አብረው አይኖሩም። ሰው ግን ስቃይን እርግፍ አድርጎ አይተውም። ስቃይን፣ ውድመትንና ምሥቅልቅልን። ምክንያቱም መከራ የንቃተ


t.me/OLDBOOKSPDF

ከቤቴ ስሆን ዋና ሥራዬ ማንበብ ነበር:: በውስጤ ይተራመስ የነበረውን ነገር ሁሉ በውጫዊ ስሜት አምቄ አስቀምጥ ብዬ ጊት ማታ እያነበብኩ ነበር ጊዜዬን የማሳልፈው:: ማንበብ በርግጥ ጠቅሞኛል:: ረብሸኝ፣ አሰቃየኝ፣ አስደሰተኝ:: አልፎ አልፎ ግን ቋቅ ይለኝ ነበር:: ያኔ ታዲያ ወጣ ብዬ መንቀሳቀስ ያምረኝና ከአልባሌ ርክሰት ገብቼ እዳክራለሁ:: በዕረፍት አልባነትና በሡላም ማጣት በሽታዬ ምክንያት ያማረኝን ነገር ካላደረግኩት እፎይ አላልም:: ማልቀስ፣ መንሰቅሰቅ፣ በሲቃ መጠማረር ልምዴ ነበር:: ከማንበብ በቀር የማመልጥበት ዋሻ አልነበረኝም:: ከዚህ በቀር ጉዳይ የምለው ነገር በአካባቢዬ አልነበረም:: ከውስጤ የታመቀው ደስታቢስነት ገንፍሎ ሲፈስ ነፍሴ አጉል ነገር አጥብቃ ትናፍቃለች:: መጥፎ መንገድ፣ ዋልጌነት:: ይህን የምነግርዎ ድርጊቶቼን በምክንያት ለማንተራስ ብዬ አይደለም:: አዬ፣ እንደገና ዋሸሁ:: ይህን ሁሉ የነገርኩዎ የምክንያቴን ጭብጥነት አሳይ ብዬ ነው:: አልዋሽም ብዬ ቃል ስለገባሁ እስቲ ይቺ ማስታወሻ ትሁነኝ::

ብቻዬን በውድቅት ሌሊት ተንሿክኬ ሂጄ ቆሻሻ ነገር አደርግና ተላብሼው የምመለሠው የሃፍረት ማቅ ከገላዬ ተጣብቆ ይቀጣኛል፤ አንዳንዴም ለጆሮ የሚቀፍ ነገር ከአንደቤቴ ልውጣ እያለ ይታገለኛል:: ይህን ሳደርግ ሳለሁ ነፍሴ በሥርቻ ህይወቴ ርግማን ነቅዛ ነበር:: መታየትና የሚያውቀኝን ሰው ማግኘት ስለምፈራ፣ ብርሃን የናፈቃቸው ሰዋራ ቦታዎችን ነበር የማዘወትረው::

አንድ ቀን በጨለማ በመሸታ ቤት ደጃፍ ሳልፍ ሰዎች ከከረምቦላ ጠረጴዛ ዙሪያ ተኮልኩለው ሲጨቃጨቁ ቆዩና ከመካከላቸው አንዱን ገፍተው በመስኮት ሲያስወጡት አየሁ:: ሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ በድርጊታቸው እጠየፍ ነበር:: ያኔ ግን የተገፋውን ሰው መሆን ተመኘሁና በደረሰበት ውርደት ቀንቼ ወደ ከረምቦላው


t.me/OLDBOOKSPDF

እስከዚያ ድረስ ግን የዶሮ ቤትን ከቪላ አልቆጠረውም:: ይህ የመስታወት ቤት ሕንፃ የሃሳብ ውላጅ ቢሆንም እንኳን፣ ከድንቁርናዬ የመጣ፣ የተፈጥሮ ህግ የማይፈቅደው የህልም እንጀራ:: ታዲያ ተፈጥሮ ባይፈቅደው እኔን ምን ሲገደኝ? የምኖረው በምኞት ውስጥ ሆነ፣ ወይም የህንፃው ማኖር ምኞቴ እስከኖረ ድረስ፣ እኔ ምን ቸገረኝ?

አሁንም እየሳቁ ነው? እንዳሻዎ፣ ይሳቁ:: ቢሳለቁብኝም እየራበኝ ጠግቤያለሁ አልልም:: በእርግጥ ስለኖረና የተፈጥሮ ህግ ስላነገሰው ብቻ ለፍፃሜ አልባ ባዶነትና ለተልካሻ ስምምነት እጄን አልሰጥም:: ቪላ እያለ፣ የሺህ ዓመት ውል የተፈረመበት ዛኒጋባ የፍላጎቴ ቁንጮ አይሆንም:: ፍላጎቶቼን ደምስሰው፣ ክቡር መመሪያዎቼን ነቅለው፣ የተሻለ ነገር ሲያሳዩኝ ያኔ እከተልዎታለሁ:: ላንተ ግን ግድ ይሠጠዋል ካሉኝም፣ እኔም እርስዎን ጉዳይ አልልዎትም:: የምናወጋው ከልብ ነውና ትኩረትዎን ሊሰጡኝ ካልፈቀዱ እኔም እርስዎን ደጅ አልጠናም:: ወደ ስርቻዬ እዘገማለሁ::

ግን በሕይወት እስካለሁና፣ መሻቴ እስካላከተመ ድረስ፣ ይህን ለመሠለ ቤት አንዲት እንኳን ጡብ ባበረክት ክንዴ ሽባ ይሁን! የመስታወቱን ቤት ሕንፃ የናቅኩበት ምክንያት ሰው በውስጡ ምላሱን ማውጣት ስለማይችል በመሆኑ ብዙ አይደነቁ:: ያንን ያልኩትም ምላስ በማውጣት ፍቅር ተለክፌ አይምሠልዎ:: የነገሮች ሁኔታ የምላስ ማውጣት ፍላጎቴን እንዲያጠፋ ሆኖ ቢገኝ ኖሮ፣ ከደስታዬ ብዛት በፈቃዴ ምላሴን ባስቆረጥኩ ነበር:: መሻቴና ምኞቴ ለምን ተፈጠሩ? በዚህ ተፈጥሮዬ ምክንያት ማንነቴ ከንቱ ነው ብዬ እንዳስብ ልገደድ ታቅዶ ይሆን? አይመስለኝም::

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን ግን ይወቁ:: እኛ የስርቻ ሰዎች በወጉ ተጠፍረን መያዝ እንዳለብን ተረድቻለሁ:: የኔ አይነቱ ሰው አንዲት ቃል ሳይተነፍስ ለዓርባ ዓመታት ጉድባው ውስጥ ተወትፎ ይኖርና አንድ ቀን ወጣ ብሎ አፉን ከከፈተ ማቆሚያ የለውም::

- 9 -

በመጨረሻም፣ ድንቁ ነገር ምንም አለማድረግ ነው:: ሲያውቁ ከምግባር መታቀብ! ስለዚህም እሰዬው ለስርቻዬ! ምንም እንኳን በደህነኛው ሰው እጅጉን ብቀናም፣ በየዕለቱ ባየሁት ቁጥር እሱን መሆን አልመኝም ( ያም ሆነ በርሱ መቅናቴን አላቆምም):: እውነቴን ነው፣ የስርቻ ብቸኝነት በምንም መንገድ ይሻላል:: አዩ፣ እዚያ ሌላው ቢቀር . . . አሁንም እየዋሸሁ ነው:: ምክንያቱም፣ መልካሙ ነገር፣ የምመኘው፣ ሳገኘው ጥሬ ግሬ ያልተሳካልኝ ስርቻው ሳይሆን ጭራሹን ሌላ ነገር ነው:: ሥርቻዬ ሲፈልግ ገደል ይግባ!

ልክ አሁን በጣፍኳት አንዲት ቃል እንኳን እኔው ራሴ እምነት ቢኖረኝ ምንኛ ጥሩ ነበር:: የዘበዘብኩትን ባምንበትም ቅሉ በሌላ በኩል ደግሞ እንዲሁ የምቀላምድ ይመስለኛል:: " ታዲያ ይህን ሁሉ ለምን ቀባጠርክ?" ብለው ይጠይቁኛል:: እስቲ እግዚአብሔር ያሳይዎ! ምንም እንዳይሰሩ ቆልፈ.ብዎት ከአርባ ዓመታት በኋላ ምን እንደደረሱ ለማየት ከጉድባዎ ብመጣ ከኔ የሚለዩ ይመስልዎታል?

እርስዎም " ይህ ወራዳ፣ ርካሽ ነገር ነው" ይሉኛል በንቀት ራስዎን እየነቀነቁ:: " ነፍስህ በመኖር ጥማት ተፈረካክሳ ሳለች፣



t.me/OLDBOOKSPDF

የሕይወትን ችግር በሎጂክ ድራድር ትተበትበዋለህ:: ቦቅቧቃነትህን በዓይናውጣነት እንቀልባ አዝለህ፣ የባጥ የቆጡን ቢመቀባጠርህ ትኩራራለህ:: እፍረተቢስ ነገር ታወራና፣ ወዲያው በፍርሃትና በሰበብ ትከልሰዋለህ:: የምፈራው የለም እያልክ፣ ዞር ብለህ ትለማመጣለህ፣ በሡቆቃ ጥርሴን አነፋጫለሁ ብለኸን፣ ኋላ ደግሞ እየቀለድክ ሳቁልኝ ትለናለህ:: ቀልዶችህ ጣዕመቢስ መሆናቸውን ስታውቅ፣ በስንፅሁፍ ዋጋቸው ትመፃደቃለህ:: መከራ ደርሶብህ ብታውቅም እንኳን ለስቃይህ ቅንጣት እንኳን ዋጋ አትሰጠውም:: ከምትቀባጥረው አንዳንዱ እውነት ቢሆንም፣ ይሉኝታ ቢስነትህ መጠን የለውም:: ከግብዝነትህ የተነሳ ሐቅህን አደባባይ አውጥተህ ታረክሰዋለህ:: በርግጥ ማለት የምትሻው ነገር አለ፤ እቅጩን እንዳትናገር ግን ፍርሃት ጠፍሮ ይዞሃል፤ ለመናገር የሚያበቃህ ድፍረት አጥሮሃል:: የፈሪ ባለጌ ነህ:: በአእምሮ ንቃትህ እየተኩራራህ ሳለህ ትወላውላለህ:: ምክንያቱም አእምሮህ ብሩክ ቢሆንም እንኳን፣ ልብህ በልክስክስነት ዕልመት ተወርሷል:: ንፁህ ልቦና በሌለበት ደግሞ ምሉዕ ንቃተኀሊና ሊኖር አይችልም:: ወራዳነትህ! አትርሱኝ ባይነትህ! የመቀላመድህ ገደብአጤነት!"

ይህን ሁሉ ካንደበትም ያስቀመጥኩት ራሴ ነኝ:: ይህም የፈለቀው ከስርቻ ነው:: የተሻለን ነገር አእምሮዬ ስለማይቀበል ይህን አለምኩ:: ስለዚህ አነጋገሬ ቢራቀቅና ሁሉን በልቤ አጥንቼ ብይዘው አይግረምዎት::

ይህን ሁሉ ለህትመት አብቅቼ እንዲያነቡልኝ የምፈቅድ ይመስልዎታል? አይሳሳቱ:: ለምንድነው ደግሞ አንባቢዬ የሆኑ ይመስል እርስዎ እያልኩኝ የማወራው? ቀጥዬ የምጀምረው አይነት ጉድ ለህትመት አይገባም፣ ለአንባቢያን አይሆንም:: ያን የማደርግበትም ወኔው የለኝም::

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲህ ነው ነገሩ:- ሰው ሁሉ ከባልንጀራው በቀር ለሌላ የማይገልጠው ነገር ሞልቷል:: ሌላ ደግሞ ራሱም ቢሆን በድብቅ ተንሿክኮ የሚመለከተው ድብቅ ምሥጢር አለው:: በመጨረሻም፣ መልካም ሰው የምንለው ሁሉ ከራሱ እንኳን የሠወረው ብዙ ቋጠሮ ተሸክሟል:: እንዲያውም የሰው ጨዋነቱ በላቀ መጠን ይህን መሣይ ከራሱ እንኳን የሰወራቸው ጉዶች በዚያው ልክ በዝተው ይርመሠመሣሉ:: ያም ሆነ ይህ፣ እስካሁን በስጋት ሸፋፍኜ ያቆየኋቸውን ጀብዱዎቼን ለማስታወስ በቅርቡ ድፍረት አግኝቻለሁ:: ግን ልክ አሁን ገበናየን ሳስታውሰው ብቻ ሳይሆን ከትቤ ላስቀምጠው ስቆርጥ፣ ሰው ለራሱ መዋሸቱን ትቶ ሳይፈራ ከእውነት ፊት ይችል እንደሆነ ማየት ፈለግኩ:: ማን ነበር እውነተኛ የግል ሕይወት ታሪክ ማግኘት አስቸጋሪ ነው ያለው?

እስማማለሁ:: አንዳንድ ጊዜ፣ ከግብዝነት የተነሳ፣ ሰው ራሱን እንደሚያጎድፍና ያልሰራውን ወንጀል ራሱ ላይ እንደሚለጥፍ አውቃለሁ:: ይህን መሳይ ግብዝነት መኖሩን እገነዘባለሁ:: ያ ታዲያ ጉዳቸውን ስለሚለፍፉ ሰዎች ሲሆን፣ እኔ ግን የምፅፈው ለራሴ ብቻ ነው:: ለአንባቢያን የምፅፍ ያስመሰልኩት ስለሚመቸኝ ነው:: አንባቢ ሊኖረኝ አይችልም:: ያንን ቀድሜ ተናግሬያለሁ:: የምፅፈውንም አርማለሁ ብዬ ራሴን አልወስንም:: ምንም አይነት ስርዓትና ቅደም ተከተል አልጠብቅም:: ትዝ ያለኝን ሁሉ እከትባለሁ:: ልክ አሁን ለምሣሌ አንዱ ተነስቶ « በእርግጥ አንባቢ እንደማይኖርህ ካወቅክ፣ የአፃፃፍህን ሁኔታ ወረቀት ላይ ለምን ታሠፍራለህ? ሥርዓት አልጠብቅም፣ ትዝ ያለኝን ሁሉ እፅፋለሁ፣ እያልክ ለምን ትፎክራለህ? ይህ ሁሉ ለምን አስፈለገ?» ብሎ ቢጠይቀኝ፣ « እንዲያው እንዲሁ » ስል እመልስለታለሁ::

ለነገሩማ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጥልቅ የሥነ ልቡናዊ ጉዳይ አለ:: የጥያቄው መልስ ምናልባት ፈሪነቴ ይሆናል:: ወይም ደግሞ


t.me/OLDBOOKSPDF

በሃሣቤ በፈጠርኳቸው አንባቢዎች ትችትና ትዝብት ፍራቻ ምክንያት አፃፃፌን በወጉ እንዳደርገው:: መፃፉንስ ለምን ፈለግኩት? ለአንባቢያን ካላቀድኩት በቀር ወረቀት ላይ በማስፈር ፋንታ ቁጭ ብዬ በአእምሮዬ ሁሉን ነገር እያውጠነጠንኩ ብመላለስበት አይበቃም ነበር?

ልክ ነው:: ይሁንና ግን ሃሣብ ወረቀት ላይ ሲቀመጥ ከበሬታ ይኖረዋል:: ወረቀት ላይ መሆን ያልቀዋል:: ራሴን አጥብቄ እመረምራለሁ፣ እፈርጃለሁ:: የሚያምረው እንዲያ ነው:: ከዚያም በላይ ሁሉን በመፃፌ እፎይታ አገኝ ይሆናል:: ለምሣሌ ዛሬ አንድ ትውስታ የጊዜን ጭጋግ ሰንጥቆ መጥቶ ነፍሴን ተጭኗታል:: በጧት ከአእምሮ ተጣብቆ የሙጥኝ እንደሚል ጆል ዜማ፣ ከትናንት ጀምሮ ተጠናውቶኛል:: ይህን የመሳሰሉ ብዙ ትውስታዎች አሉኝ:: አልፎ አልፎ ታዲያ እነኚህ ከተቀበሩበት አንዱ ፈትለክ ብሎ ወጥቶ ይሠፍርብኝና ያስጨንቀኛል:: ብዕሬው ቀለል የሚለኝ ይመስለኛል:: ለምን አልሞክረውም?

በመጨረሻም፣ ከመደበሬ ብዛት ምንም አላደርግም:: ስለዚህ መጫጫርን ከስራ እቆጥረዋለሁ:: ሥራ ሰውን ደግና ሐቀኛ ያደርገዋል ይሉ የለም? ሞክሮ ማየቱ አይከፋም::

አሁን ገለባ የመሰለ በረዶ ከሠማይ እንደፎረፎር ይረግፋል:: ትላንትም በረዶ ሲወርድ ነበር:: ከትላንት ወዲያም እንዲሁ:: ይህን አልለቅም ብሎ እረፍት የነሣኝን ነገር ያስታወሰኝም ምናልባት ይህ በረዶ ይሆናል:: ስለዚህ የሚቀጥለውን የበረዶ ወቅት ትረካ እንበለው::

ያኔ ዕድሜዬ ሃያ አራት ዓመት ነበር:: ሕይወቴ- ድንግዝግዝ፣ ቅጥ ያጣ፣ በብቸኝነት ቆፈን የተወረሰ:: ከሰው ጋር

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳልቀሳቀል መነጋገር እንኳን ትቼ እያደር ርቄ ወደ ጉድባዬ የገባሁበት ወቅት:: ከሥራ ቦታዬ በተቻለኝ መጠን ሰው ማግኘት ተውኩ:: በዚህም ምክንያት ለባልደረቦቼ እንዳስጠላኋቸው ይሠማኝ ነበር:: አንዳንዴም " ለምንድነው እኔ ብቻ የተጠላሁ አድርጌ የማስበው፣ ለምንድነው ሌሎች ራሳቸውን እንዳስቀያሚ የማይቆጥሩት?" እያልኩ እገረም ነበር:: ለምሳሌ አንድ አብሮኝ የሚሠራ ሰውዬ ፊቱ ተኾራኩሮ ማጅራት መች ስላስመሠለው ለዓይኔ ያስጠላኝ ነበር:: የሌላው ባልደረባዬ ያረጀ ልብስ ደግሞ እድፍ ደልቦበት ይከረፋል:: ታዲያ እነኚህ ሰዎች በልብሳቸው፣ በፊታቸውም ሆነ በማንነታቸው ሃፍረት ተሰምቷቸው አያውቅም፣ ሰው ይጠላናል ብለውም አያስቡም:: ለሰው አስቀየምን ብለው ቢያስቡ እንኳን ተቀያሚው አለቃቸው እስካልሆነ ድረስ ግድ አይሰጣቸውም::

ዛሬ ነገሩን ሳጤነው፣ ገደብ በሌለው ትዕቢትና ግብዝነቴ ምክንያት ከራሴ ከምጠብቀው የላቀ ስብዕና የተነሳ ለነበረኝ እንከን ሁሉ መልሴ ሃዘንና ራሴን መጥላት ሆኖ፤ ኋላም ይህንን የወደቀ የራስ ግምቴን ከሰው ያገኘሁት አድርጌ እንደቆጠርኩት አውቀዋለሁ:: ለምሣሌ መልኬን እጅግ እጠላው ነበር:: ፊቴ ላይን የሚያስከፋ፣ ማስጠሎ ስራ በሄድኩ ቁጥር ውዳቂነቴን እደብቅ ብዬ በተቻለኝ መጠን ያልነበረኝን ግርማ ሞገስ ተላብሼ እጀነን ነበር:: ምንም እንኳን ፊቴ ውብ ባይሆንም፣ ቢያንስ ሕይወት የሠፈነበት የብልህ ሰው ፊት ከመሰለ ይበቃል ብልም፣ ይህን ሳስብ እንኳን ታዲያ ፊቴ ውበትንም ሆነ ብልህነትን እንዳላጎናፀፈው ይገባኛል:: ሌላው ሁሉ ቀርቶ፣ ሰዎች ፊቴን የብልህ ፊት አድርገው ቢያዩልኝ ኖሮ ርጉም መምሠሉ ባልከፋኝ ነበር::

ባልደረቦቼን አንዱ እንኳን ሳይቀር እጠላቸው፣ እንቃቸውና እፈራቸው ነበር:: በል ሲለኝ ደግሞ ከኔ እጅጉን የተሻሉ አድርጌ

t.me/OLDBOOKSPDF

አያቸዋለሁ:: በእነዚያ ዓመታት ዓመሌ ቅጥ ያጣ፣ የሚሰማኝም ስሜት እንደ እስስት የሚለዋወጥ ነበር:: አንዴ ሰው እንቃለሁ፤ ኋላ ደግሞ ሁሉ ከእኔ በላይ የሆነ ይመስለኛል:: ስልጡን ጨዋ ሰው አልፎ አልፎ ራሱን ሳይቀጣና፣ የራስ ንቀቱ ከጥላቻ ድንበር ሳይደርስ ግብዝነቱ እውን አይሆንም:: ታዲያ እኔ ሌሎችን ብንቅም ሆነ የበላዬ አድርጌ ብመለከታቸውም፣ ከፊታቸው ስቆም ዓይኔን ከምድር ከመጣል አልዳንኩም:: « ዓይኖቼ በዚህ ወይስ በዚያኛው ሰው ዕይታ ይረቱ ይሆን? » እያልኩ ራሴን እፈትነውና፣ ሁልጊዜ የኔው ዓይኖች ቀድመው ይሰበራሉ:: ያም በሆነ ቁጥር ከእብደት የተጠጋ የደም ፍላት ከልቤ ውስጥ ይንተከተካል:: መቀለጃ መሆንን እንደሞት ከመፍራቴ ብዛት፣ በማደርገው ነገር ሁሉ ሠጥ ለጥ ያልኩ የወግና ልማድ ተገዢ ነበርኩ:: ነፍስና ስጋዬን ለደንብና ሥርዓት ባርነት ሰጥቼ፣ የወግ ዘለልነት ፍንጭ እንዳይታይብኝ የሞት ሞቴን ተጣጣርኩ::

ታዲያ በዚህ እንዴት ልፅና? እንደዘመናችን ስልጡን ሰው ብዙ አውቃለሁ:: የአካባቢዬ ሰዎች ደግሞ አእምሮ ድንግዝና እንደበግ መንጋ አንዱ ከሌላው የማይለዩት ናቸው:: በሥራ ቦታዬ ከነበሩት መሃል ከኔ በቀር ራሱን ፈሪና ተገዢ አድርጎ የሚያይ አንድም ሰው የነበረ አይመስለኝም:: ፈሪ፣ በጭንቀት-ጥበት የምኖር ሰው ነበርኩ:: ይህን ስነግርዎ ሃፍረት አይሰማኝም:: የዘመናችን ሥልጡንና ጨዋ ሰው ሁሉ ከፍርሃትና ከባርነት አያመልጥም:: አይጠራጠሩ:: ተፈጥሮው አይፈቅድለትም:: የጨዋ ሰው ሁሉ ባርነትና በቅቢ ቃነት ኋላ የመጣ እንግዳ ነገር ሳይሆን የነበረና የሚኖር ነው:: በደፋርነታቸው የሚመኩ አህዮችና አጫፋሪዎቻቸው ናቸው:: የነርሱም ድንፋታ ያ የማይቀር ግድግዳ እስከሚጋረጥባቸው ድረስ ነው:: ግን ለምን በእነርሱ ጊዜ እናባክናለን? ምን ሲፈይዱ?

t.me/OLDBOOKSPDF

ያኔ ያሰቃየኝ የነበረው ሌላ ነገር ማንም እንደኔ አለመሆኑና እኔም ማንንም አለመምሠሌ ነበር:: « እኔ አንድ እኔው ብቻ ነኝ፣ እነርሱ ግን ማንም ናቸው » እያልኩ ብዙ እጨነቅ ነበር:: የዚህ ምክንያቱ ምናልባት ልጅነቴ ይሆን?

አንዳንዴ ደግሞ ከተቃራኒ ሁኔታዎች እላተማለሁ:: ቢሮ መሂድ ያንገፈግፈኝና እየታመምኩ ከቤቴ እመለሳለሁ:: ከዚያም በድንገት የጥርጣሬና የግዴለሽነት ዛር ይሠፍርብኝና በትዕግሥት አልባነቴ፣ ሁሉን በመጠየፌ እየቀለድኩ ራሴን ከቅዠታምነት አቆጥራለሁ:: አብረውኝ ከሚሠሩት ጋር መነጋገር ያስጠላኝና፣ ኋላ ደግሞ በማልገታው የወሬ ፍቅር ተለክፌ ምላሴ እንደገመድ ይተረተራል:: ይባስ ብሎ ከነርሱ ጋር ጓደኝነት መጀመር ይቃጣኛል:: ያላንዳች መንሥኤ መጠየፌ እንደጤዛ ይረግፋል:: ማን ያውቃል፣ ምናልባትም ያ ሁሉ ንቀቴና መጠየፌ ከውስጤ የፈለቀ የግል ጠባይ ሳይሆን ከመፅሃፍ የለቀምኩት ሳይሆን አይቀርም:: ይህን አሁን እንኳን በውል አላውቀውም:: እንዲማ ጭራሹን ከባልደረቦቼ ጋር ቂጥ ገጥሜ ከቤታቸው እየሄድኩ ካርታ መጫዎት፣ አረቄ መጠ ጣትና የቢሮ አሉባልታ መቋረስ ጀምሬ ነበር:: እስቲ ይህ በዚህ ይቆየን::

እኛ ሩሲያዎች ስንባል የጀርመኖች፣ በተለይም ደግሞ ምንም የማያውካቸው የፈረንሳውያን የመጠቀ ምድር ለቀቅነት በሽታ የለብንም:: ለምሣሌ ፈረንሳዊያን መሬት ከእግራቸው ስር ብትሰነጠቅ፣ ወይም ሕዝብ ቢተላለቅ ሽብር አይነካቸውም:: እንዲያው ለይምሠል እንኳን:: ነፍስና ስጋቸው እስኪለያዩ ድረስ በርጋታ እያዜሙ ይጠብቃሉ:: ምክንያቱም ቂሎች ናቸውና:: የኛዋ አገር ሩሲያ ግን ቂል አልበቀለባትም:: እንደጀርመንና ፈረንሳይ ካሉ አገሮች የሚለየን አንዱ ነገር ይህ ነው::

t.me/OLDBOOKSPDF

የእኛ ሮማንቲክ ሁሉን የተገነዘበ፣ ነገሮችን ከሌሎች ይበልጥ ለይቶ የሚያመዛዝን ነው:: ራሱን ለምንምና ለማንም የማይሠጥ ሆኖ ሳለ አንዳችም ነገር የማይንቅ፤ በምንም የማይጨበጥ፣ ከሁሉ የሚስማማ፣ የመንግሥት ችሮታና ድጎማ የመሳሰሉ ጠቃሚ ነገሮችን ከማሣደድ ወደ ኋላ የማይል ብልጣብጥልጥ ነው:: ሆኖም ግን እስኪሞት ድረስ የውቡንና የታላቁን ነገር ራዕዩን ከልቡ አይፍቅም:: በዚህ ሁሉ መሃልም ራሱን መንከባከብ ቸል አይልም:: እንደ ክቡር ድንጋይ በጥጥና በሱፍ ተጠቅልሎ ለመኖር ሲል የማይበጥሰው ቅጠል የለም::

ለምሣሌ ሥራዬን እጅግ እንቀው ነበር:: ኤጭ! ብዬ ተፍቼበት እንዳልሄድ ደግሞ የምከፈልበት ማደሪያዬ ሆነብኝ:: ያሻኝን ባስብም እንኳን ጨክኜ ልተፋበት አልቻልኩም:: ሮማንቲክ የምንለው ሰው ሌላ ዕድል ሳይኖረው ስራው ላይ ከሚተፋ አእምሮውን ቢስት ይቀለዋል:: አእምሮውን ስቶም ወደ ዕብድ ሆስፒታል ካልወሰዱት በቀር ከስራው በጅ ብሎ አይፈነቀልም:: ይህ ስሜት የነካካቸው ብዙዎች አያብዱም:: እንዲያውም ጊዜ በገፉ ቁጥር በያዙት መንገድ ከሹመት ወደ ሹመት ይተላለፋሉ:: ሾላካነታቸውና ጥበባቸው ይገርማል:: ልባቸው የተቃራኒ ስሜቶች ጎጆ ናት:: የቱንም ያህል ቢረክሱ እንኳን የእምነት ማተባቸውን አይበጥሱም:: ለዚህ እምነታቸው አንዲት ድንጋይ ባይሸከሙና፣ የምላጮችና የሌቦች ቁንጮ ቢሆኑ .እንኳን በልባቸው የከበሩና ለእምነታቸው በመቆርቆር የሚያነቡ ናቸው::

ቀድሜ ወደ ጀመርኩት ልመለስና:- ከሥራ ጓደኞቼ ጋር በቅፅበት ያጠፍኩት ጓደኝነት ብዙም አልቆየም:: ወዲያው ተጣላኋቸውና እርግፍ አድርጌ የተውኳቸው ይመስል ሰላምታ እንኳን ነፈግኳቸው:: ይህ የሆነው አንዴ ብቻ ነው:: ሌላውን ጊዜ ግን ብቸኛ ነበርኩ::

t.me/OLDBOOKSPDF

ከቤቴ ስሆን ዋና ሥራዬ ማንበብ ነበር:: በውስጤ ይተራመስ የነበረውን ነገር ሁሉ በውጫዊ ስሜት አምቄ አስቀምጥ ብዬ ጧት ማታ እያነበብኩ ነበር ጊዜዬን የማሳልፈው:: ማንበብ በርግጥ ጠቅሞኛል:: ረብሾኝ፣ አስቃየኝ፣ አስደስተኝ:: አልፎ አልፎ ግን ቋቅ ይለኝ ነበር:: ያኔ ታዲያ ወጣ ብዬ መንቀሳቀስ ያምረኝና ከአልባሌ ርክሰት ገብቼ እዳክራለሁ:: በዕረፍት አልባነትና በሠላም ማጣት በሽታዬ ምክንያት ያማረኝን ነገር ካላደረግኩት እፎይ አልልም:: ማልቀስ፣ መንሰቅሰቅ፣ በሲቃ መጠማረር ልምዴ ነበር:: ከማንበብ በቀር የማመልጥበት ዋሻ አልነበረኝም:: ከዚህ በቀር ጉዳይ የምለው ነገር በአካባቢዬ አልነበረም:: ከውስጤ የታመቀው ደስታቢስነት ገንፍሎ ሲፈስ ነፍሴ አጉል ነገር አጥብቃ ትናፍቃለች:: መጥፎ መንገድ፣ ዋልጌነት:: ይህን የምነግርዎ ድርጊቶቼን በምክንያት ለማንተራስ ብዬ አይደለም:: አዩ፣ እንደገና ዋሸሁ:: ይህን ሁሉ የነገርኩዎ የምክንያቴን ጭብጥነት አሳይ ብዬ ነው:: አልዋሽም ብዬ ቃል ስለገባሁ እስቲ ይቺ ማስታወሻ ትሁነኝ::

ብቻዬን በውድቅት ሌሊት ተንሿክኬ ሄጄ ቆሻሻ ነገር አደርግና ተሳብሼው የምመለሠው የሃፍረት ማቅ ከገላዬ ተጣብቆ ይቀጣኛል፤ አንዳንዴም ለጆሮ የሚቀፍ ነገር ከአንደቤቴ ልውጣ እያለ ይታገለኛል:: ይህን ሳደርግ ሳለሁ ነፍሴ በሥርቻ ህይወቴ ርግማን ነቅዛ ነበር:: መታየትና የሚያውቀኝን ሰው ማግኘት ስለምፈራ፣ ብርሃን የናፈቃቸው ስዋራ ቦታዎችን ነበር የማዘወትረው::

አንድ ቀን በጨለማ በመሸታ ቤት ደጃፍ ሳልፍ ሰዎች ከከረምቦላ ጠረጴዛ ዙሪያ ተኮልኩለው ሲጨቃጨቁ ቆዩና ከመካከላቸው አንዱን ገፍተው በመስኮት ሲያስወጡት አየሁ:: ሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ በድርጊታቸው እጠየፍ ነበር:: ያኔ ግን የተገፋውን ሰው መሆን ተመኘሁና በደረሰበት ውርደት ቀንቼ ወደ ከረምቦላው


t.me/OLDBOOKSPDF

ቤት ገባሁ፣ ምናልባት እድሌ ቀንቶ፣ ጠብ ጭሬ ፡በመስኮት አምዘግዝገው ቢጥሉኝ ብዬ።

አልሰከርኩም ነበር። አዩ ግን መድረሻቢስነት ሰውን ከምን እንደሚያደርሰው? ለነገሩ ምንም አልፈጠርኩም። ከመስኮቱ ዘልዬ በእግሬ መቆም እንደማይቻለኝ አውቄ፣ ፈራ ተባ ስል፣ ከሰዎቹ መሃል አንዱ መቶ አለቃ ቢጤ ዋጋዬን ሰጠኝ። እንደገባሁ ከከረምቦላው ጠረጴዛ አጠገብ ቆሜ መንገድ ስለዘጋሁበት፣ ምንም ሳይናገር ትከሻዎቼን ጨምድዶ ቆሜ ከነበርኩበት ቦታ ፈቀቅ አድርጎ መንገዱን አስለቀቀኝና መፈጠሬንም ልብ ያለ ሳያስመስል ጨዋታውን ቀጠለ። በቡጢ ቢዘልጠኝ እንኳን ይቅር ባልኩት ነበር፣ እንደግዑዝ ዕቃ ገለል አድርጎኝ ያላንዳች ቃል አልፎኝ ከሚሄድ።

በዚያ ወቅት ከሰውዬው ጋር በወጉ፣ በሥርዓቱ ትግል ልገጥመው እንድችል ምንም ለማድረግ ዝግጁ ነበርኩ። በርግጥ እሱ ጠርብ የሚያህል ግዙፍ ነበር፣ እኔ አጭርና አቅመቢስ። በመገፋቴ አሻፈረኝ ብል ኖሮ በመስኮት ይወረውሩኝና የተመኘሁት ይደርስልኝ ነበር። ግን ሁሉም ይቅር ብዬ ሾልኬ ወጣሁ፣ ውስጤ በንዴት እየበገነ።

ከዚያ ወጥቼ ወደቤቴ ተመለስኩ። ግራ ገብቶኝ፣ የምሆነውን አጥቼ። በማግስቱ ሲመሻሽ ተመልሼ በስውር፣ በፍርሃትና ማመንታት ጉልበቴ እየራደ፣ ዓይኖቼ ዕንባ ያረገዙ እስኪመስለኝ ሃዘን ተጭኖኝ፣ ከውርደት ቀየ መልከስከስ ቀጠልኩ። ሆኖም ግን ያ ወታደር፣ የግንድ ቁራጭ የሆንኩ ይመስል አንስቶ ገለል ሲያደርገኝ አንገቴን ደፍቼ የወጣሁት ከፍርሃት አይመስለኝም። የምግባር ሰው ባልሆንም እንኳን በልቤ ፈሪ አይደለሁም። አይሣቁብኝ። ይህን አስረዳዎታለሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ያ መቶ አለቃ የሽጉጥ ፍልሚያ የሚደፍር ሰው ቢሆን ኖሮ እንዴት ሸጋ ነበር:: እሱ ግን በከረምቦላ እንጨት መጣለዝና ፍርድ ቤት እየሮጡ መካሠሥ የሚወዱት አይነት ነው:: የሱ ብጤዎች ፍልሚያ አይሆናቸውም:: ቢደፍሩትም እንኳን ከኔ ብጤ ተራ ፀሐፊ ጋር መጋጠም ዝቅ የሚያደርጋቸው ይመስላቸዋል:: ለነርሱ፣ ሽጉጥ ተማዞ መፋለም የማይታሰብ የከሃዲዎች ድርጊት ነው::

ሹልክ ብዬ የወጣሁት በፍርሃት ሳይሆን በድንበር ዘለል ግብዝነቴ ነው:: ያስፈራኝ የወታደሩ ግዙፍነት፣ በዚያ ጉልበቱ ቢነርተኝ የሚሰማኝ ሕመም ታስቦኝ፣ ወይም በመስኮት የመወርወሩ ሃሳብ ዘግንኖኝ አይደለም:: ለርግጫና ለጡጫው ሰውነቴ ሳይርበተበት፣ የሰው መሣቂያ መሆንን ብቻ ነበር የፈራሁት:: ከባለጌው ቁጥር ያኘ ጀምሮ እስከዚያ ፊቱ ብጉር የተዘራበት፣ ጨርቁ ላይ የደለበው ዕድፍ የኮቱን አንገት ጥቁር አሳ ያስመሠለው የመሸታ ቤት አውደልዳይ፣ በረቀቀ አነጋገር ለወታደሩ ስመልስለት ቢሰሙኝ፣ ሃሳቤን ሳይረዱ መሣቂያና መሣለቂያ ያደርጉኛል ብዬ ሰግቼ ነው::

ከጠቀለለኝ ምድርለቀቅ ዝባዝንኬ ወጣ ብዬ ጭብጡን ነገር ስመለከተው፣ ያ ወታደር ወዲያውኑ በብስጭት ወግሮኝ ዞር በማለት ፊንታ በጉልበቱ እየነረተ በከረምቦላው ጠረጴዛ ዙሪያ ሲያንደፋድፈኝ፣ ዙሪያ ተመልካቾቹ አንጀታቸው እስቲቆስል በሣቅ እንደሚፈርሱ በግልፅ አወቅሁት:: ከዚያም ሲበቃው በመስኮት ወርውሮኝ ያርፋል::

የኔ ነገር እንደሚያውቁት በዚህ አያልቅም:: ከዚያ በኋላ ይህን መቶ አለቃ በመንገድ ባየሁት ቁጥር ልብ እያልኩ አስተውለው ጀመር:: እሱ ግን ምኔንም ያስታወሰ አይመስለኝም:: የጥላቻ መርዝ ባረገዙ ዓይኖቼ እያየሁት ጥቂት ዓመታት አለፉ:: ዓመታት ባለፉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቁጥርም ለርሱ የነበረኝ ጥላቻ እየናረ ሄደ:: ልበቀለው ፈለግኩ:: በቅድሚያ በድብቅ ስለእሱ እየጠያየቅኩ ማንነቱን ማሠባሠብ ጀመርኩ:: ሰው ባለማወቄ ምክንያት ይህ ለኔ ቀላል ነገር አልነበረም:: አንድ ቀን እንዲሁ ከእግሩ ያቆራኙኝ ይመስል ከኋላው ስከተለው ሳለሁ፣ የሆነ ሰው ሲጠራው ሰምቼ ስሙን ለቂም አደረግሁ:: ሌላ ጊዜ ደግሞ እስከቤቱ ድረስ ተከትዬው፣ ለአገልጋዩ ትንሽ ጉርሻ ሰጠሁና የወታደሩ ቤት ስንተኛው ፎቅ ላይ እንደሆነ፣ ከማን ጋር እንደሚኖርና፣ ባጭሩ ከአገልጋይ ሊገኝ የሚችለውን ሁሉ ሰበሰብኩ:: በማግስቱ ከእንቅልፌ ስነቃ የዚህን ወታደር ምንነት የሚገልፅ ነገር ፅፌ ለጋዜጣ በመላክ ላጋልጠው እንደምችል ሃሣብ በድንገት አእምሮዬ ውስጥ ብልጭ አለልኝና ብድግ ብዬ በደስታ የጠነሰስኩትን ፃፍኩት:: ሰውዬውን አጥላላሁት፣ አጎደፍኩት:: መጀመሪያ እጅግም ሥውር ያልሆነ፣ በቀላሉ ማንነቱን የሚጠቁም ሥም ሠጠሁት:: ኋላ ግን ነገሮችን አገናዝቤ ስሙን ለወጥኩና ለጎትመት ይበቃ ዘንድ ፅሁፉን ለዝነኛ ጋዜጣ ላኩት:: ያኔ ታዲያ እንዲህ ያለ የስም ማጉደፍ ፅሁፍ ገና አልተለመደም ነበርና ሳይታተምልኝ ቀረ:: በዚህም ተከፍቼ ነበር::

የከረቦላው ቤት ውርደቴ ትውስታ እንደእኩይ ነቀርሳ ቀናት ባለፉ ቁጥር እየከፋ ሄደና ባሰብኩት ቁጥር ትንፋሽ እስቲያጥረኝ ድረስ ንዴት ያቃጥለኝ ጀመር:: በመጨረሻም ይህን ጠላቴን ልፋለመው ወሰንኩና ግሩም የሆነች ደብዳቤ ፃፍኩ:: በደብዳቤዬ ላይ፣ ይቅርታ ካልጠየቀኝ ሽጉጥ መማዘዛችን እንደማይቀር ፍንጭ ሰጠሁ:: ደብዳቤውን የፃፍኩት ወታደሩ መልካሙንና የላቀውን ነገር ለይቶ ማየት ከቻለ ከኔ ዘንድ ሲከንፍ መጥቶ፣ አንገቴን አቅፎ፣ ጓደኛው እንድሆን እንዲጠይቀኝ ይገፋፋው ይሆናል ብዬ ነበር:: ያ ቢሆን ኖሮማ እንዴት ጥሩ ነበር! ምንኛ ያማረ ጓደኝነት በመሠረትንና ሕይወታችን እንዴት የቀና ባሆነ ነበር:: እሱ

t.me/OLDBOOKSPDF

በደረጃውና በስልጣኑ ሲያጥረኝ፣ እኔ ደግሞ በዕውቀቴና በስልጣኔዬ ከፍ አደርገው ነበር:: ሌላም ሌላም::

እግዚአብሄር ያሳይዎ! ከዘለፈኝ ሁለት ዓመታት ሆኗል:: ምንም እንኳን የደብዳቤዬ አፃፃፍ ያማረ ቢሆንም፣ የፍልሚያ ግብግቤዬ እጅግ የዘገየ ነበር:: ደብዳቤውን ባለመላኬ ታዲያ ዓይኖቼ እንባ እያቀረሩ ተመስገን እላለሁ:: ብልከው ኖሮ ምን እንደሚከተል ሳስበው ይዘገንነኛል::

ከዚያም ተሳካልኝና በድንገት፣ በቀላሉ ብቀላዬን መፈፀም ቻልኩ:: አንድ ቀን እንዲሁ እንደማለዳ ጀንበር ግሩም ሃሳብ አእምሮዬ ውስጥ ፍንትው አለ:: ያኔ አዘውትሬ ቅዳሜና እሁድ ከቀኑ አሥር ሰዓት ገደማ በኔቭስኪ ጎዳና ፀሐይዋ ባለችበት በኩል እግሬን አፍታታ ነበር:: እዚያ ከመሄድ የተረፈኝ በሠላም በመንሸራሸር ፋንታ ፍፃሜ በሌለው ሥቃይና ብስጭት መጠበስ ቢሆንም ቅሉ፣ የምፈልገው ይህንኑ ሆኖ አገኘሁት:: በዚያ ጎዳና ከሚንፈላሰሰው ሕዝብ መሐል ብቅ ጥልቅ እያልኩ ለሹ-ለከለክና ለሹማምንትና ለሐብታም ሴት ወይዘሮዎች መንገድ ስለቅ ቆይቼ ነበር የምመለሰው:: በነዚያ ሰዓታት ልቤ በሃዘን ፍላፃ ትሰነጠቅና፣ በጨርቃም ድኅነቴና ያለቦታዋ ጥልቅ ብላ ቱር ቱር በምትል ድውይ አካሌ ጀርባዬ እስከሚግል ድረስ አፍርና እከፋ ነበር:: በዚያ የመኳንንት፣ የመሣፍንትና የነአገሌ ፊት የኔ ስምየለሽ ተባይነት በውርደት ጅራፍ እየገረፈኝ ማለቂያ ከሌለው መከራ ከተተኝ:: ዝንብነቴን አወቅኩት:: ከሚተራመሱት ጌቶችና እመቤቶች ይበልጥ አእምሮዬ የላቀ፣ በችሎታዬም የበሰልኩና የነጠርኩ መሆኔን ባውቀውም ከሁሉ ፊት የምሸሽ፣ የተናቅኩ ዝንብ ነበርኩ:: ይህንን ተጋድሎ ለምን ተያያዝኩት? ከኔቭስኪ ጎዳና ምን ነበር ጉሮሮዬን እያነቀ የሚወስደኝ?

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚያ ጊዜ ያ ቀደም ብዬ የገለፅኩልዎት አይነት ሐሴት ይሰማኝ ጀምሮ ነበር:: በተለይማ ከወታደሩ ጋር ካጋጠመኝ ጉዳይ በኋላ ከኤቭስኪ መለየት ተሳነኝ:: መቶ አለቃውን ያገኘሁት ከዚሁ ጎዳና ነበር:: እዚሁ ነበር በወገ ሳደንቀውም የተቻለኝ:: እሱ ይህንን መንገድ የሚያዘወትረው በበዓላት ነበር:: ከጄኔራሎችና ከባለማረጎች ፊት በተጋረጠ ቁጥር በአክብሮት ቀድሞ ፈቀቅ በማለት ያሳልፋቸዋል:: የኔ ብጤዎችን ግን ከሰው ሳይቆጥራቸው ከፊቱ ምንም የሌለ ይመስል መሰስ ብሎ ሄዶ መንገድ እንዲለቅቁ ያስገድዳቸዋል:: ከእንደኔ አይነቱ በፊት ቢሞት ፍንክች አይልም:: ይህን ሲያደርግ እያየሁ እርር፣ ድብን ከማለቱ ሱስ ያዘኝ:: ውስጤ በንዴት እየበገነ ሲመጣብኝ መንገድ እለቃለሁ:: በአገር ጎዳና እንኳን ከራሴ እኩል ላየው አለመቻሌ ቆረቆረኝ:: « ሁልጊዜ ለምን አንተ ብቻ? አንዳንዴስ ለምንድነው እሱ መንገድ የማይለቀው? መንገድ ስለመልቀቅ የተፃፈ ሕግ ያለ ይመስል! ለምንድነው በእኩልነት የማይሆነው? እሱ ግማሽ መንገድ፣ አንተ ግማሽ መንገድ ለቃችሁ በእክብሮት የማትተላለፉት? » ይህ ግን በጭራሽ አልሆነም፣ ወታደሩም ገለል ማለቴን ልብ እንኳን ሳይል እኔ ለሱ መንገድ መልቀቄን ቀጠልኩ:: አንድ ቀን እንዲሁ ጎራ ብዬ አሳልፌው እንደቆምኩ ነበር « ከፊቴ ሲጋረጥ መንገድ መልቀቄን ብተውስ?» የሚለው ሃሳብ ከአእምሮዩ ውስጥ ዱብ ያለው::

ይህ የድፍረት ሃሳብ ከመወለዱ ጎልብቶ ቀስ በቀስ ሙጭጭ አለብኝና እረፍት ነሳኝ:: ሥራዬ ጧት ማታ ይህንኑ ማውጠንጠን፣ ስለዚሁ ማለም ብቻ ሆነ:: ይህን ዕቅዴን ልፈፅመው በቆረጥኩ ቀን እንዴት እንደማደርገው በሕሊናዬ ለመመልከት ብዬ ወደኔቭስኪ ጎዳና ከወትሮው ይበልጥ አዘወትሬ መሄድ ጀመርኩ:: ምኞቴ እውን ሆኖ ለማየት ነፍሴ ቋመጠች እቅዴ ለፍሬ እንደሚበቃ ታየኝ:: ኋላም ደስታ አለዘበኝና የመጎነጡን ሃሣብ ችላ ብዬ መንገድ ሳልለቅለት ቀጥ ብዬ ሄጄ ከተላተምኩት ይበቃል ብዬ ወሰንኩ::

t.me/OLDBOOKSPDF

መጋጨቱ ኃይል የበዛበት ሳይሆን በልኩ፣ ትክክሻ ለትክክሻ፣ ከገደብ ሳያልፍ እንደሚሆን፣ የሚገጨኝን ያህልም እንደምመልስለት አሰብኩ::

ሳደርገውም አምርሬ ከተሳልኩ በኋላ ለቁርጡ ቀን መዘጋጀቱ ጊዜ ፈጀብኝ:: የመጀመሪያው ነገር ዕቅዴን በምፈፅምበት ወቅት የተቻለኝን ያህል ደኅና ሰው መምሰል ሲሆን፣ ለዚህም የተሻለ ልብስ መልበስ ይኖርብኛል:: ማን ያውቃል! ከዚያ የተራቀቀ የፒተርስበርግ ሕዝብ መሐል አጉል ነገር ሊፈጠር ይችላል:: ደህና ልብስ ከለበስኩ ሰው ሊፈርድብኝ አይችኩልም:: ከወታደሩም ጋር በአንድ ዓይን ይመለከቱኛል::

ከደሞዜ ላይ ብድር ወስጄ ጥቁር ጓንትና ባርኔጣ ገዛሁ:: አስቤው ከነበረው አረንጓዴ ባርኔጣ ይልቅ ጥቁሩ ግርማ የሚያለብሰኝ መስሎ ታዬኝ:: ሎሚ አይነቱ ባርኔጣ ዓይን የሚወጋ፣ እዩኝ እያለ የሚለፍፍ ይመሥላል ብዬ ተወኩት:: ባርኔጣና ጓንቱን ከመግዛቴ በፊት አስቀድሜ ጥሩ ሸሚዝ አዘጋጅቻለሁ:: አንዷ ጎደሎ ነገር ካፖርቴ ነበረች:: ለነገሩ መጥፎ አልነበረችም፣ ስለብሳትም ትሞቀኛለች:: ሆኖም ግን ገበሯ የተጣጣፈና በላይ አንገትየዋ ያጌጠው በምጥማጥ ፀጉር በመሆኑ በለበስኳት ቁጥር ቀጣፊ ደላላ ታስመስለኛለች:: ቢያንስ ፀጉሯን እንኳን አስነቅዬ መኮንኖች እንደሚለብሱት ካፖርት በቀበሮ ፀጉር መተካት የግድ ያስፈልገኛል:: ለዚህ ስል ከመደብር መደብር ተመላልሼ፣ አንዲት በቀበሮ ፀጉር የተዋበች ኮሌታ ላይ ልቤ ወደቀ:: ስጠይቅ ዋጋዋ ውድ ሆነብኝ:: ከዚያም የኔን የምጥማጥ ፀጉር አንገትያ ሽጬ፣ ቀሪውን ከቢሮ አለቃዬ ከአንቶን ተበድሬ ለመግዛት አሰብኩ:: አንቶን ለዘብ ያለ፣ ቆም ነገረኛና የረጋ ሰው ነው:: ገንዘብ አያበድርም:: ስራዬን ያገኘልኝ አንድ የሚያውቀኝ ሰው፣ ለአንቶን የኔን ጥሩ ሰራተኛነት አወድሶለታል:: አንቶንን ብድር መጠየቅ የሞት ሞት መስሎኝ ከፉኛ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተሰቃየሁ፣ ለሦስት ቀናት እንቅልፍ ባይኔ አልዞር አለ:: ለነገሩማ ያኔ በወቱ ተኝቼ አላውቅም:: ትኩሳት ጀመረኝ:: ልቤ ይከዳኝና መምታቱን መተው ይቃጣዋል:: ከዚያም ቆየት ብሎ ድም! ድም! እያለ ይንፈራፈራል::

አንቶን ብድር ስጠይቀው ተገረመ:: ግንባሩን ቋጥሮ በዝምታ እየተመለከተኝ ቆየና፣ ከከፍያ ቀን ሁለት ሳምንት በኋላ ያበደረኝን ከደሞዜ ቆርጦ እንደሚሰጠኝ ተስማምቼ፣ ፈርሜ፣ ገንዘቡን ወሰድኩ:: እንዲህ እንዲህ እያለ ሁሉ ነገር ዝግጁ ሆነ:: ውቡ የቀበሮ ፀጉር ከካፖርቴ አንገትያ ላይ ተተከለ፣ እኔም ለቁርጡ ቀን መዘጋጀት ጀመርኩ:: አዩ፣ እንዲሁ በጭፍን ዘልዬ ድርግም ማለት የለብኝም:: ሁሉም ነገር በዘዴና በርጋታ ቢሆን ይበጃል:: ያም ሆኖ እንኳን ከብዙ ሙከራ በኋላ ተስፋ መቁረጥ ያንዣብበኝ ጀምሮ ነበር:: ከመቶ አለቃው ጋር ደፍሬ ልላተም አቃተኝ:: ከዚያ ሁሉ ዝግጅትና ውሣኔ በኋላ፣ ላልምረው ተገዝቼ ሄጄ፣ ከፊቴ ሳየው ሐሞቴ ፈስሶ እኔ ቀድሜ መንገድ እለቅና እሱ መፈጠሬን ረስቶ መሠሥ ብሎ ያልፋል:: ጭራሹን ልጠጋው ስል መፀለይ ጀመርኩ:: እግዚአብሔር ቆራጥነቱን ሠጥቶኝ፣ የወጠንኩትን ያስፈፅመኝ ዘንድ:: አልተሳካልኝም:: አንድ ቀን ታዲያ ሳላደርገው ላልመለስ አምርሬ ሄድኩና ያደረግኩት ነገር ቢኖር፣ ከፊቱ ስንዝር ሲቀረኝ ወኔዬ ፈረጠጠና እግሩ ስር ተደናቅፌ እንደኳማ ኳስ መንጠር ብቻ ነበር:: እሱም በርጋታ ተራምዶኝ አለፈ:: ያኔ ሌሊት ታምሜ አደርኩ:: ሰውነቴ እንደእቶን ነደደ:: አቃዠኝ:: ተወራጨሁ::

ከዚህ በኋላ የስቃዬ ፍፃሜ በተመኘሁት መንገድ መጣልኝ:: ለነገሩማ ከፍፃሜው ቀን በፊት ይህን አደገኛ ዕቅዴን እርግፍ አድርጌ መተው እንዳለብኝ ወስኜ ነበር:: ከዚያም ይህንን ከንቱ ደባዬን እንዴት እንደምተወው ለማየት ለመጨረሻ ጊዜ ወደኔቭስኪ ጎዳና ሄጄ ሳለሁ፣ ከሰውዬው ሦስት እርምጃ ሲቀረኝ በቅፅበት ቆረጥኩና

t.me/OLDBOOKSPDF

አይኔን ጨፍኜ ገሠገሥኩ:: ትከሻ ለትከሻ ተሳተምን! አንዲት ጋት ያህል እንኳን ፈቀቅ ሳልል እንደ እኩል በኩራት አለፍኩት:: ሰውዬው ምንም ያልተፈጠረ ለማስመሠል ዞር እንኳን ብሎ አላየኝም:: ማስመሰሉ እንደሆነ አልጠፋኝም:: አሁንም ጥርጥር የለኝም:: ለነገሩ በግጭቱ የተጎዳሁት እኔው ነኝ:: ያ አይደለም ቁም ነገሩ:: ፍሬ ነገሩ ዕቅዴን ማሳካቴና ክብሬን መጠበቄ ነው:: ቅንጣት ፈቀቅ ሳልልለት እኩልነቴን አረጋግጬ፣ በብቀላ ጠጅ እንጀቴ ርሶ ወደቤቴ ተመለስኩ:: በደስታ ተፍለቀለቅኩ:: ድምፄን ከፍ አድርጌ አዜምኩ:: ይህ ከሆነ ከሦስት ቀናት በኋላ ምን ውስጥ እንደገባሁ አልገልፅልዎትም:: የዚህን መፅሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ ካነበቡ መገንዘብ አያዳግትዎትም:: ያ መቶ አለቃም ጥቂት ቆይቶ ወደ ሌላ አገር ስለተዛወረ፣ ከዚያ ወዲህ ሳላየው አሥራ አራት ዓመታት አልፈዋል:: የት ደርሶ ይሆን? ዛሬስ ማንን ይሆን የሚረጋግጠው?

- 10 -

የመልከስከስ በሽታዬ ገለል ሲልልኝ፣ ሁሉን የመጥላትና የመሰልቸት ዛር ይሰፍርብኛል:: ነፍሴ ከፀፀትና ቁጭት እግር ስር ወድቃ ትላሸቃለች:: ይህን አበሳየን ልሸሸው ጥሬ ሲያቅተኝም ቀስ በቀስ ተላምጄው ቁጭ እላለሁ:: የማልላመደው ነገር የለም:: መላመድም ባይሆን ቢያንስ ልታገሠው መፍቀድ ይቻለኛል:: በዚያ ላይ ደግሞ ሁሉን ከሚያሳምር ማምለጫዬ፣ ከላቀውና ከመልካሙ መናቤ ገብቼ አገግማለሁ:: እንደኔ በህልምና በቅዠት የሚባክን ማንም የለም:: ከጭልምልሟ ጎጆዬ ተወትፌ፣ አንዳንዴ ለሦስት ወራት ሳላሰልስ፣ ሳይታክተኝ በቅዠት ዓለም መዋዠቅ እችላለሁ:: በዚያ ጊዜ ታዲያ፣ ለይሉኝታ በካፖርቱ አንገትያ የተሳቀቀው ግብዝ ሐሞተቢስ እንዳልመስልዎ:: ብቻዬን በምነግሥበት የራዕይ ዓለም፣ የከበርኩ ጀግና ነኝ:: በዚህ ወቅት ያ ግድንግድ መቶ አለቃ ሊጎበኘኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢመጣ፣ እግሩን በደጃፌ እንዲያሳልፍ በጭራሽ አልፈቅድለትም:: ከፊቴ ቆሞ ማሠቡ እንኳን ይረብሸኛል::

ቅዠቶቼ ምን ነበሩ? እንዴትስ ከእነርሱ ርካታ ማግኘት ቻልኩ? ይህን አሁን ልነግርዎ ያዳግተኛል:: ያኔ ግን በውነቱ ጠቅመውኛል:: አሁንም ቢሆን አልፎ አልፎ በህልምና ቅዠት ነፍሴን አጠፋታለሁ:: በተለይም ስልክስክስ፣ ስዘቅጥና ከቆሻሻ ነገር ውስጥ ስርመጠመጥ ቆይቼ ልቤ በፀፀት እሾህ በምትወጋበትና ዓይኖቼ በእንባ በሚቀልጡበት ወቅት የማለም ማዕበል ይዞኝ ሲጓዝ ወዲያው በሐሴት፣ እንደጌሾ በሚያሰክር ደስታ ከመብከንከኔ ብዛት በውስጤ ቅንጣት እንኳን ምፀት ወይም በራስ መቀለድ አይገኝም:: እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ከእቅፋቸው ያገቡኛል:: በተዓምር፣ ልቆጣጠረው በማልችለው ኃይል አማካይነት ሁሉ ነገር ተንሠራፍቶ፣ አድነና በልዕነ የተንጣለለ፣ የመልካም፣ ለፍሬ የታጨ ምግባር ምዕራፍ ከፊቴ ወለል ብሎ ተከፍቶ፣ ልገባበት እንደምችል ጭፍን እምነት ከልቤ ውስጥ ይወለዳል:: ይህ ምግባር ምን እንደሆነ በውሉ ባላውቀውም ዋናው ነገር ዝግጁ ሆኖ እንደሚጠብቀኝ ማወቄ ነበር:: በመናብ ከንፍ መጥቄ፣ ነጭ ፈረስ እየጋለብኩ፣ አክሊሌን ደፍቼ ከመንግሥተ ሠማይ ጥልቅ እላለሁ::

ምክትልነትን ነፍሴ ትጠላለች:: ለዚህም ነው የግርጌ ቦታዬን በእውን ሕይወቴ በአርምሞ የተቀበልኩት:: በበኩሌ፣ በታላቅነትና በጭቃነት መሃል ያለውን ቦታ አልፈልገውም:: ጉድ የሠራኝም ይኸው ነው:: የውርደት ረግረግ በዋጠኝ ቁጥር ባንድወቅት ታላቅነቴ እየተዕናናሁ፣ ትውስታው ግሚን ያፀዳልኛል:: (ለተራ ሰው ከዐያፍ ነገር ገብቶ መዳሸቅ አሳፋሪ ነገር ሲሆን፣ የታላቅ ሠው ክብሩ ግን በግም ከመበከል ስለሚያድነው ለጊዜው ቢዘፈቅበትም አይከፋም ብዬ የማስብ ይመስል::)

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለውቡና ታላቁ ነገር ማሰብ የምጀምረው በከርፋት ማጥ እየዳከርኩ መውጫው ሲጠፋብኝ መሆኑ ይገርመኛል:: የዚህ ሃሳብ መከሰት ብቻ ግን የልክስክስነቴን ፍፃሜ አያበስርም፣ ከጥፋቴና ከመርከሴ ጣዕም አፍልቆ ግሩም ቃናና መዓዛ ይጨምርበታል እንጂ:: ይህ ጣዕም የተቀመመው በተቃራኒ ነገሮች፣ በስቃይና ሰላም በሚነሳ የማውጠንጠን አባዜ ነው:: ይህ ሁሉ ታዲያ የረቀቀ ትርጉም ያለው ይመስለኛል::

በነዚያ የራዕይ ጊዜያት በውስጤ ይፈስ የነበረው ፍቅር! የዚያ ዓይነት ፍቅር በምኞትና በመናብ ዓለም እንጅ በእውን ለምንም ዓይነት የሰው ልጅ ሁናቴ አይገጥምም:: ሁሉ ሸጋ የሆነበት፣ ፍፃሜ ሁሉ የሠመረበት:: የቅዠቴ ሠጋር ፈረስ ዕፁብ ድንቅ ከሆነ የሥነጥበባት ዓለም፣ ከገጣሚዎችና ከደራሲዎች ለቃቅሜ ያሻሁትን እንዲመስል የቀባሁት እንከን አልባ ሕይወት ከሰፈነበት ዓለም ያደርሰኛል::

ለምሣሌ ከሰው ሁሉ በላይ ሆኜ ሁሉም ከፊቴ ለጥብለው እጅ እየነሱኝ ታላቅነቴን ሲያወድሱና፣ የበደሉኝን ሁሉ ይቅር ስል ይታየኛል:: ሌላ ጊዜ ደግሞ ዝነኛ ባለቅኔ ወይም የቤተመንግሥት ሹም ሆኜ የሚፈስልኝን የገንዘብ ጅረት ለችሮታ ስሰጥ አልማለሁ:: ከአድናቂዎቼ ፊት ራሴን እያጣጣልኩ ስናዘዝ፣ ኃጢአቴ ተራ ኃጢአት ሳይሆን ለይምሰል በድራቶ የተሸፈነ ዕፁብ ድንቅ ነገር መሆኑን ሕዝብ ሲመለከት አስባለሁ:: እያለቀሱ ሲስሙኝ፣ ከዚያም ጫማዬን ወዲያ ብዬ በባዶ እግሬ፣ በባዶ ሆዴ መልካሙን ዜና ላስራጭ ጉዞ ስጀምር . . . ወዘተ ይታየኛል:: ይህን እርስዎስ ያውቁት የለም?

ከሦስት ወራት በላይ ግን ቁጭ ብዬ በቅዠት መባከን አልችልም:: ከዚያ ወዲያ በሰው ጥማት የተኮማተረችው ነፍሴ ከሰው መቀላቀል ይናፍቃታል:: ለኔ ታዲያ ከሰው መቀላቀል ማለት የቢሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

አለቃዬን አንቶንን መጎብኘት ነው:: በሕይወቴ ለረጅም ጊዜ የቆየው ትውውቄ ከሱ ጋር ብቻ መሆኑ ይገርመኛል:: እሱም ዘንድ እንኳን የምሄደው የህልም ዓለም ደስታዬ ሞልቶ መፍሰስ ሲጀምርና፣ ከልቤ የሚንተከተከው የሰው ፍቅር ባስቸኳይ ወጥቼ የሰውን ዘር እንዳቅፍ ሲገፋፋኝ ነው:: ለዚያ ደግሞ ቢያንስ አንድ እንኳን ሰው ሊኖር ያስፈልጋል:: አንቶን ከቤቱ በጊዜ የሚገኘው ማክሰኞ ዕለት ብቻ ነው:: ስለዚህ የሰው ዘር ጥማቴን ከዚህ ቀን ጋር ማቆራኘት ነበረብኝ ::

አንቶን የሚኖረው አምስት ማዕዘን ከሚባል ሠፈር አራተኛ ፎቅ ላይ ሲሆን፣ አራት ትናንሽ ክፍሎች ያሉት ቤቱ ውስጡ ደብዛዛ ነው:: ሁለት ሴቶች ልጆቹና ዘወትር ሻይ የምታፈላ እህቱ አብረውት ይኖራሉ:: እቤቱ በሄድኩ ቁጥር የአሥራሶስትና የአሥራአራት ዓመት ሴት ልጆቹ እየተንሾካሾኩ ስለሚስቁብኝ በጣሙን አፍርና የምገባበት ይጠፋኝ ነበር:: የቤቱ ባለቤት አንቶን ከጠረጴዛው ፊት በቆዳ የተለበደ ሶፋ ላይ ቁጭ ብሎ ከሁለት የሥራ ጓደኞቹ ጋር ያወጋል:: ሁሌ የማገኛቸው እንግዶቹ እነኚያው ሁለቱ ሰዎች ነበሩ:: ወጋቸው ስለቀረጥ ጉዳይ፣ ስለሽንኅ ክርክር፣ ስለደሞዝ ዕድገትና ንጉሱን ደስ ስለሚያሰኛቸው ነገሮች ብቻ ነበር:: ከነርሱ ጋር ተቀምጬ ለአራት ሰዓታት እንደጅል ተለጉሜ ሳዳምጣቸው እቆይና፣ ከመሠልቸቴ ብዛት መላ አካሌ ደንዝዞ ላብ ላብ ይለኛል:: ሆኖም ግን የአንቶን ቤት እንግድነቴ እንደጠቀመኝ አልክድም:: አልፎ አልፎ የሚጎበኘኝን ከሰው ዘር አንገት ዘለህ ተጠምጠም የሚል በሽታዬን ይነቅልልኛል::

ሌላ ደግሞ እንደነገሩ የማውቀው፣ ሲሞኖቭ የተባለ ድሮ አብሮኝ የተማረ ሰው ነበር:: ወትሮ ትምህርት ቤት የማውቃቸውና አሁን ግን የማልጠይቃቸው፣ መንገድም ላይ ሲያጋጥሙኝ ሰላም የማልላቸው ብዙ አሉ:: የምሠራበትን ቦታ የቀየርኩትም ከእነርሱና እነርሱን ከሚያስታውሱኝ መራር የልጅነት ጊዜዬ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እለያይ ብዬ ሳይሆን አይቀርም:: ያ ትምህርትቤቴና እነኚያ

t.me/OLDBOOKSPDF

የግዞት ዓመታት የተረገሙ ይሁኑ! ከትምህርትቤት ወጥቼ ነፃነቴን እንደተቀዳጀሁ እዚያ ካወቅኋቸው ሁሉ ጋር ተቆራረጥኩ:: ከነኚያ ሁሉ ልጆች ሁለት ወይም ሦስት ብቻ ናቸው እስካሁን ሰላምታ የማልነፍጋቸው:: ከእነርሱም አንዱ ሲሞኖቭ ነው:: ሲሞኖቭ በትምህርቱ እምብዛም አልነበረም:: ዝምተኛና ልዝብ ነበር:: በአንዳንድ ነገሮች ላይ የነበረውን የግል አመለካከቱንና ግልፅነቱን ተመልክቼ በአንድ ወቅት ቀርቤው ነበር:: ለጥቂት ጊዜም ያህል በጓደኝነት ጡፈናል፤ ወዲያው ግንኙነታችንን ውርጭ ወረሰው እንጂ:: ዛሬ ታዲያ የዚህ ትውስታ እየረበሸውና፣ ወትሮ ያየብኝ እኩይነቴ ያልለቀቀኝ እየመሠለው የሚጠላኝና የሚርቀኝ ይመሥለኛል:: ቢሆንም ግን እኔ ዓይኔን ጨፍኜ እቤቱ መሄዴን ቀጠልኩ::

አንድ ሐሙስ ቀን፣ የአንቶን ቤት ለእንግዶች በሚዘጋበት ዕለት፣ ሲሞኖቭን አስታወስኩት:: ወደቤቱ እያመራሁ ሳለሁም ሲሞኖቭ የእኔ ከአጠገቡ መሆን እንደሚያውከውና፣ መሄድ እንደሌለብኝ ተሰማኝ:: ነገር ግን ይህን መሣይ የሃሣብ ሹክታዎች ለክፋት ይመሥል ልሸሸው ከሚገባኝ ነገር ጎትተው ስለሚያላጉኝ፣ ሳላመነታ ቀጥ ብዬ ወደቤቱ አመራሁ:: ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት ከአንድ ዓመት በፊት ነበር::

ሁለት የቀድሞ አብሮተማሪዎቼንም ከሱ ጋር አገኘኋቸው:: ስገባ ከፍ ያለ ቁም ነገር የሚወያዩ ይመስላሉ:: የኔን መኖር ከምንም አልቆጠሩት:: ካየኋቸው ዓመታት ስላለፉ እኔን ችላ ማለታቸው ደነቀኝ:: ከክፍሉ ዝንብ የገባ ያህል እንኳን ልብ አላሉኝም:: ትምህርት ቤት ሣለሁ ልጆች ሁሉ ቢጠሉኝም እንኳን፣ ይህን የመሠለ የንቀት ክሰ ተግቼ አላውቅም:: በስራዬ ጥሩ ደረጃ አለመድረሴ፣ የለበስኩት ድሪቶዬና፣ ባጠቃላይ ወድቄ መቅረቴ በእነርሱ አመለካከት የዋጋቢስነቴ ምልክት በመሆኑ እንደናቁኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገባኝ:: ይህን የመሠለ ውርደት ተቀብዬ ግን ይሁን ለማለት አልተዘጋጀሁም ነበር:: ሲሞኖቭማ ሲያየኝ ጭራሹን የተገረመ መሠለ:: ለነገሩ ከቤቱ ባየኝ ቁጥር ይገርመዋል:: በሁኔታቸው ግራ ተጋብቼ፣ ቅስሜ ተሰብሮ፣ ሲከፉኝ ተቀምጬ ወሬያቸውን ማዳመጥ ጀመርኩ::

እንደዚያ በተመስጦ የሚወያዩት፣ ወደሌላ ክፍለሃገር በቅርቡ ለሚሄደው እዝቬርኮቭ ለሚባል ጓደኛቸው በማግስቱ የመሸኛ ራት ስለማዘጋጀት ነበር:: አቶ እዝቬርኮቭም የኔው አብሮተማሪ ነበር:: ትምህርታችንን ልንጨርስ ስንቃረብ ነበር እሱን መጥላት የጀመርኩት:: የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ሳለን እዝቬርኮቭ መልከመልካም፣ በሁሉ የተወደደ፣ ሲፈነጥዝና ሲቦርቅ የሚመሸለት ልጅ ነበር:: ያኔ እንኳን ደስተኛና መልከመልካም በመሆኑ ብቻ ነበር የጠላሁት:: በትምህርቱ ድሮም ደካማ ነበር:: እየቆየ ይባሱን ተስፋቢስ ቢሆንም:: ግን በታዋቂ ዘመዶቹ ምክንያት ያለችግር ትምህርቱን ጨርሶ ለመመረቅ በቃ:: ትምህርቱን በጨረሰበት ዓመት፣ ትልቅ ርስት ከሁለት መቶ ገባሮች ጋር ወርሶ በኛ በድሆቹ ላይ ይወጣጠርና ይበጣጠስ ጀመር:: ገራገር ቢሆንም እንኳን ብልግናው ልክ አልነበረውም:: የዚያን ጊዜ ተማሪዎች ጥራዝ ነጠቅ የኩራትና የራስ ክብር ሥሜታቸው እንኳን እዝቬርኮቭን ከመለማመጥና ጫማውን ከመሣም አላዳናቸውም:: ጉራው እየናረ በሄደም ልክ አጃቢውና አወዳሹ በዛ:: አሁን ሳስበው፣ ያ እዝቬርኮቭን ከቦ የሚያጨበጭብ ተማሪ ሁሉ ከሱ ጥቅም ያገኝ መሥሎት ሳይሆን፣ እንዲያው ተፈጥሮ ስላደለችውና ስለሞላለት አድናቆቱን በማጎብደድ ማሳየቱ እንደነበር ይገባኛል::

ከዚያም አልፎ እዝቬርኮቭ በመካከላችን የማኅበረሠብ ሥነምግባር አዋቂ ተደርጎ ይገመት ነበር:: ይህ ነበር እኔንም በንዴት የሚያቃጥለኝ:: ድፍረት የተሞላበት ቃጭል ድምፁን፣ ያለአፍረት

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚዘራቸው ወዛቸው የተሟጠጠ የራሱን ቀልዶች ማድነቁን፣ ቢያምርም እንኳን ቂልነት የተቀባ (ሆኖም የአእምሮ ልቀት በሚነበብበት ፊቴ ብለውጠው የምወደው) ፊቱን፣ ግዴሌሽነቱን፣ ሁሉን ጠላሁት። ወደፊት ስላቀዳቸው የፍቅር ምርኮዎችና፣ በዚያ ሳቢያ ስለሚከተሉት በርካታ ፍልሚያዎች ጉራውን ሲነፋ መስማት አንገፈገፈኝ። ትዝ ይለኛል አንድ ቀን በእረፍት ሠዓት ስለወደፊት ዕቅዱ ለጓደኞቹ እያወራ፣ ፀሐይ እየሞቀች እንደምትቦርቅ ቡችላ ተቀናጣና፣ ከእርሰቱ የምትገኝ አንዲትም ገጠሬ ልጃገረድ ከሱ ወጥመድ እንደማታመልጥ ሲዝት ሰምቼው፣ ከዘወትር ልጉምነቴ ተፈትቼ ልክ ልኩን ስነግረው። « እነዚያ ሪዛም ገባሮቼ በዚህ ሳቢያ ቢያምፁ፣ እያንዳንዳቸውን አስገርፌ ግብራቸውን እጥፍ አደርገዋለሁ! » ብሎ ሲፎክር እንስሶቹ ሲስቁለት እኔ ተጋፈጥኩት። የወረድኩበት ለገጠሬዎቹ ክረዶች አዝኜ ሳይሆን እዝቤርኮቭን የመሠለ አልባሌ ሰው ሲሳቅለት በማየቴ ነበር። ጥሩ አድርጌ መለስኩለት። እዝቤርኮቭ ግን ደደብ ቢሆንም በቀላሉ የማይከፋ እፍረተቢስ ነውና ድንፋታዬን ስቆ አለፈው። ሙከራዬ ሳይሳካልኝ፣ የተሳቀለት እሱ ብቻ ሆኖ ቀረ። ከዚያን ቀን ጀምሮ እንደቀልድ እያደረገ በነገር ይኮረኩመኝ ጀመር። እኔ ግን ቂሜን በሆዴ ቋጥሬ፣ በይምሰል ንቂት ልጓም ተሸብቤ መልስ አልሰጠሁትም። ከተመረቅን በኋላ ሊቀርበኝ መሞከሩ ራሴን ስላሞካሸልኝ ፊት አልነሳሁትም ነበር። ሆኖም ግን የማይቀረውን ወዲያው ተቃቅረን ተራራቅን። ከዚያ ቆየት ብሎ በኮሌኔልነት መሾሙንና ጋጠወጥ አኗኗር መጀመሩን ሰምቼ ነበር። ኋላም ስለደረሰበት ማዕረግ ወሬ ደርሶኛል። መንገድ ላይ እያየኝ ሠላምታ ሲነፍገኝ እኔን ከመሠለ ትቢያ ጋር ሰላምታ በመለዋወጥ ደረጃውን ሲያራክስ መታየት ፈርቶ እንደሆነ ገብቶኛል። አንዴ ደግሞ ከቴያትር አዳራሽ አንደኛ ደረጃ ክፍል ውስጥ ተቀምጦ፣ የማዕረግ መለያውን ከትከሻው ኮልኩሎ፣ የአንድ የሽማግሌ ጄኔራል ሴቶች ልጆች ፊት ሲያጎበድድና ሊነጠፍላችሁ ሲል ሳየው፣ ትምህርቱን በጨረሰ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ራሱን መረን

t.me/OLDBOOKSPDF

መልቀቁን ተመለከትኩ:: ምክንያቱም፣ ምንም እንኳን ያኔም መልካምነቱና ግርማ ሞገሱ ባይጠፋም፣ አካሉ ረግቦና ከብዶ ነበር:: ሰላሳ ሲሞላው ሥቡ እንደሚንጠለጠል ጥርጥር አልነበረኝም:: ታዲያ የወትሮ አብሮተማሪዎቼ ሪ ት ለማዘጋጀት ደብ እንቅ የሚሉት ለዚሁ እዝቬርኮቭ ነበር:: ራሳቸውን የሱ እኩል አድርገው ባይመለከቱም እንኳን፣ በእነዚያ ሦስት ዓመታት ከእዝቬርኮቭ ጋር የነበራቸውን ጓደኝነት ጠብቀዋል::

ሲሞኖቭ ቤት ከመጡት መሐል አንደኛው ፌርፊችኪን የተባለ በሰው መቀለድና ማሾፍ የሚወድ ድውይ ጦጣ ፊት ነው:: ከልጅነታችን ጀምሮ አምርሬ የምጠላው ዋነኛ ጠላቴ ነበር:: ፌርፊችኪን በልቡ ቦቅቧቃ ሆኖ ሳለ ጀግና መሳይ፣ አይናውጣ ጥፍራም ነው:: እሱ ነበር ከእዝቬርኮቭ አጃቢዎች አንዱ:: እዝቬርኮቭን ማዘል የሚቃጣው ቢጠቅመኝ ብሎ ነበር:: አንዳንዴም ገንዘብ ይበደረዋል:: ሌላው ሲሞኖቭ ቤት ያገኘሁት ትሩዶሊቦቭ በምኑም እገሌ የማይሉት ተራ ወታደር ነበር:: ቁመቱ ዘለግ ያለና ፊቱ ቅዝቃዜ የለበሰ፣ ለሃብትና ለሹመት የሚያደገድግ፣ ከጧት እስከማታ ስለዕድገትና ደሞዝ ቢያወራ የማይታክተው ሰው ነው:: የእዝቬርኮቭ የሩቅ ዘመድ በመሆኑ በመካከላችን ለየት ያለ ቦታ ተሰጥቶት ነበር:: ከምንም ስላልቆጠረኝ ትህትና ቢነፍገኝም ብዙም አልተከፋሁም::

«መልካም» አለ ትሪዶሊቦቭ:: «እያንዳንዳችን ሰባት ብር ብናዋጣ በሃያ አንድ ብር ጥሩ እራት መብላት እንችላለን:: እዝቬርኮቭን ግን አናስከፍለውም::»

«ልክ ነህ፤ እኛ ጋብዘን አናስከፍለውም» ሲል ተስማማ ሲሞኖቭ::

t.me/OLDBOOKSPDF

«በርግጥ እዝቬርኮቭ ዝም ብሎ ስንከፍል የሚያይ ይመስላችኋል? በጨዋነቱ ግብዣችንን ይቀበላል፣ ኋላ ግን በራሱ ገንዘብ ስድስት ወይ ሰባት ጠርሙስ መጠጥ ማዘዙ አይቀርም» አለ ፊርፊችኪን በጌታው ርስት እንደሚኩራራ አገልጋይ::

«ሰባት ጠርሙስ ለሶስታችን?» ሲል ጠየቀ ትሩዶሊቦቭ:: ልብ ያለው የጠርሙሱን ሰባት መሆን ብቻ ነበር::

«እሺ እንግዲህ:: ሦስታችን፣ ከእዝቬርኮቭ ጋር አራት ነን:: ሃያአንድ ብር:: ነገ ከፓሪስ ሆቴል፣ ልክ በአሥራአንድ ሰዓት» የዝግጅቱ አቀናባሪ ሲሞኖቭ በዚህ ውይይቱን ደመደመ::

«ለምን ሃያ አንድ ብቻ? እኔ ስጨመር ሃያስምንት ብር አይሆንም?» ስል ጠየቅኩ:: ከባህር ሆዴ የተቀጣጠለውን የቁጣ ሞገድ ለማመቅ እየሞከርኩ፣ እያቃተኝ::

ይህ ያልጠበቁት ቀላቅሌኝ ማለቴ በአይናቸው ከፍ ሊያደርገኝ የሚችል ጥሩ ዘዴ መስሎ ታየኝ::

«አንተም መምጣት ትፈልጋለህ?» ሲሞኖቭ ቅሬታውን ሳይደብቅ ዓይኖቼን ወዲያ ብሎ ጠየቀኝ:: እንደሱ ጠንቅቆ የሚያውቀኝ የለም::

«እንዴ! ባልሳሳት እኔም እኮ የድሮ አብሮተማሪያችሁ ነበርኩ! ገለል ስታረጉኝ አይከፋኝም?» ብዬ ገነፈልኩ::

«የት ብለን እናግኝህ?» ሲል ፊርፊችኪን ተመናጨቀ::

t.me/OLDBOOKSPDF

«ከእዝቤርኮቭ ጋር ተቀያይማችሁ የለም?» ሲል ተቀጠለ ትሩዶሊቦቭ ግንባሩን ከስክሶ:: እኔ ግን አንዴ ካሰብኩት ሙጭጭ ብዬ አልለቅም አልኩ::

«ያን ማንም ሊፈርድ አይገባውም» ስል መለስኩ ድምፄ እየተብረከረከ:: ምን እንደነካኝ ፈጣሪ ያውቃል:: «መምጣት የምፈልገው በዚሁ በመቀያየማችን ምክንያት ቢሆንስ?»

«በል እንግዲህ! አንተ እንደሆንክ ምንህም የማይጨበጥ ነህ» አለኝ ትሩዶሊቦቭ ከናፍሩን በደረቅ ፈገግታ ለጥጦ::

«እሺ ስምህን ጨምር» ሲል ወሰነ ሲሞኖቭ ወደኔ ዞር ብሎ «ነገ፣ በአሥራአንድ ሰዓት፣ ከፓሪስ ሆቴል፣ እንዳትረሳ::»

«ገንዘቡስ?» ሲል ፌርፊችኪን ሲሞኖቭን ጠየቀው፣ ድምፁን ዝቅ አድርጎ:: በጥያቄው ሲሞኖቭ እንኳን ሲሸማቀቅ አይቶ ደንገጥ አለ::

«እሺ መልካም:: ይህን ያህል መምጣት ከፈለገ ይምጣ» ብሎ ትሪዶሊቦቭ ከተቀመጠበት ብድግ አለ::

«ይህ እኮ ግን የኛ የቅርብ ጓደኞች እንጂ የሕዝብ ስብሰባ አይደለም! ያንተ መምጣት እያስደስተን ይሆናል» አለኝ ፌርፊችኪን ባርኔጣውን እያነሳ::

ወጥተው ሄዱ:: ፌርፊችኪን ደህና ዋል ሳይለኝ ሾለከ:: ትሩዶሊቦቭ ሳያየኝ ራሱን ነቅንቆ ወጣ:: ከኔ ጋር የቀረው ሲሞኖቭ ብቻ ነበር:: ቆሞ በመገረም እያየኝ ተቀመጥ አላለኝም::



t.me/OLDBOOKSPDF

«ህም . . . ደህና . . . ያው ነገ እንግዲህ:: ገንዘቡን አሁን ልትሰጠኝ ትፈልጋለህ? ማለቴ. . . እንዲያው ማን ያውቃል» ሲል አጉተመተመ የሚለው ጠፍቶበት:: ክው አልኩ:: በጥያቄው ሃፍረት እየገረፈኝ ሳለ ከሲሞኖቭ ድሮ የተበደርኩት አሥራአምስት ብር ትዝ አለኝ:: አልከፈለው እንጂ መበደሬን እንዳልረሳሁ እግዚአብሔር ያውቃል::

«እንደምታውቀው እዚህ ስመጣ ስለራቱ የማውቀው ነገር አልነበረም:: ያኛውን . . . . ሳልከፍልህ በመቅረቴ ይቅርታ . . . »

«አይ ግዴለም፤ ምንም አይደል:: ነገ እዚያው ስንገናኝ ትከፍላለህ:: እንዲሁ ማወቅ ፈልጌ ነው:: ችግር የለም. . . » አለኝና በመረበሽ መንቆራጠጥ ጀመረ:: ወለሉን በተረከዙ እየወገረ ወዲያ ወዲህ ሲመላለስ ለሁለት ደቂቃ ያህል ዝም ብዬ አስተዋልኩትና «የምትሄድበት አለህ?» ስል ጠየቅኩት::

«አይ የትም አልሄድ» አለና ወዲያው መለስ ብሎ « እ! ረስቼው . . . አዎ አንድ የምደርስበት ጉዳይ አለኝ . . . ለነገሩ ከዚህ ብዙም አይርቅ » አለኝ እንደማባበል አድርጎ::

« እንዴ? ምን ነካህ ለምን አትነግረኝም ነበር ታዲያ?» ስል ብድግ ብዬ ባርኔጣዬን አፈፍ አደረግኩ:: ይህን ስናገር ነፃነት የሞላበትና ለቀቅ ያለ ሁኔታዬ ለራሴ እንኳን አስገርሞኛል::

« እዚሁ አካባቢ ነው እኮ . . . » አለ ሲሞኖቭ ወደበሩ ሳመራ እየተከተለኝ:: ያልነበረ ሽርጉዱ በጭራሽ አላማረበትም:: «ያው ነገ ልክ በአሥራአንድ ሰዓት» አለኝ ጮክ ብሎ ከኋላዬ:: በመሄዴ እፎይታ አግኝቷል:: የእኔም አንጀት በንዴት ገሞራ መጠበስ ጀምሯል::

t.me/OLDBOOKSPDF

«ምን ነካኝ? ምን ሰይጣን ሰፈረብኝ?» አልኩኝ እግሬ ከበሩ አልፎ መንገዴን እንደጀመርኩ:: «ለዚያ ወሮበላ? ለዚያ አሟጣ አዝቤርኮብ? አልሞክራትም! መሄድ በጭራሽ አይታሰብም! ሁሉም ገደል ይግቡ! ከነሱ ጋር አልተቆራኘሁ:: ሀሣቤን መለወጤን ነገ ለሲሞናብ በደብዳቤ አሳውቀዋለሁ::»

በንዴት የተቃጠልኩት ግን ከራቴ እንደማልቀር ውስጤ ስላወቀው ነበር:: እንዲሁ ለከፋት እንደምሄድ ጥርጣሬ አልነበረኝም:: መሄዴ አጉልና አሣፋሪ መሆኑ እየገባኝ፣ እንደማልቀር ግን ተረድቼዋለሁ::

ለነገሩማ መሄዴን ሊያሰናክል የሚችል ችግር አለ:- ገንዘብ አልነበረኝም:: የነበረችኝ ዘጠኝ ብር ናት:: ከዚያችው ላይም ሰባቷ፣ ቀን ቀን ለሚያገለግለኝ ለአፖሎን የወር ደሞዙ ይከፈልባታል:: አፖሎንን ካወቁት ደግሞ ደሞዙን ማዘግየት የማይሞከር ነገር ነው:: ስለዚህ ርጉም ፍጡር፣ ስለዚህ የሕይወቴ ነቀርሳ፣ ኋላ አወጋዎታለሁ:: ይሁንና አፖሎንን ደሞዙን ከልክዬም ቢሆን ከነገው ራት አልቀርም::

የዚያን ዕለት ማታ የሚዘገንኑ ሕልሞች ሳይ አደርኩ:: ሲመሻሽ ጀምሮ በትምህርት ቤት ያሳለፍኳቸው የግዞት ዓመታት ከሃሳቤ ሰርገው አልለቅም አሉኝ:: የሚያሳድጉኝ የሩቅ ዘመዶቼ ነበሩ ከትምህርት ቤት ወስደው የጣሉኝ:: ከዚያ በኋላ አይቻቸው አላውቅም:: በስድብ፣ በወቀሳና በማጥላላት አላሽቀው፣ ብቻዬን ከትምህርት ቤት ትተውኝ ሲሄዱ፣ በዚያ ለጋ ዕድሜዬ እንደትልቅ ሰው መተከዝና አካባቢዬን በዝምታና በጥርጣሬ መመልከት ልማዴ ሆኖ ቀረ:: ልዩነቴ አልገባ ያላቸው የትምህርት ቤቱ ውሪዎች ያለርኅራኄ መቀለጃቸው አደረጉኝ:: እንደነርሱ በቀላሉ ከሌሎች መጎዳኘትም ሆነ፣ ሲሳለቁብኝ በትዕግስት ማለፍ ባለመቻሌ ሁሉንም

t.me/OLDBOOKSPDF

ወዲያው ጠላኋቸው:: ራሴን ገለል አድርጌ፣ ኩራት ባስመሰልኩት ብቸኝነት ተጠቅልዬ፣ ከዘበት አለንጋቸው ለማምለጥ ሞከርኩ:: ጭካኔያቸው አንገፈገፈኝ:: በፊቴና በአካሄዴ ቀለዱብኝ:: ድንቁርናቸውን የሚለፍፍ ገፅታቸውን ኮልኩለው ተሳለቁብኝ:: እኛ ትምህርት ቤት የእያንዳንዱ ተማሪ መልክ በያመቱ ይብሱን ድድብና እየተጠናወተው ይሄዳል:: መልካቸው ያማረ ልጆች ይመጡና ጥቂት ቆይተው ነሁላላ፣ ማስጠሎ ሆነው ያርፋታል:: ገና በአሥራስድስት ዓመቴ ዝም ብዬ በመገረም አያቸው ነበር:: በአእምሯቸው ተልካሻነት፣ በምግባራቸው፣ በጨዋታቸውና በወሬያቸው አልባሌነት እደነቅ ነበር:: አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ባለማወቅ በድንቁርና ተጠምደው፣ በውን ጠቃሚ ለሆኑ አቢይ ጉዳዮች ቅንጣት እንኳን ደንታ እንደሌላቸው ሳውቅ፣ የበታቼ አድርጌ አያቸው ጀመር:: ለዚህ ያበቃኝ ግን የተገፋና የተረገጠ የራስ ክብሬ አልነበረም:: ሕይወትና ምሥጢሯ በግልፅ አልተከሰተችላቸውም ነበር:: ይህ ነበር የሚያበሳጨኝ:- ቁልጭ ያሉ ግልፅ የየዕለት ጭብጥ ነገሮችን ሁሉ በድንግዝግዝ መነፅራቸው እየተመለከቱ፣ አንድ የሚያመልኩት ነገር ሹመትና ሽልማት ብቻ መሆኑን ማወቁ::

ሐቅ ሲገፋና ሲረገጥ በጭካኔ መሳቂያና መሣለቂያ ያደርጉታል:: የማዕረግና የአዋቂነት ልዩነት አይታያቸውም:: በአሥራስድስት ዓመታቸው ስለሹመትና ምቾት ያወራሉ:: በርግጥ የዚህ ሁሉ ስንኩልነት መንሥኤው በልጅነታቸው የከበቧቸው መጥፎ ምሳሌዎች ናቸው:: ይህ ሁሉ ሥር ያልሰደደ ክፋትና ተንኮል መሆኑንና፣ ከከይሲነታቸው ጀርባ እምቡጥነታቸው መኖሩን ባይም ልጅነታቸው እምብዛም ደስ የማያሰኝ፣ በሥርዓት አልባነት የተለወሱ መሆናቸው አሳዘነኝ:: ምናልባትም እኔ ከነሱ የከፋሁ ብሆንም አጥብቄ ጠላኋቸው፤ እነርሱም ጥላቻዬን ሰፍረው መለሱልኝ:: እንዲወዱኝ ብዬ ያደረግኩት ነገር አልነበረም:: ሲወድቁና ሲዋረዱ ማየት ነበር የምመኘው:: ከስድብና ከግልምጫቸው አመልጥ ብዬ

t.me/OLDBOOKSPDF

ትምህርቴ ላይ ተጠመጠምኩበትና ወዲያው ከምርጥ ተማሪዎቹ አንዱ መሆኔን ሲያዩ ገረማቸው:: ኋላም ከችሎታቸው በላይ የሆኑ መፃህፍትን ማንበቤንና ሰምተዋቸው የማያውቁ፣ ትምህርት ቤት ያልተማርናቸውን ነገሮች ማወቄን ተረዱ:: በዚህ እየደነቃቸው ሊቀልዱ ቢሹም፣ አስተማሪዎቼ እንኳን ሲያወድሱኝ አይተው ሊቅነቴን ተቀበሉት:: ጥላቻቸው ተዳፍኖ፣ ግንኙነታችን ሻካራና ቀዝቃዛ ቢሆንም ቅሉ፣ ስድባቸውን ገቱልኝ::

ጊዜ እየገፋ ሲሄድ ብቸኝነት አንገፈገፈኝና የሰው ጥማቴ በረታብኝ:: ከጥቂት ልጆች ጋር ጓደኝነት ለመመስረት ብሞክርም የአፍታ ጓደኝነታችን ስንክሳር የበዛበት ጠማማ ነገር ይሆንና ሳይቆይ ይፈርሳል:: አንዱ ጓደኛዬን ያደረግኩት ትዝ ትለኛል:: ከላይ በጓደኛ መሻት የተቃጠልኩ ብሆንም ከውስጤ የፈላጭ ቆራጭነት ሰይጣን ነበረና፣ የዚህን ልጅ ነፍስና ስጋ መግዛት ፈለግኩ:: የሚያውቀውንና የከበበውን ነገር ሁሉ አክ እትፍ ብሎ እንዲተው ጎተጎትኩት:: ትንፋሽ በማይሰጥ እፍ ያለ ጓደኝነቴ አስጨነቅኩት፣ አስፈራራሁት፣ አስነባሁት፣ አወራጨሁት:: ምንም የማያውቅ ጭምትና ታማኝ ልጅ ነበር:: የተመኘሁት፣ ልማርከውና ልገዛው ብቻ እንደሆነ ሁሉ፣ ራሱን ጠቅልሉ ከእጄ ሲያስገባልኝ ጊዜ ጠላሁትና አከላፍተው ጀመር:: አዎ እሱ ከሌሎቹ የተለየ ነበር:: ሁሉም እንደሱ ቢሆኑ ኖርማ የሁሉ ገዢ በሆንኩ:: ከትምህርት ቤት ተመርቄ ስወጣ መጀመሪያ ያደረግኩት ነገር ከማውቃቸው ሁሉ ጋር ላንገናኝ እንድለያይ ከሰለጠንኩበት የሙያ ክፍል መልቀቅ ነበር:: ያለፈውን ረግሜ በትቢያ ልሸፍነው:: ከዚያ ሁሉ በኋላ ታዲያ ወደ ሲሞናቭ ቤት የሚወስደኝ ምን እንደሆነ አላውቅም::

ሁሉ ነገር ባንዴ ሊሳካ የተቃረበ ይመስል በማለዳ ራሴን ከእንቅልፍ እቅፍ አላቅቄ ከአልጋዬ ተፈናጥሬ ዱብ አልኩ:: ሕይወቴ ከወሳኝ ምዕራፍ ጠርዝ የደረሰች፣ ታላቅ ነገር የዚያን ዕለት

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚወለድ መሠለኝ:: ከውጭ ከሚከሰቱ ነገሮች ባለመላመዴ፣ ረባም አልረባም አንድ ነገር ሲፈጠር፣ በሕይወቴ ትልቅ ለውጥ የሚያስከትል ይመስለኛል:: እያቁነጠነጠኝ ወደስራ ሄድኩና ለመዘጋጀት ብዬ ከዘወትሩ ሁለት ሠዓት ቀድሜ ወጣሁ:: ከሆቴሉ ቀድሜ መገኘት የለብኝም:: ከሌሎቹ በፊት ከደረስኩ፣ በግብዣው ከልክ በላይ የቋመጥኩ ይመስልብኛል::

ጫማዎቼን ራሴ ለሁለተኛ ጌዜ ወለወልኳቸው:: አገልጋዬ አፖሎን ጫማ በቀን ሁለት ጊዜ መወልወል ብልግና ነው ይላል:: ቢሞትም በጅ እንደማይለኝ ስላወቅኩ አልጠየቅኩትም:: ከዚያም ልብሶቼን መረመርኳቸውና ያረጁ፣ ያፈጁና የተጎሳቆሉ መሆናቸውን አየሁ:: ራሴን በጣሙን ችላ ብዬዋለሁ! አንድ የሚሻለው የስራ የደንብ ልብሴ ነበር:: እሱን ለብሼ ለእራት መሄዴ ግን አይታሰብም:: ይባስ ብሎ ከሱሪዬ ጉልበት ላይ ትልቅ ቢጫማ ነጥብ ቁጢጥ ብሏል:: ይህ ብቻ ከአሥር እጅ የራስ ክብሬ ዘጠኙን እንደሚሰርቀው አወቅሁት:: በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ማሰቤ ግብዝነት መሆኑ ተሰማኝ «አሁን የሃሳብ ጊዜ አይደለም፤ የዕውን ሕይወት ከፊቴ ተጋርጣለች» እያልኩ ራሴን መቀስቀስና በፍርሃት መጎንጥ ጀመርኩ:: የነገሩን ሁሉ ምንነት ከልክ በላይ ማጋነኔ ይታወቀኝ ነበር:: ግና ምን በጀኝ? ምኔንም መቆጣጠር ተሰኖኝ፣ ወባ እንደያዘው ሰው መንዘፍዘፍ ጀምሬያለሁ:: ያ እዝቬርኮቭ የሚሉት አሣማ ሲያየኝ እንዴት በንቀት እንደሚመለከተኝ፣ ያ ጡንቻራስ ትሪዶሊቦቭ በደረቅ ሃፍረተቢስ ዘበት እንደሚገመግመኝ፣ ያ ተባይ ፌርፌችኪን ከእዝቬርኮቭ ፊት ሽርጉድ እያለ እንደሚስቅብኝና፣ ሲሞኖቭ ይህን ሁሉ አስተውሎ እንደሚረዳ፣ ግብዝነቴንና ሃሞተቢስነቴን አውቆ በልቡ ከትቢያ እንደሚቆጥረኝ በተስፋ መቁረጥ አሰብኩት:: የሁሉም ነገር ምናምንቴነት ቁልጭ ብሎ ታዬኝ::

t.me/OLDBOOKSPDF

ብቀር ሳይሻል አይቀርም፤ ከመቅረቴ በፊት ግን ሰማይና ምድር ሊያልፉ ይገባል:: አንድ ነገር ማድረግ ካሰብኩ እስከጭንቅላቴ ሳልሰጥምበት አልተወውም:: ሳላደርገው ብቀር፣ «ሸሽተህ አረፍከው? ከሕይወት ደጃፍ ፈረጠጥክ! ? ወኔ አጥሮህ ደነበርክ!? » እያልኩ እስተሕይወቴ ፍፃሜ በራሴ እዘብታለሁና:: ነኝ ብዬ ያሰብኩት ቦቅቧቃ አለመሆኔን ለራሴ ማረጋገጥ ነበረብኝ:: ነፍሴ በፍርሃት ሽብር እየራደች ሳለች፣ ድል ስቀዳጅ፣ ፈላጭ ቆራጭ ስሆን፣ ሳዛቸውና ሲቀበሉኝ፣ ሌላው ቢቀር የአእምሮዬን ልቀትና የማይታበለው እውቀቴን አይተው ሲወዱኝ አለምኩ:: እዝቬርኮቭን ዋጋውን ሰጥቼው እርግፍ አድርገው ትተውት ሐፍረት ተከናንቦ ከዳር ተቀምጦ ታዬኝ:: ከዚያ በኋላ ምናልባት ታርቄው ለአዲሱ ጓደኝነታችን ፅዋችንን እናጋጭ ይሆናል:: እንዲህ እያሰላሰልኩ ሳለሁ ታዲያ፣ ይህን የመሰለውን ትርዒት እንደማልፈልገው፣ ልገስፃቸውም ሆነ ላሸንፋቸው፣ ላቀርባቸውም ሆነ እንዲወዱኝ ላደርግ እንደማልሻ ጥሩ አድርጌ አውቀው ነበር:: ያለምኩት ቢሳካም እንኳን ሁሉም በጠ ጠር የምለውጠው ከንቱ ነገር እንደሆነ በልቤ ጥርጣሬ አልነበረም:: ያ ቀን ቶሎ እንዲያልፍ እየፀለይኩ፣ በሰቀቀን መስኮቴን እየከፈትኩ፣ የሚወርደውን ግራጫ በረዶ ማስተዋል ቀጠልኩ::

በመጨረሻ አሮጌው የግድግዳ ሰዓቴ አሥራአንድ ሰዓት ሞላ ሲል ተንቋቋ:: ባርኔጣዬን ብድግ አድርጌ፣ የአፖሎንን ዓይን ሸሽቼ፣ አልፌው ውልቅ ብዬ ወጣሁ:: አፖሎን ከጧት ጀምሮ ደሞዙን እንድከፍለው ሲጠብቅ ነበር:: ከትእቢቱ ብዛት ግን አፍ አውጥቶ አልጠየቀኝም:: የቀረችኝን አምሣ ሳንቲም ለጋሪ ነጂ ከፍዬ እንደጌታ እየተንፈላሰስኩ ወደ ፓሪስ ሆቴል አመራሁ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀድሜ እንደምደርስ ማወቄ አልገደደኝም:: ስደርስ እንዳቸውም ካለመኖራቸው ሌላ ለራት የተያዘውን ክፍል እንኳን ማግኘት አልቻልኩም ነበር:: ጠረጴዛውም አልተዘጋጀም:: ምን ማለት ነው? አስተናጋጆቹን ጠያየቅኩና ራቱ ለአሥራአንድ ሰዓት ሳይሆን ለአሥራሁለት ሰዓት እንደታዘዘ ነገሩኝ:: አፍሬ የምግብ ክፍል ሃላፊውን ስጠይቀውም ይህንኑ አረጋገጠልኝ:: ሰዓቱ ገና አሥራአንድ ሰዓት ከሃያ ነው:: የተስማማንበትን ሰዓት ከለወጡት ሊያሳውቁኝ አይገባም ነበር? የከተማው ፖስታ ቤት ሳለ፣ ከራሴና ከአሳላፊዎቹ ፊት ውርደት የሚያለብሱኝ ምን በድያቸዋለሁ? ተቀመጥኩ:: አንደኛው አስተናጋጅ ጠረጴዛውን ማዘጋጀት ሲጀምር የመከፋት ሕመሜ ባሰብኝ:: አሥራ ሁለት ሰዓት ሲሞላ ሻማዎች በጠረጴዛው ላይ ተቀመጡ::

ከነበርኩበት ክፍል አጠገብ ሁለት የተበሳጩ የሚመስሉ ኮሶ ፊት ሰዎች በዝምታ ራታቸውን ያግበሰብሳሉ:: ከማይታየኝ ራቅ ያለ ክፍል ጫጫታ ይሰማኛል:: ጩኸትና የብዙ ሰዎች ጣራ ስንጥቅ ማሽካካት:: አልፎ አልፎ ጆሮዬን ከሚወጋው የቡችላ ዓይነት ድምፅና የፈረንሳይኛ ቃለአጋኖ ከዚያ ክፍል ሴቶች መኖራቸውን ተረዳሁ:: ባጭሩ እጅግ የሚያስከፋ ሁናቴ ነበር:: እንደዚያ መድረሻ ያጣሁበት ሰዓት ያጋጠመኝ በህይወቴ ጥቂት ጊዜ ስለነበር እዝቬርኮቭና አጫፋሪዎቹ በአሥራሁለት ሰዓት ከሆቴሉ ሲደርሱ ሳያቸው ነፃ አውጪዎቼ የሆኑ ይመስል ለቅፅበት የእፎይታ ደስታ ሊሰማኝ ከጅሎ ነበር፤ የደፋሁትን የእሣት አክሊል ላወልቀው::

አለቃው እዝቬርኮቭ ቀድሞ ገባ:: ሁሉም ይስቃሉ:: እኔን ሲያይ እዝቬርኮቭ ራሱን ሰብሰብ አድርጎ፣ በዝግታ እየተራመደ ተጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጋኘና፣ ወገቡን በልኩ ሰበር አድርጎ ሊጨብጠኝ እጁን ሲዘረጋ፣ አድናቂዎቹን ሰላም እንደሚል ጄኔራል ሊከሰት ከሚችል ያልታወቀ ነገር ራሱን የሚጠብቅ ይመስል ነበር:: እኔ የጠበቅኩት፣ ልክ እንደገባ ያን ጆሮ የሚሰረስር ሳቁን እየለቀቀ፣ ጣመቢስ የሆኑ ቀልዶቹን ይጀምራል ብዬ ስለነበር፣ ከትናንት ማታ ጀምሮ ለዚሁ ነበር የተዘጋጀሁት እንጂ፣ ይህን በመሠለ መመፃደቅና የጌትነት መሳይ ትህትና ይደፍረኛል ብዬ ፈፅሞ አላሰብኩም:: በምንም ላልደርስበት የራቀ፣ የበላዬ የሆነ አድርጎ ራሱን እንደሚያይ አሳወቀኝ:: እንደዚያ ራሱን ዝቅ ያደረገ መስሎ ሰላም ያለኝ ሊዘልፈኝ አስቦ ከሆነ ብዙ አያስከፋም፤ ተገቢ መልስ ልሰጠው እችላለሁ:: ግን ያ መመፃደቁ በኔ ለማፌዝ ብሎ ሳይሆን ከልቡ ከኔ የላቀ መስሎት፤ ልዩነታችን ከመግዘፉ የተነሳ ከእንግዲህ ባገኘኝ ቁጥር ቁልቁል ወርዶ ሲቸገር በመታገስ እንደሚመለከተኝ ያ የበግ ጭንቅላቱ ሹክ ብሎ ቢሆንስ? ይህን በመጠርጠሬ ብቻ ትንፋሽ አጠረኝ::

« ከኛ ጋር ለመቀላቀል ማሰብህን ሰምቼ ደነቀኝ» ሲል ጀመረ አዝቬርኮቭ ያለወትሮው መኮላተፍና መለፋደድ እየቃጣው:: «ተጠፋፍተን ከረምን:: አንተም ትሸሽናለህ:: ያሳዝናል:: እንደምታስበው እኮ መጥፎዎች አይደለንም:: ይሁንና ጌታው፣ ግንኙነታችንን ማደሳችን ደስ ያሰኘኛል» ብሎ ባርኔጣውን ከመስኮቱ ግርጌ ላይ ወርውሮ አስቀመጠው::

« ብዙ ጠበቅክ?» ሲል ትሩዶሊቦቭ ጠየቀኝ::

« በተነገረኝ መሠረት ልክ በአሥራአንድ ሰዓት ነው የደረስኩት» ድንፋታ ባረገዘ ድምፅ መለስኩ::

t.me/OLDBOOKSPDF

« ሰዓቱ መለወጡን አልነገርከውም ነበር? አለ ትሩዶሊቦቭ ወደ ሲሞኖቭ ዞር ብሎ::

« አልነገርኩትም:: ረሳሁ» መልሱ የፀፀት ሽታ እንኳን የለበትም:: ይቅርታ ሳይጠይቀኝ ስለምግቡ ሊጠይቅ ሄደ::

«እና አንድ ሰዓት ሙሉ ቁጭ ብለህ ጠበቅከን? ምስኪን» አለኝ እዝቬርኮቭ:: በሱ ቤት ሁኔታው አስቂኝ መስሎታል:: ዱርዬው ፌርፊችኪን በቃጭል ድምፁ ቀበል አድርጎ እንደዶሮ አስካካ::

«ይሄ በጭራሽ የሚያስቅ ነገር አይደለም! » ስል ፌርፊችኪን ላይ ጮህኩበት፣ ቁጣዬ ደረቴን ሰንጥቆ ሊወጣ ይተናነቀኛል::

«ጥፋቱ የኔ ሳይሆን የሌላ ነው:: ማንም ሊነግረኝ አልፈለገም:: ይሄ . . . ይሄ . . . ከልክ ያለፈ ነው::»

«ከልክ ያለፈ ብቻ ሳይሆን ሌላም ነገር ነው» ሲል ትሩዶሊቦቭ አጉተመተመ በየዋህነት ለኔ አዝኖ:: «አንተ ታጋሽ ነህ እንጂ ይሄ የለየለት ብልግና ነው:: ግን ሆን ብሎ አይመስለኝም:: እንዴት ሲሞኖቭ . . . ህም!»

«ይህ የተደረገው እኔ ላይ ቢሆን ኖሮ. . .» አለ ፌርፊችኪን::

«አንድ ነገር ታዝ ነበር፣ ወይም ማንንም ሳትጠብቅ ራትህን በልተህ ትሄድ ነበር» ብሎ አቋረጠው እዝቬርኮቭ::

«ተቀመጡ» አለ ሲሞኖቭ ከሄደበት ተመልሶ:: «ሁሉም ነገር ዝግጁ ነው:: ሻምፓኙ በደንብ ቀዝቅዞ ተቀምጧል . . . እ . . .

t.me/OLDBOOKSPDF

አድራሻህ አልነበረኝም» አለኝ ወደኔ ዞር ብሎ፣ «ወዴት ብዬ ልፈልግህ?» አይኔን ግን ማየት አልደፈረም:: እንደጠመደኝ ያስታውቅበታል:: ከትላንት ወዲህ ነገሮችን ሲያውጠነጥን የቆዬ ይመስላል::

ሁሉም ተቀመጡ:: እኔም:: ጠረጴዛው ክብ ነበር:: በግራዬ ትሩዶሊቦቭ፣ በቀኜ ሲሞኖቭ:: እዝቬርኮቭ ከፊት ለፊቴ፣ ከጎኑ ደግሞ ፌርፌችኪን በሱና በትሪዶሊቦቭ መሃል ተቀምጧል::

«ለመሆኑ ከመንግሥት መስሪያ ቤት ነው የምትሰራው? ሲል ጠየቀኝ እዝቬርኮቭ:: ከኔ ላይ ትኩረቱን አላነሳም:: መሸማቀቄን አይቶ ጓደኝነት እንደምሻና አይዞህ ሊለኝ እንደሚገባው ወሰኗል:: «በጠርሙስ አናቱን እንድለው ይፈልጋል?» እያልኩ በልቤ በንዴት ጨሰኩ:: ከሰው ጋር መሆን ስላልለመድኩ በትንሽ በትልቁ ቁጣ ቁጣ ይለኛል::

«አዎ» አልኩኝ ዓይኖቼን ከሰሃን ላይ ተክዬ::

«ይሻላል ብለህ ነው? የቀድሞ ስራህን ለምን ተውከው?»

«የቀድሞ ሥራዬን የለቀቅኩት ልለቀው ስለፈለግኩ ነው» አንጀቴ እየተቃጠለ ቃላቴን ከእሱ ይበልጥ ሦስት እጅ ለጠጥኳቸው:: ፌርፌችኪን ተቁነጠነጠ:: ሲሞኖቭ በምፀት ተመለከተኝ:: ትሩዶሊቭ ማንኪን አቁሞ በመገረም አስተዋለኝ:: እዝቤርኮቭ ቅሬታውን ለመደበቅ እየሞከረ:- «ክፍያህስ?» አለኝ::

«የምን ክፍያ?»

«ደሞዝህ ማለቴ ነው::»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ይህን ሁሉ ምርመራ ምን አመጣው?» አልኩና ወዲያው የደሞዜን ልክ ነገርኩት:: ፊቴ በእፍረት ቲማቲም መስሏል::

«ምንም የላት » ሲል እዝቬርኮቭ አጣጣለት::

«በዚያ ደሞዝ ሆቴል መብላት አይቻልም» አለ ፌርፊችኪን አፉን አሹሎ::

«ድኀማ ናት » አለ ትሩዶሊዩቭ ካንጀቱ::

«ደግሞ እንዴት ከስተሃል?!» ከድሮው በጣም ተለውጠሃል» ሲል ሰንኮፉን ተከለብኝ እዝቬርኮቭ፣ ከእግር እስከራሴ እኔንና ልብሴን እየቃኘ::

«አይ ይብቃህ አታሳቅቀው» ብሎ ሳቀ ፌርፊችኪን::

«ወንድም፣ በዚህ እንደማልሳቀቅ እንድታውቅልኝ እፈልጋለሁ» ብዬ ገነፈልኩ:: «ትሰማኛለህ? እዚህ ምግብ ቤት ራት ልበላ የመጣሁት በራሴ ገንዘብ ነው:: ያንን አስታውስ ጌታው ፌርፊችኪን!»

«ምን ማለትህ ነው? ማን በሰው ገንዘብ የሚበላ አይተሃል?» አለ ፌርፊችኪን የወጋሁበትን እሾህ ነክሶ:: ፊቱ ድልህ መስሎ፣ የቁጣ እሣት በለበሱ ዓይኖቹ አፈጠጠብኝ::

« እንጃ » አልኩኝ ራሴን ለመቆጣጠር እየሞከርኩ:: «ሌላ ደህና ቁምነገር ብንጫወት የተሻለ ይመስለኛል::»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ችሎታህን ልታሣየን አስበሃል?»

«እሱን ተወው፡፡ ያ እዚህ አያስፈልግም፡፡»

«ታዲያ ይህ ሁሉ ዝብዝብ ምን አመጣው? የመንግሥት መስሪያ ቤት ስራ ጭንቅላትህን ነካው?»

«አይ ይብቃችሁ! » አለ እዝቬርኮቭ፡፡

«ቅጣ ያጣ ነገር» አለ ሲሞኖቭ ድምፁን ዝቅ አድርጎ፡፡

«እውነትም ቅጥ ያጣ! ጥሩ ጓደኛችንን ልንሸኝ በተሰባሰብንበት ስለገንዘብ ታወራለህ?» ብሎ ገላመጠኝ ትሩዶሊቦቭ፡፡ «ትናንት ሳንጋብዝህ በግድ ተቀላቀልክ፡፡ አሁን ታዲያ ምናለ ሰላም ብትሰጠን?»

«ይብቃ! ይብቃ! » ብሎ ጮኸ እዝቬርኮቭ፡፡ «ቆም አድርጉት፡፡ አጉል ነገር ውስጥ አንግባ፡፡ ይልቁን ባለፈው እንዴት ከትዳር አፋፍ እንደተመለስኩ ላጫውታችሁ፡፡»

ከዚያም ቀጥሎ አንድ ቀን እንዴት ከትዳር አፋፍ እንደተመለሰ፣ የለዛ ጠብታ የሌለበት ታሪክ ተረተረ፡፡ በነገራችን ላይ ከእዝቬርኮቭ ትረካ ውስጥ ስለጋብቻ አንድ እንኳን ቃል አልነበረም፡፡ በወሬው አልፎ አልፎ የጄኔራሎች፣ የኮሎኔሎችና የዳኞችን ስም ጣል ጣል አድርጎ፣ ራሱን የሁሉ በላይ አስመስሎ፣ ሳያፍር ተናገረ፡፡ ጓደኞቹ በመደነቅ ሳቁ፡፡ ፌርፌችኪን አናፋ፡፡ የኔ መፈጠር ተረስቶ ተዋርጄና ተረግጬ በዝምታ ተቀመጥኩ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

«አምላክ ሆይ! በውኑ ይህ የኔ ቦታ ነውን? » ስል አሰብኩ:: «እንዴት ራሴን ከፊታቸው አራከስኩ ! ፊርፊችኪን እንኳን እንዲጨማለቅብኝ ልፍቀድለት? ! እነዚህ በድንራሶች ከነርሱ ጋር ራት እንድበላ ስለፈቀዱ የዋሉልኝ መስሏቸዋል፤ ያከበርኳቸው እኔ መሆኔ አይገባቸውም:: 'እንዴት ከስተሃል? ' አለኝ እዝቬርኮቭ:: ሱሪዬ ነው ጉድ የሠራኝ! ከሱሪዬ ላይ ያለውን ቢጫ ነገር አይቶታል:: እዚህ ምንድነው የምሠራው? አሁኑኑ ተነስቼ መውጣት አለብኝ:: አሁኑኑ! ያላንዳች ቃል . . . በንቀት! ነገ ታዲያ የፈለገው ይምጣ፤ ፍልሚያም ቢሆን! ወርበሎች! ስለሰባት ብሩስ መጨነቅ ይኖርብኛል? ሌላ ነገር ቢያስቡስ? የራሳቸው ጉዳይ! ሰባት ብሬን ባጣ ግዴለኝም:: አሁኑኑ እሄዳለሁ! . . .»

ንቅንቅ አላልኩም:: ውስጤ ከመብገኑ የተነሳ መጠጡን እያነሳሁ ጨለጥኩት:: አልኮል ስላልለመድኩ ወዲያው ስካር ጀመረኝ:: ስካሬ ሲበረታ ብስጭቴ ገደብ ማሰ:: እጅግ ፀያፍ በሆነ መንገድ ዘልፌያቸው ለመሄድ ጓጓሁ፤ ጥሩ ወቅት ጠብቄ ማንነቴን ላሳያቸው:: መሣቂያ ነህ ቢሉኝም እሳትነቴን ይረዱታል:: እንዲያውም . . . ባጭሩ ገደል ይገቡ::

በመጠጥ የቦዙ ዓይኖቼን በዕብሪት እያንከባለልኩ ተራ በተራ ተመለከትኳቸው:: መኖሬን የረሱ ይመስላሉ:: ያወካሉ፣ ይስቃሉ፣ ይፈነድቃሉ:: እዝቬርኮቭ የወሬው ንጉሥ ሆኗል:: ማዳመጥ ጀመርኩ:: ስለአንዲት ቆንጆ ሴት ነበር የሚያወራላቸው:: ማፍቀሯን ገልጣ እስከምትናዘዝለት ድረስ እንዴት እንደገፋፋትና በዚህም ጉዳይ አንድ ኮሊያ የተባለ ባለሦስት መቶ ገበር ሃብታም ጓደኛው እንዴት እንደረዳው:: አይኑን በጨው አጥቦ ሲወሻክት::

t.me/OLDBOOKSPDF

«እና ይህ ባለሦስት መቶ ገባር ጓደኛህ ኮሊያ እዚህ ከኛ ጋር መጥቶ ሊሸኝህ አልፈለገም?» ብዬ አቋረጥኩት:: ለጥቂት ሴኮንዶች ሁሉም ፀጥ አሉ::

«ሰክረሃል!» አለኝ ትሩዶሊቦቭ:: መኖሬን ድንገት ልብ ብሏል:: እዝቬርኮቭ ቁጫጭ የሆንኩ ይመስል ግንባሩን ከስክሶ አትኩሮ አስተዋለኝ:: ዓይኖቼን ሰበርኩ:: ሲሞኖቭ ጠርሙሱን ብድግ አድርጎ ከሁሉም ብርጭቆ ሻምፔኝ መቅዳት ጀመረ:: ትሪዶሊቦቭ ብርጭቆውን ሲያነሳ ከኔ በቀር ሁሉም ተከተሉት:: «ለጤናህ፣ መንገዱን ቀና ያድርግልህ! » አለው እዝቬርኮቭን:: ከዚያም ከሌሎቹ ጋር ብርጭቆውን እያጋጨ « ለድሮውና ለወደፊቱ!» ብሎ መጠጡን ጨለጠው:: ሁሉም ሻምፔኛቸውን ጨልጠው እዝቬርኮቭን ሊስሙት ተሽቀዳደሙ:: እኔ ግን ንቅንቅ አላልኩም:: ብርጭቆዬ እንደሞላ ከፊቴ ተቀምጧል::

«አንተስ አትጠጣም? » ሲል አጓራብኝ ትሪዶሊቦቭ ትዕግሥቱን አውልቆ::

«እኔም የራሴን ንግግር ማሰማት እፈልጋለሁ . . . ከዚያም እጠጣለሁ፣ አቶ ትሪዶሊቦቭ::»

«ርጉም ዲቃላ ! » አጉተመተመ ሲሞኖቭ:: የምናገረውን ባላስበውም፣ እየተብረከረኩ ከወንበሬ ብድግ ብዬ፣ ብርጭቆዬን አነሳሁ::

« ፀጥታ! » ብሎ ጮኸ ፌርፊችኪን:: « ድንቅ ንግግር ልንሰማ ነው:: » እዝቬርኮቭ የነገሮችን አቅጣጫ አውቆ በስጋት ተውጧል::

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሌተና ኮሎኔል እዝቬርኮቭ፣ » ብዬ ጀመርኩ ንግግሬን። «ጥራዝ ነጠቅ ቃላትን፣ ንግግር የሚቀሽሩ ሰዎችንና የተጎነተሉ ሽንጦችን እንደማልወድ ልታውቅልኝ እሻለሁ . . . ይህ የመጀመሪያው ነጥቤ ነው። ወደ ሁለተኛው እንቀጥል፡-»

ሁሉም በጭንቀት ተቁነጠነጡ።

«ሁለተኛው ነጥቤ ደግሞ፡- ዝቃጭ ነገርን ዝቃጭ የሚወዱ ሰዎችን እጠላለሁ፤ በተለይም ዝቃጭ የሚወዱ ሰዎችን! ሦስተኛው ነጥብ፡- እውነትን፣ ቅንነትን፣ ሐቀኛነትን እወዳለሁ » አልኩኝ በፍጥነት። ይህን የመሠለ ነገር እንዴት ካፌ እንደወጣ ስላላወቅኩት አካሌ እንደድንጋይ ቀዝቅዞ ነበር። «አዎ፣ መልካም ሃሳቦችን እወዳለሁ፣ ጌታው እዝቬርኮቭ፣ በእኩልነት የተመሠረተ እውነተኛ ጓደኝነት እወዳለሁ። በእኩልነት እንጂ በ . . . ህም . . . እወዳለሁ . . . ግን ምን ቸገረኝ። ለጤንነትህ እኔም እጠጣለሁ፣ ጌታው እዝቬርኮቭ። አይዞህ፣ ያው የሩቅ አገር ቆንጃጆቹን ማርካቸው፣ የአገራችንን ጠላቶች ዘርራቸው፣ እና . . . እንዲሁም . . . ለጤናህ ጌታው እዝቬርኮቭ! »

እዝቬርኮቭ ከወንበሩ ተነስቶ እጅ ነሳኝና፡-

« እጅግ አመሠግናለሁ » አለኝ። ከንዴት ብዛት ፊቱ አመድ መስሏል።

«እንዲህ ነው እንጂ! » ብሎ ትሩዶሊቦቭ ጠረጴዛውን በጭብጡ ወገረው።

«አሄ! ይህን ቀባጥሮ መንጋጋ ላይ ቡጢ መቅመስ የት ይቀራል?» አለ ፌርፌችኪን።

t.me/OLDBOOKSPDF

«በርግጫ ተነርቶ መውጣት አለበት» ሲል አጉተመተመ ሲሞኖቭ::

«ምንም አያስፈልግም:: አርፋችሁ ተቀመጡ! » አለ እዝቬርኮቭ የጓደኞቹን ቁጣ እያለሳለሰ:: «ሁላችሁንም አመሠግናለሁ፤ ግን እኔ ራሴ ለሱ ንግግር የሚሰጠውን ዋጋ ሳሳየው እበቃለሁ::»

«አቶ ፌርፊችኪን፣ አሁን ለተናገርከው ነገ ትመልስልኛለህ! » አልኩ በአርምሞ ድምፄን ከፍ አድርጌ::

«ፍልሚያ ማለትህ ነው? ምን ገዶኝ » ሲል መለሠልኝ:: እሱን ለፍልሚያ መጋበዜ ከጠቅላላ ሁኔታዬ ጋር ስላልተጣጣመ ሁሉም በሣቅ ፈረሱ:: ፌርፊችኪንም ተጨምሮ ተንከተከተ::

«አዩት እስቲ! ጥምብዝ ብሎ ሰክሯል:: ወዲያ ብናባርረው ይሻላል » አለ ትሪዶሊቦቭ በመጠየፍ::

አሁን ነው በጠርሙስ የአንዱን ጭንቅላት መተርከክ ያለብኝ ብዬ አሰብኩና፣ ጠርሙስ አፈፍ አድርጌ . . . ብርጭቆዬን ሞላሁ::

አዎ:: እስተመጨረሻው ብቀመጥ ይሻላል ብዬ ወሰንኩ:: ብሄድ በደስታ እንደምትፈነጩ አውቃለሁ:: እኔ ግን በጭራሽ አልነቃነቅም:: እንዲሁ ለክፋት እዚሁ ቁጭ ብዬ እየጠጣሁ እስከፍፃሜው እቆያለሁ:: ቦታ እንደማልሰጣችሁ አሳያችኋለሁ:: እቀመጣለሁ፣ እጠጣለሁ፤ ምክንያቱም ይህ የመጠጥ ቤት ነው፤ የራሴንም ሂሳብ ከፍያለሁ:: አዎ አልሄድም፣ እጠጣለሁ . . . ካሻኝም እዘፍናለሁ:: እንዴታ . . . ደስ ካለኝ ለምን አልዘፍን? ምክንያቱም ለመዝፈን መብት አለኝ . . . ህም::



t.me/OLDBOOKSPDF

ግን አልዘፈንኩም:: እንዳቸውንም ላለማየት እየሞከርኩ፣ ነገሩ ሁሉ ግድ ያልሰጠኝ መስዬ፣ ቀድመው እስኪያናግሩኝ በጉጉት መጠበቅ ጀመርኩ:: ይሁንና አላነጋገሩኝም:: ልታረቃቸው ፈለግኩ:: የግድግዳው ሰዓት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት፣ ከዚያም ሦስት ሰዓት ደወለ:: ጠረጴዛውን ለቅቀው ወደ ሶፋው ሄዱ:: እዝቬርኮቭ ከሦፋው ላይ ተንፈላሰሰ፣ አንድ እግሩን ከትንሽ ከብ ጠረጴዛ ላይ አጋደመ:: የወይን ጠጅ አቅርበው እየጠጡ ጨዋታቸውን ቀጠሉ:: ፌርፌችኪን እንደተመኘው፣ ተጋባዡ እዝቬርኮቭ መጠጥ ገዝቶ ጨምሮ ነበር:: እኔ እንድቀላቀላቸው አልጋበዙኝም:: ጓደኞቼ ከሶፋው ላይ በሱ ዙሪያ ተኮለኮሉ:: አፋቸውን ከፍተው ሲያዳምጡት እጅግ እንደሚወዱት ግልፅ ነበር:: «ለምን? ለምን? » ስል ራሴን ጠየቅኩት:: አልፎ አልፎ በስካር ሐሴት እየተነሱ ይተቃቀፋሉ፣ ይሳሳማሉ:: ስለእውነተኛ ፍቅር፣ ያኔ አዲስ ስለነበረው የካርታ ጨዋታና ጥሩ ደሞዝ ስለሚያስከፍሉ ሥራዎች አወሩ:: እንዳቸውም አግኝተውት የማያውቁት ፓድካርዤቭስኪ ስለተባለ ባለሥልጣን የዓመት ገቢ አንሥተው በመብዛቱ ሲደሰቱ፤ እንዳቸውም ያላዩዋት ልዕልት ዳሪያ የተባለች ሴትን ውበትና ግርማ ሲያደንቁና፤ ከዚያም ሼክስፒር ሕያው ነው ከሚል ውሳኔ ላይ ሲደርሱ እኔ የምፀት ፈገግታ ከፊቴ ላይ ለጥፌ፣ ከተቀመጡበት ሶፋ ፊት ለፊት በግድግዳው ጥግ ከጠረጴዛው ወደ ምድጃው እየተመላለስኩ እንጎራደድ ነበር::

ያለእነሱ አንዳች እንደማይጎድልብኝ ላሳያቸው እየጣርኩ፣ ሲታወቀኝ ወለሉን በተረከዜ እወግረው ጀመር:: ምንም አልፈጠርኩም:: የሌለሁ አስመስለው ወሬያቸውን ቀጠሉ:: የለከፈኝ ነገር ከውስጤ ተሰራጭቶ በግድግዳው አጠገብ ከፊታቸው ከሁለት ሰዓት ጀምሮ እስከአምስት ሰዓት ድረስ ከጠረጴዛው ወደምድጃው ሳልሰለች እንድመላለስ አስቻለኝ:: « በበኩሌ የምንጎራደደው እግሬን ለማፍታታት ነው:: ይህን ደግሞ ማንም ሊከለክለኝ አይችልም:: »



t.me/OLDBOOKSPDF

እልፎ እልፎ ወደክፍሉ የሚገባው አስተናጋጅ ሥራውን ትቶ በመገረም ያየኝ ነበር:: ከመመላለስ ብዛት ጭንቅላቴ ዞረብኝ:: አንዳንዴ ቅዠት ውስጥ ያለሁ ይመስለኛል:: ላብ ያጠምቀኝና በገዛ እጁ ይደርቃል:: አሥር ዓመታት፣ ወይም ሃያ፣ ወይም አርባ ዓመታት እንኳን አልፈው ነፍሴን የውርደት አተላ የጋትኩበትን ይህን ርጉም ሰዓት ሃፍረት እየወረሰኝ እንደማስታውሰው እየቆየ ሲሰማኝ፣ ልቤን በስለት የወጉት ያህል ያመኛል:: ራሱን በፈቃዱ ይህን ከመሠለ ይቅርታ ከማይገባው ቅሌት ውስጥ የሚከት ሰው እንደሌለ እያወቅኩት፣ ከምድጃው ወደ ጠረጴዛው መንቆራጠጤን ቀጠልኩ::

«እነዚህ እንስሶች ምን የመሣሠሉ ሃሳቦችና ስሜቶች በውስጤ መኖራቸውን ቢያውቁ ኖሮ » እያልኩ አስብ ነበር፣ ጠላቶቼ የተቀመጡበትን ሶፋ እያስተዋልኩ:: እነርሱ ግን የኔን መኖር ዘንግተዋል:: አንዴ ብቻ እዝቬርኮቭ ስለሺክስፒር ሲያወራ ሰምቼው የማንጓጠጥ ሳቅ ስስቅ ሁሉም ተመለከቱኝ:: አሳሳቄ፣ ሲታወቀኝ ያደረግኩት የከፋትና የአትርሱኝ ባይነቴ ሲቃ ስለነበር፣ ወሬያቸውን አቁመው፣ በጥላቻ ለአንድ ደቂቃ ያህል ሲያዩኝ፣ እኔ በቸልታ ከምድጃው ወደ ጠረጴዛው እንጎራደድ ቀጠልኩ:: ያም ምንም አላመጣም:: አንዳቸውም አልተናገሩኝም:: መልሰው ረሱኝ:: አምስት ሰዓት ሞላ::

«አሁኑኑ እዚያ መሄድ አለብን! » አለ እዝቬርኮቭ ከሶፋው ብድግ ብሎ::

«አዎ እንሂድ » ብለው ተስማሙ ሁሉም:: ያኔ ነበር በድንገት ከእዝቬርኮቭ ፊት ሄጄ ተጋረጥኩት:: ታክቼ፣ ሆድ ብሶኝ ስለነበር ለሥቃዩ ፍፃሜ ካመጣልኝ ምንም ነገር ባደርግ አይገደኝም



t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር፣ ራሴን መስቀል እንኳን ቢሆን! ሰውነቴ ይብረከረካል:: በላብ የራሰው ፀጉሬ ከቅንጨና ከግንባሬ ተለጥፏል::

«እዝቤርኮቭ! ይቅርታ እለምናለሁኝ! » አልኩት አምርሬ፣ በድፍረት::

«ፌርፌችኪን፣ አንተም ይቅር በለኝ:: ሁላችሁም:: ሁላችሁንም ስለዘለፍኳችሁ ይቅርታ::»

«አሂሂሂ . . . ፍልሚያ ቀልድ አይደለም! » አለኝ ፌርፌችኪን እሳት ጎርሶ:: ቃላቱ ልቤን እንደጅራፍ ገረፋት::

«ፍልሚያውን ፈርቼ አይምሠልህ ፌርፌችኪን! አሁን ታረቁኝ እንጂ ነገ ለመፋለም ዝግጁ ነኝ:: አንተም ብትሆን ነገ ከፍልሚያው ማምለጥ አትችልም:: ያንን እንደማልፈራ ታያለህ:: እንዲያውም አንተ መጀመሪያ ትተኩስና እኔ ወደ ሰማይ እተኩሳለሁ:: »

« በራሱ እየቀለደ ነው » አለ ሲሞኖቭ::

« አሁንስ ለይቶለታል » አለ ትሩዶሊቦቭ::

« እንለፍበት መንገድ ልቀቅ! ምንድነው ከኛ የምትፈልገው? » ብሎ አከላፈተኝ እዝቬርኮቭ:: ሁሉም ፊታቸው ቲማቲም መስሏል:: የዓይናቸው ብርሃን እስኪደበዝዝ ጥፉ አድርገው ቀምቅመዋል::

« ጓደኝነትህን እሻለሁ እዝቬርኮቭ:: አዎ ደፍሬሃለሁ:: ግን . . . »



t.me/OLDBOOKSPDF

« ደፈርኩህ? እኔን ደፈርከኝ?! አንተ እኔን በምንም ዓይነት ሁኔታ ልትደፍረኝ አትችልም! »

« እንግዲህ ይብቃህ ወንድም! ወዲያ ዞር በል እንሂድበት! » አለኝ ትሩዶሊቦቭ ቁርጥ አድርጎ::

« አሊምፒያ የኔ ናት፣ በዚህ እንስማማ! » አለ እዝቬርኮቭ::

« ይሁንልህ » አሉት እየሳቁ::

ተረግጬ፣ ተተፍቶብኝ፣ ቆሜ ቀረሁ:: ከሆቴሉ እንደወጡ ትሩዶሊቦቭ መደዴ ዘፈን ማንጎራጎር ጀመረ:: ለአስተናጋጁ ጉርሻ ሊሰጥ ሲሞኖቭ ወደኋላ ቀርቶ ስለነበር መሰስ ብዬ ተጠጋሁት::

« ሲሞኖቭ! ስድስት ብር ስጠኝ » ብዬ ጠየቅኩት ተስፋቢስነት የሰጠኝን ድፍረት አጥልቄ::

የሰማውን ማመን አቅቶት በዝምታ አስተዋለኝ::

« እኛ ጋር መሄድ አስበህ እንዳይሆን! »

« አዎ፣ ከናንተ ጋር መምጣቴ ነው! »

« በል ይቅርታህን፣ ምንም ገንዘብ የለኝም » አለኝና በመጠየፍ ወደበሩ ሲያመራ ተንደርድሬ ካፖርቱን ጨመደድኩ:: የማልጋፋው ቅዠት ውስጥ ነበርኩ::

t.me/OLDBOOKSPDF

« ሲሞኖቭ! ገንዘብ እንዳለህ አይቻለሁ:: ለምን ትነፍገኛለህ? ከወሮበላ ቆጥረኸኝ ነው? ባትከለክለኝ ይሻላል:: ለምን እንደምጠይቅህ አታውቅም:: ካልሰጠኸኝ ብዙ ነገሮች ይበላሹብኛል:- እቅዴ፣ ለወደፊት ያሰብኩት ሁሉ . . . »

ሲሞኖቭ ብሩን ከኪሱ አውጥቶ ወረወረው::

« ይህን ያህል እፍረትህን ከሸጥክ ያውልህ ውሰደው! » ብሎ ጓደኞቹ ጋር ለመድረስ ተቻኩሎ ወጣ::

ለቅፅበት ብቻዬን ቀረሁ:: ክፍሉ ተተራምሷል:: የምግብ ትርፍራፊ፣ የተሰበረ ብርጭቆ፣ የፈሳሰሰ የወይን ጠጅ፣ የሲጋራ እላቂዎች፤ የሥካር ትርምሥ ከጭንቅላቴ ውስጥ፣ ሰቆቃ በልቤ ሙሉ፤ ሁሉንም አይቶና ሰምቶ በመገረም የሚያየኝ አስተናጋጅ::

« መሄድ አለብኝ! » ስል ወሰንኩ:: « ተንበርክከው ጓደኛቸው እንድሆን ይማፀኑኛል፤ ወይም . . . እዝቬርኮቭን በጥፊ እልሰዋለሁ! »



« አዎ እንግዲህ ይኸው ነው:: ሕይወት በአካል ከፊቴ ቆማለች፤ በቅዠት ዓለሜ ውስጥ የማያት፣ ሰላምና ፍቅር የሠፈነባት ስሙር ሕይወት አይደለችም » አልኩ በደረጃው ቁልቁል እየተንደረደርኩ::

t.me/OLDBOOKSPDF

«ምንም እንኳን አሁን ባይመስልህም ባለጌ ሰው መሆንህን እወቀው » አለኝ አእምሮዬ:: « ብሆንስ? » ስል መለስኩ:: « አሁን ሁሉም ያለቀለት ነገር ነው! :: »

ከሆቴሉ እንደወጣሁ ላያቸው አልቻልኩም:: የሚሄዱበትን ስለማውቀው ግን አልገደደኝም:: ከፓሪስ ሆቴል መግቢያ ላይ አንድ ጋሪ ነጂ ጆንያ በመሠለ ካፖርት ተጠቅልሎ፣ የሠፈረበት በረዶ ዱቄት የወረሰው አስመስሎት ቆሟል:: አየሩ እርጥበት አርግዞ ይጨሳል:: የባለጋሪው ከሳሳ ፈረስም እንደጌታዋ በረዶ ለብሳ ትስላለች:: ይህ ሁሉ ቁልጭ ብሎ ይታወሰኛል:: ወደ ከርካሳው ጋሪ ገሥግሼ፣ ልሳፈር እግሬን ሳነሳ፣ ሲሞኖቭ እንዴት አድርጎ ብሩን እንደወረወረው ትዝ ብሎኝ፣ እንደ ግዙፍ ሸክም ከመቀመጫው ላይ ተዘፈዘፍኩ::

«ወይኔ! » ይህን ሁሉ ጉድ ለመፋቅ ማድረግ ያለብኝ ብዙ ነገር አለ! :: የዛሬውን ውርደቴን እንደምንም ብዬ ካላፀዳሁ እሞታታለሁ! »ብዬ አሰብኩ::

« ንዳው ሰውዬ! » ጮኽኩበት በባለጋሪው::

« ጭንቅላቴ እያወካብኝ ጉዞ ጀመርን:: ተንበርክከው እርቅና ጓደኝነት አይለምኑኝም:: ያ ከንቱ ምኞት ነው፤ ርካሽ ቅዠት፣ እብደት:: ስለዚህ አዝቬርኮቭን በጥፊ ማቅመስ አለብኝ፤ ግዴታዬ ነው፤ የማይቀር ጉዳይ !

t.me/OLDBOOKSPDF

ጋሪ ነጂው ልጓሙን አራገበው::

እንደደረስኩ በጥፌ እመታዋለሁ:: ከዚያ በፊት ግን ለመግቢያ ያህል ጥቂት ቃላት መሰንዘር ይገባኝ ይሆን? . . . አይ፣ ንግግር አያስፈልግም:: ዝም ብዬ ሄጄ ፊቱን በጥፌ ማጮህ! ከሳሎኑ ተቀምጠው አገኛቸዋለሁ! እዝቤርኮቭም ከሶፋው ላይ ከአሊምፒያ ጋር ሲንፈላሰስ:: ያቺ አሊምፒያ! አንድ ቀን ስቃብኝ አልፈልግህም ብላኛለች እኮ:: እሷን በፀጉሯ እየጎተትኩ የእዝቤርኮቭን ጆሮ አልመዘምዝለታለሁ:: እንዲያውም ጆሮውን ከመቆንጠጥ ይልቅ ይዤ ወዲያ ወዲህ ብጎትተው ይሻላል:: ይህን ሳደርግ ጓደኞቼ ተረባርበው ይወግሩኝና ከቤቱ ወርውረው ያስወጡኛል:: ያንን እንደሚያደርጉ አልጠራጠርም:: ይበሉኝ! ቀድሞ ዱላ ሰንዛሪው እኔው ነኝ:: የድብድብ ግብዣው ከእኔ መምጣቱ ክብሬን ይጠብቅልኛል:: ቢደበድቡኝም እንኳን እዝቤርኮቭን የማለብሰውን የውርደት ማቅ ሊያወልቁለት አይችሉም:: የጥፌ ቅሌት የሚፋቀው በፍልሚያ ብቻ ነው:: ሊፋለመኝ ይገደዳል:: ይበሉኝ! ይደብድቡኝ! ስለክብርና ስለታላቅነት ምን ሲያውቁ! ትሩዶሊቦቭ አክርሮ ይነርተኛል:: እሱ ከሁሉም ያይላል:: ፌርፊችኪን ከጓላዬ ሾከክ ብሎ ነው ፀጉሬን የሚነጨው:: ያሻቸውን ያድርጉኝ፣ አልፈራም! በመጨረሻ የነገሩን ሁሉ አሳዛኝነት በበግ እንንላቸው ይረዱታል::



t.me/OLDBOOKSPDF

እየጎተቱ ሲያስወጡኝ ከትንሽ ጣቴ ያነሱ መሆናቸውን እነግራቸዋለሁ::

«ፍጠን ባለጋሪ፣ ፍጠን ! » ብዬ ጋሪ ነጂው ላይ እጓራሁበት:: ደንግጦ ጅራፉን አጮኸው::

በማለዳ እንፋለማለን፤ ያ የማይቀር ነው:: የስራዬ ነገር ገደል ገባ ማለት ነው:: ግን ከወዴት ነው ሽጉጥ የማገኘው? ህም . . . ምን ችግር አለ? ከደሞዜ ብድር ወስጄ እገዛዋለኋ:: ጥይቱስ? ያ የኔ ችግር አይደለም:: አጃቢዬ ይጨነቅበት:: ይህን ሁሉ ታዲያ እንዴት አድርጌ ነው ከነገ ጧት በፊት የማዘጋጀው? አጃቢስ ማን ይሆነኛል? ያን ያህል የማውቀው ሰው የለኝ:: ከንቱ ጭንቀት! አንዱን ከመንገድ የማገኘውን ሰው እጠይቀዋለሁ:: ውሃ የሚወስደውን ሰው ለማዳን ወደኋላ የማይል ሰው ከሆነ፣ እምቢ አይለኝም:: የማይታሰበውን ሁሉ ማሰብ አለብኝ:: ዲሬክተራችንን አንቶንን እንኳን ብጠይቀው ለክብሩ ሲል እሺ ይለኛል:: ኋላም ገበናዬን ይደብቃል::

በእውነቱ ግን በዚህ ሰዓት የሃሳቤን ተስፋቢስ ከንቱነትና መሣቂያነት፣ ባጠቃላይ ከቅዠቴ ባሻገር የነበረውን ጭራሽ ሌላ ዓይነት ፍፃሜ ከማንም የበለጠ ራሴ አጥርቼ አውቀው ነበር:: ይሁንና . . .

«ፍጠን ባለጋሪ ! ንዳው እንጂ አንት አመዳም ! »

«ምነው ጌታዬ » አለኝ ፊቱን ከርችም አድርጎ::

t.me/OLDBOOKSPDF

« ብርድ ተሰማኝ:: ቀጥ ብዬ . . . ነቤቴ ብሄድ . . . አይሻልም? አንተ እግዚአብሔር! ምን ነክቶኝ ነው ለዛሬው ራት ራሴን የጋበዝኩት? አይ! መመለሴ አይታሰብም! በጠረጴዛውና በምድጃው መሃል ለሦስት ሰዓት የተንቆራጠጥኩትስ? በጭራሽ! እነሱ እንጂ ሌላ ማንም ለዚያ ሥቃዬ መክፈል ያለበት የለም::

«ብረር ባለጋሪ ! »

ከፖሊስ ጣቢያ ቢወስዱኝስ? እሱን እንኳን አይሞክሩትም:: ወሬውን ይፈሩታል:: አዝቤርኮቭ በንቀት የፍልሚያ ግብዣዬን ባይቀበልስ? እንደማይስማማ አውቃለሁ:: እምቢ ካለ ግን አሳያቸዋለሁ:: ነገ ጧት ሊሳፈር ሲል ሮጬ እግሩ ላይ እጠመጠምና ካፖርቱን አወልቅበታለሁ:: ከዚያም ጥርሶቹን እጁ ላይ ሰግስጌ እነክሰዋለሁ:: « እያችሁ መድረሻ ማጣት ሰውን ከምን እንደሚያደርሰው! » ብዬ እጮሃለሁ:: ከዚያ ቢፈልግ ራሴን እንደእባብ ይቀጥቅጥ:: ጓደኞቹም ከኋላ፣ ከፊት ይጠልዙኝ ! «ተመልከቱት ይህን ጥጃ፣ የሩቅ መንደር ቆነጃጅትን ሊማርክ ሲሄድ ለሃጩን ከፊቱ ላይ ለጥፎ ! » ብዬ ለህዝብ እለፍፋለሁ::

ከዚያ ወዲያ ሁሉ ነገር ያከትማል ! እያዝና ለፍርድ እቀርባለሁ:: ከሥራዬ ተባርሬ ወኅኒ ቤት እገባለሁ:: ምንም አይደል:: ከአሥራ አምስት ዓመታት በኋላ ስፈታ፣ ተጎሳቁዬና ደህይቼ፣ አዝቤርኮቭን ፍለጋ እንከራተታለሁ:: እሱም ያኔ አግብቶ፣ ከሚስቱና ከደረሰች ሴት ልጁ ጋር ከሆነ የክፍለሃገር ከተማ ይኖራል::

t.me/OLDBOOKSPDF

«ተመልከተኝ አንተ እንስሳ ! አፅም የመሠለ ፊቴንና ድሪቶዬን ተመልከት! ሁሉን አጥቻለሁ፡- ስራዬን፣ ደስታዬን፣ ስነጥበብን፣ ሳይንስን፣ የማፈቅራትን ሴት፤ ሁሉንም ባንተ የተነሳ፡፡ ሽጉጤም ይኸው፡፡ የመጣሁት ሽጉጤን ተኩሼ . . . ይቅር ልልህ ነው» ብዬ ወደ ሰማይ አተኩስና፣ መድረሻዬ ላይገኝ እልም ብዬ እጠፋለሁ፡፡

ይህን ሁሉ የለቀምኩት ካነበብኩት መፅሐፍ መሆኑን ሳውቀው፣ ለራሴ አዝኜ የእንባ ዘለላዎች በጉንጮቼ ላይ ኮለል አሉ፡፡ ወዲያው የሚዘገንን የእፍረት ማዕበል ትንፋሼን ሲያሳጥረው ጋሪውን አስቁሜ ከመንገድ መሃል ከተቆለለው የበረዶ ክምር ገባሁበት፡፡ ባለጋሪው በመገረም አየኝና በረጅሙ ተነፈሠ፡

«ምን ላድርግ? እንዳልሄድ፣ ቅሌቱን ፈራሁት፤ እንዳልቀር ደግሞ . . .»

«ኧረ በጭራሽ ! እንዴት እንዲሁ እተወዋለሁ! ? እንደዚያ ተዋርጄ? » አልኩና ከጋሪው ላይ ዘልዬ ተሳፈርኩ፡፡ «ያለቀ ነገር ነው፣ የደቀቀ፡፡ ንዳው ሰውዬ! ፍጠን እንጂ! » ከመቻኮሌና ትንፋሽ ከማጣቴ ብዛት ባለጋሪውን አንገቱ ላይ በቡጢ አልኩት፡፡

«ምን ነካዎት?! ለምን ይመቱኛል? » አለኝ ባለጋሪው ደንግጦ፣ ፈርቶኝ፡፡ ያም ሆኖ ፈረሱ በኋላት እርግጫ እስኪትፈናጠር ድረስ በጅራፉ ገረፋት፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ርጥቡ በረዶ ከሠማይ ይረግፋል፡፡ እኔ ግን ምንም ሳይመስለኝ የካፖርቴን ቁልፎች ከፈትኳቸው፡፡ እዝቬርኮቭን በጥፊ እንደምለው አምርሬ ስለወሰንኩ፤ የሁሉን ነገር ለፍፃሜ መቃረብ በፍርሃት ተገንዝቤ ከመሆን የሚገታው ነገር እንደሌለ ስላወቅኩ፤ ሌላውን ነገር ሁሉ ችላ ብየዋለሁ፡፡ በጨፍጋጋው የበረዶ ዝናብ ተውጠው አልፎ አልፎ ብልጭ እልም የሚሉት የመንገድ መብራቶች፣ የምሽት ቀብር ላይ የሚያበሯቸውን ጧፎች ይመስላሉ፡፡ በረዶ በካፖርቴ፣ በኮቴና በክራባቴ ሥር ተሠግሥጎ ከገላዬ ላይ ሲቀልጥ ራሴን ለመሸፈን አልሞከርኩም፡፡

ደረስን፡፡ ከጋሪው ዱብ ብዬ፣ በፍጥነት ሮጬ ደረጃውን ወጣሁና በሩን በጭብጥና በእግሬ መውገር ጀመርኩ፡፡ ቅልጥሞቼ፣ በተለይም ጉልበቶቼ፣ ይብረከረካሉ፡፡ መምጣቴን ሲጠብቁ እንደነበሩ ሁሉ በሩ ወዲያው ተከፈተ፡፡ ቤቱ እንደዛሬ ፖሊስ ሳይዘጋው፣ በዚያን ጊዜ ከነበሩት ዕውቅ ሥፍራዎች አንዱ ነበር፡፡ ቀን ቀን በሱቅነት ያገለግልና፣ ሲመሻሽ ምንነታቸው በውል የታወቁ ሰዎች ይጎበኙታል፡፡ ለጥንቃቄ ሲባል ቤቱን የሚጎበኙ ሰዎች በቅድሚያ መታወቅ ነበረባቸው፡፡ ያ ሲሞኖቭ ልመጣ እንደምችል ነግሯቸው ይሆናል፣ እኔን በቀጥታ አሳለፉኝ፡፡ በጨለማው ክፍል አልፌ አንዲት ሻማ ብቻዋን ከምትበራበት ሳሎን ጥልቅ ብዬ፣ ግራ ተጋብቼ ቆሜ ቀረሁ፡፡ ማንም አልነበረም፡፡

«የት ሄዱ? » ስል ጠየቅኩ፡፡ ለካስ ሁሉም በየፊናቸው ተበታትነዋል፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደነገሩ የምታውቀኝ የቤቱ እመቤት በለዛቢስ ፈገግታ ጥርሶቿን ገለጥ አድርጋ ከፊቴ ቆማለች:: ወዲያው እንደኛው በር ተከፈተና ሌላ ሴት ገባች::

ሁሉን ነገር ረስቼ ከራሴ ጋር እየተነጋገርኩ ወዲያ ወዲህ እል ጀመር:: ከሞት ያተረፉት ሰው አመሥል ነበር:: ደስታ አጥለቅልቆኛል:: ባገኛቸው ኖሮ እዝቤርኮቭን በጥፊ አቀምሠው ነበር:: አሁን ግን እንዳቸውም የሉም . . . ስለዚህ ጉዱ እንደጉም ተነነ . . . ጥቁሩ ደመና ከፊቴ ገለል አለ . . . አካባቢዬን ቃኘሁት:: ገና ምኑም አልተጨበጠልኝም:: እንዲያው ለነገሩ ቅድም ድምጿን አጥፍታ የገባችውን ልጅ ተመለከትኳት:: ፊቷ ለዛው ያልተነካ፣ የልጅ ፊት ነበር:: ቀጥ ያሉ ጥቁር ቅንድቦቿንና የሰከኑ ዓይኖቿን አይቼ ወደድኳት:: ፈገግታ ብትሞክር ኖሮ እጠላት ነበር:: ካልተረጋጋው አእምሮዬ ጋር እየታገልኩ ጠጋ ብዬ መረመርኳት:: ከፊቷ ኮስታራነት ሥር ደግነቷና ቅንነቷ ይነበባል:: ፈገግታቢስነቷና ርጋታዋ ከሥራዋ ጋር እንደማይጣጣም ግልፅ ነበር:: እነኚያ ወንበዴዎችም ያልፈቀዷት በዚሁ በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም:: ቁመቷ ዘለግ ያለ፣ ቅርጿ ያማረና ሞላ ያለች ብትሆንም ቅሉ ቆንጆ የሚሏት አይደለችም:: አለባበሷ በልኩ ነበር:: ከውስጤ መናጢ ነገር ተፍለከለከና መሠሥ ብዬ ተጠጋኋት::

አጠገቧ ስደርስ ፊቴን በመስታወቱ አየሁት:: ሠቆቃ የጨፈረበት ፊቴ እጅጉን አስቀያሚ መሠለኝ፣ ግርጣታም፣ የከይሲ ፊት:: ፀጉሬ ተተረማምሷል:: ግድ የለም:: እንኳንም ማስጠሉ ሆንኩ! ከሷ ፊት በአስቀያሚነት መቆሜ ደስ ብሎኛል . . .



t.me/OLDBOOKSPDF

ከመጋረጃው በስተኋላ የነበረው የግድግዳ ሰዓት ግዙፍ ጓዝ የተጫነው ይመስል ሲንጣረር በገሚስ እንቅልፍ መሃይ ሠመመን ካሸለብኩበት ነቃሁ:: ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ሞልቷል:: ቤቱ ጠባብና ጣራው ዝቅ ያለ ስለነበር ያስጨንቃል:: ከመካከሉ ከተገተረው ቁም ሳጥን ዙሪያ ካርቶኖች፣ ብጥስጣሽ ጨርቆችና የተለያዩ ቀለማት ያላቸው እላቂ ልብሶች ተዝረክርከዋል:: የተለከሰችው ቁራጭ ሻማ በከበባት ድቅድቅ ጨለማ ተወርሳ በራሁ፣ ጠፋሁ ትላለች:: ጥቂት ቆይታ ስትረታ ክፍሉ በፅልመት ካባ ይደፈናል::

ሁኔታዎችን ለመገንዘብ ጊዜ አልፈጀብኝም:: ሁሉም ነገር ባንዴ ታወሰኝ፤ ስነቃ ሊሠፍርብኝ በጉጉት ሲጠባበቅ የቆየ ይመስል:: እንቅልፍ ሸለብ አድርጎኝ ሳለ እንኳን ከጭንቅላቴ ውስጥ አሻፈረኝ ብሎ ህልምና ቅዠቴን የበከለ ነገር መኖሩ ይታወቀኛል::

አእምሮዬ ይዋኘር ቃል:: አንዳች ነገር ከበላዬ እየተንሳፈፈ የሚነካካኝ፣ የሚኮረኩመኝና የሚረብሸኝ ይመስለኛል:: ስቃይና ምሬት ደጋግመው ከውስጤ እየገነፈሉ መፍሠሥ ቃጣቸው:: ከዚያም፣ በመገረም የሚያጠኑኝን ሁለት ዓይኖች አየኋቸው:: እስተያየታቸው የባይተዋር ቀዝቃዛ ምንቸገረኝነት የተዋሃደው ስለነበር እስከፉኝ:: የበሠበሠና የረጣጠበ የምድር በታች ቤት ሲገባ የሚሠፍረው ዓይነት የመቅፈፍ ሥሜት አእምሮዬ ውስጥ በቀለና በመላ አካላቴ ተሠራጨ:: ለሁለት ሰዓታት ያህል ለዚች ፍጡር አንዲት ቃል ባለመተንፈሴ መደሰቴን አስታወስኩ:: አሁን ታዲያ በድንገት፣ የአመንዝራነት ክርፋቱን፣ ፀያፍነቱን፣ እውነተኛ ፍቅር



t.me/OLDBOOKSPDF

በሚቋጭበት ገቢር መጀመሩን፣ ነውረኝነቱንና ፍቅር አልባነቱን በግልፅ ተረዳሁት:: ለረጅም ጊዜ ተያየን፤ እሷ ግን ዓይኖቿን አልሠበረችም:: አስተያየቷም አልተለወጠም:: ሲበዛብኝ ሰላም አጣሁ::

«ማነው ስምሽ? » ስል ጠየቅኳት፤ መፋጠጡ ቢያቆም ብዬ::

« ሊዛ » አለች ያለድምፅ፤ በትንፋሿ:: ዓይኖቿን ከኔ መንጭቃ ወዲያ ወረወረቻቸው::

በዝምታ ጥቂት ቆየሁ::

« ምን ዓይነት ቀን ነው ዛሬ . . . በረዶ . . . መንቻካ! » አልኩኝ ለራሴ የማወራ ይመሥል፣ እጄን ተንተርሼ ጣራ ጣራውን እያስተዋልኩ::

አልመለሰችልኝም:: የተግማማ ነገር::

«የዚህ ከተማ ሰው ነሽ? » ስል ጠየቅኳት ፊቴን ወደሷ አዞሬ:: ጥያቄዬ የቆጣ ይመሥላል::

« አይ »

« ከወዴት ? »

« ከሪጋ »

t.me/OLDBOOKSPDF

« እዚሀ ብዙ ቆየሽ? »

« የት? »

«እዚሀ ቤት »

« ሁለት ሣምንት » አለችኝ አጠር፣ ቆረጥ እያረገች:: ብልጭ፣ እልም ስትል የቆየችው ሻማ ጭራሹን ድርግም አለችና የሊዛን ፊት መለየት ተሳነኝ::

« እናት አባት አሉሽ? »

« አዎ . . . አይ . . . አሉኝ »

« የት ናቸው? »

« ሪጋ »

« ምን ይሠራሉ? »

« ያው . . . »

« ያው ምን? »



t.me/OLDBOOKSPDF

« ያገር ሰዎች »

« እነርሱ ጋር ነበር የምትኖሪው? »

« አዎ »

« ዕድሜሽ ስንት ነው? »

« ሃያ »

« ከቤተሰቦችሽ ለምን ተለየሽ? »

« ዝም ብዬ . . . »

ይህ « ዝም ብዬ » አትረብሸኝ፣ ሠላም ሥጠኝ፣ ማለት ስለነበር ዝም አልኩ:: ለምን ብድግ ብዬ እንዳልወጣሁ እግዚአብሔር ያውቃል:: መከፋትና ሆድ መባሴ በረታብኝ:: የዚያን ቀን የሆነው ሁሉ ሳልፈልገው በግዛ እጁ ከአእምሮዬ ውስጥ ያወካብኝ ጀመር:: ማለዳ ከቤቴ ወጥቼ ወደሥራ ስሄድ ያየሁት ነገር ትውስ አለኝ::

«ዛሬ ጧት ከመንገድ ሰዎች የሬሳ ሳጥን ተሸክመው ሲሄዱ አምልጧቸው ሊወድቅ ነበር» አልኳት አምልጦኝ:: መናገር ፈልጌ አልነበረም::

« የሬሳ ሳጥን? »

t.me/OLDBOOKSPDF

« አዎ፣ ከሲኒማ ጎዳና ላይ:: ከምድር ቤት ነበር የወጣው:: »

« ምድር ቤት? »

« አዎ:: ከሲተኛ አዳሪ ቤት:: ከቁሻሻ መሃል . . . የምናምን ልጣጩ . . . ትርኪምርኪው . . . ክርፋቱ፣ ይዘገንን ነበር:: »

ዝምታ::

« የዛሬው ዓይነት ቀን ለቀብር አስቀያሚ ነው » አልኩ ዝምታውን ለመግፈፍ::

« ለምን? »

« በረዶው፣ ጎርፉ . . . » አልኩኝ እያዛጋሁ::

« ምን ልዩነት አለው? » አለች

« እንዴ? ቀፋፊ ነው እንጂ! » እንደገና አዛጋሁ:: « መቃብር ቆፋሪዎቹ በረዶ እያራሳቸው ሲቆፍሩ ማማረራቸው ይቀራል? ምናልባትም መቃብሩን ውሃ ሞልቶት ይሆናል »



t.me/OLDBOOKSPDF

« ውሃ ሞልቶት ይሆናል? ለምን? » ስትል ጠየቀችኝ:: አነጋገሯ የቁጣ ቢመስልም ጥያቄዋ ከልብ ነበር:: አንዳች ነገር ሲኮረኩረኝ ተሠማኝ::

« ቢያንስ አንድ ስንዝር ጥልቀት ያለው ውሃ ይኖረዋል:: ከዚያ ቦታ ደረቅ መቃብር ተቆፍሮ አያውቅም::»

« ለምን? »

« ምን ማለት ነው « ለምን? » ቦታው ረግረግና አረንቆ ብቻ ነው:: ሬሳ ከውሃ ውስጥ እየዘፈቁ ሲቀብሩ ብዙ ጊዜ አይቻለሁ:: » ( በእውነቱ ግን አላየሁም፣ እዚያ ሄጄም አላውቅ:: ሲያወሩ ብቻ ሰምቻለሁ:: )

« መሞትሽ አያሳስብሽም? »

« ለምን እሞታለሁ? » አለች

« አንድ ቀን መሞትሽ አይቀር፣ ልክ እንደዛችኛዋ:: የሣምባነቀርሳ ነው የገደላት:: ታዲያ እሷም እንዳንቺ . . . »

« ሸርሙጣ ብትሆን ኖሮ ከሆስፒታል ነበር የምትሞተው . . . » አሉኝ ሊዛ የጀመርኩትን ሳልጨርስ:: ያንን ታውቃለች:: « ሸርሙጣ » ማለቷን ልብ አልኩ::



t.me/OLDBOOKSPDF

« የእመቤቷ እዳ ነበረባት » ስል ቀጠልኩ ምልልሱ እየጣመኝ::

« የጠና በሽታ እያለባት ለትሞት አንድ ሐሙስ እስኪቀራት ድረስ ትሠራ ነበር:: የዚያ ሠፈር ጋሪ ነጂዎች ለወታደሮች ሲነግሯቸው ሰምቻለሁ:: የድሮ ደንበኞቿ ሳይሆኑ አይቀሩም:: ለትዝታዋ መሸታ ቤት ሄደው እንደሚጠጡ እየሳቁ ሲያወሩ ነበር:: » (ብዙውን ፈጥሬ ነው::)

ዝምታ:: ጥቅጥቅ ያለ ፀጥታ:: አልተንቀሳቀሰችም::

«እና ከሆስፒታል መሞት ይሻላል ብለሽ ታስቢያለሽ? »« ምን ልዩነት አለው? . . . እኔስ ለምንድነው የምሞተው? » አለች ተረብሻ::

« አሁን ባይሆን የኋላ ኋላ:: »

« ኋላ ሲሆን ይሆናል:: »

«አሁንማ ያን ማለት መች ይቸግራል:: ወጣት ነሽ፣ መልከመልካም፣ ለጋ:- ቀጋሽም በዚያው ልክ ነው:: ግን በዚህ ሕይወት ካንድ አመት በኋላ እንዲሁ የምትቆይ አይምሠልሽ:: ፀዳልሽም ይረግፋል:: »

« አንድ ዓመት? »


t.me/OLDBOOKSPDF

«ታዲያስ:: ዋጋሽ ዝቅ ይላል፣ » ስል ቀጠልኩ ከውስጤ የሚፈስሰውን የጭካኔ አረቄ እያጣጣምኩ:: « ከዚህ ወጥተሽ ረከስ ወዳለ ሌላ ቤት ትሄጃለሽ:: ሁለተኛው ዓመት ላይ ደግሞ ከዚያም ዝቅ ያለ ቤት:: በሰባት ዓመት ከሴናያ ጎዳና የምድር በታች ቤት ውስጥ ገብተሽ ታርፊዋለሽ:: ጉዱ ያ ብቻ አይደለም:: በዚያ ላይ ሥቃይ ጓዙን ጠቅልሎ የሚወርስሽ የታመምሽ እንደሆነ ነው:: በዚህ ዓይነት ኑሮ ሕመም ቀልድ አይደለም:: አንዴ ከተጣበቀብሽ አይለቅሽም:: ከዚያም ወደሞት ማዝገም ነው:: »

«ይሁና ታዲያ፣ መሞት ነዋ! » ብላ በንዴት መለሰችልኝ ትከሻዋን ነቅንቃ::

« አያሳዝንም? »

« ማነው የሚያሳዝነው? »

« ሕይወትን ማጣት » መልስ የለም::

« እጮኛ ነበረሽ? »

ኖረኝ አልኖረኝ አንተ ምን ገዶህ? »

«ምን አስቆጣሽ? እየመረመርኩሽ እኮ አይደለም:: እኔ ምንም አይገደኝ፣ በርግጥ በህይወትሽ ብዙ ችግር ደርሶብሽ ይሆናል:: ያ ለኔ ምኔ ነው? ቢሆንም ግን አዝናለሁ:: »

t.me/OLDBOOKSPDF

« ለማን? »

« ላንቺው »

« ግዴለም፣ አያስፈልግም » አለችኝ በትንፋሿ::

ይህን ማለቷ ነካካኝ:: እንዴ! እያባበልኩ ባናገርኳት እንዲህ . . .

« ታዲያ አሁን ምን ታስቢያለሽ? ደህና ህይወት አለኝ ትያለሽ? »

« ምንም አላስብ:: »

«ያ እኮ ነው ችግሩ፤ አለማሰብሽ:: ይልቅ ጊዜ ጥሎሽ ሳይፈተልክ ንቂ:: ጊዜ አለሽ:: ወጣት ነሽ፣ ሸጋ:: ማፍቀር፣ ማግባትና ደስተኛ መሆን ትችያለሽ . . . »

« ያገባ ሁሉ ደስተኛ አይደለም » አለችኝ በቁጣ እየገነፈለች::

« እሱንማ አውቃለሁ:: ቢሆንም ግን ከዚህ የማይሻል ትዳር የለም:: ያላማረ ትዳር እንኳን ከዚህ ጋር አይወዳደርም:: በትዳር ፍቅር ካለ ደግሞ ደስታ ቢቀርም ብዙ አያጎድልም:: ሃዘን ቢኖርም የኑሮ ጣዕሙ አይጠፋም:: እንደምንም ሆኖ መኖር መልካም ነገር



t.me/OLDBOOKSPDF

ነው:: አንቺ ግን እዚህ ከማማት በቀር ምን አለሽ?» በመጠየፍ ፊቴን ከስክሼ ተመለከትኳት:: በርጋታ ማሰብ ትቻለሁ:: የምናገረው ነገር መንፈሴን በርዞት መንገብገብ ጀምሬያለሁ:: ከዋሻዬ የቀፈቀፍኳቸውን ሃሣቦች ልዘራባት እየቋመጥኩ ነበር:: ከውስጤ የተቀጣጠለው ነገር ልፈፅመው የሚገባኝን ምግባር በመጨረሻ ከሰተልኝ::

« የእኔን ከዚህ መኖር እርሺው፣ እኔ ጥሩ ምሣሌ አይደለሁም:: ቆናልባትም ካንቺ የባሰኩ እሆናለሁ:: ስመጣ ደግሞ ሠክሬ ነበር » ብዬ ኃጢአቴን አለባበስኩና « በዚያ ላይ ደግሞ ወንድ ለሴት ምሣሌ አይሆንም:: ራሴን ባራክስና ባጎድፍ እንኳን የማንም ባሪያ አይደለሁም:: አሁን እዚህ ነኝ፣ ኋላ ደግሞ ሂጃለሁ:: ተጣጥቤ ሌላ ሰው ሆኜ ቁጭ እላለሁ:: አንቺ ግን ከመጀመሪያው ባሪያ ነሽ:: አዎ፣ ባሪያ! ሁሉን ሃብትሽን፣ ነፃነትሽን ጭምር አስረክበሻል:: በኋላ ከጫኑሽ ቀንበር መላቀቅ ብትፈልጊም አይቻልሽም:: ሌላውን ሁሉ እንተወው እስቲ፣ አሁን ላይገባሽ ይችላል:: ግን እውነቱን ንገሪኝ:- ገና ካሁኑ የእመቤትሽ ዕዳ አለብሽ አይደል? እየሽ ? ያውልሽ ! » አልኩኝ የሰጠችኝ መልስ ባይኖርም:: ዝም ብላ በመላ እሷነቷ ታዳምጠኛለች:: « ያ ነው ቀንበር ማለት፣ ሰንሰለት! ነፃነትሽን መመለስ ፈፅሞ አትችይም:: አያስችሉሽም:: ነፍስሽም ለሠይጣን የመሸጥ ያህል ነው . . .

« ከዚያም በላይ እኔም እንዳንቺ ያልታደልኩ፣ መከረኛ ሆኜ ከዚህ ቆሻሻ ምግባር ራሴን የምከተው መድረሻ ከማጣቴ ብዛት ይሆናል:: ስቃያቸውን አልኮል የሚያለዝብ የሚመስላቸው ሰዎች አሉ አይደለም? እኔም እዚህ እመጣለሁ:: እስቲ አንቺው መልሺልኝ:-

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚህ ቦታ ምን አንድ ጥሩ ነገር አለ? አንድ አልጋ ውስጥ ተኝተን እንዴት እንኳን ቃል ሳንለዋወጥ ለስንት ሰዓታት ቆየን:: ኋላ ነው አንቺም እኔም እንደዚሁ:: እንደዚህ ነበር ሰዎች ሊተዋወቁና ሊገናኙ የሚገባቸው? ከዚህ በላይ አፀያፊ ነገር ምን አለ? »

« አዎ ! » አለች ሊዛ በረጅሙ ተንፍሳ:: በፍጥነት መስማማቷ ገረመኝ:: ለካ እሷም እኔን በዝምታ እያዳመጠች ይሆንኑ ስታስብ ነበር:: « ይቺን ይወዳል ! » አልኩኝ በሆዴ፤ በደስታ እጆቼን ማፋተግ እየቃጣኝ:: እንዲህ ነው እንጂ ! . . . ተስማማን፣ ተመሣሠልን:: ይቺን የመሠለች እምቡጥ ከእጄ ማግባት አያቅተኝም:: ከሁሉም የጣመኝ የትብተባው አካሄድ ነበር::

ፊቷን ወደኔ ጠጋ አረገች:: አገጪን በእጇ ደግፋ ከራሷ ቀና ያለች መሠለኝ በጨለማው:: እንደገና እየመረመረችኝ ይሆናል:: ዓይኖቿን ማየት አለመቻሌ ቆጨኝ:: ትንፋሿ ከባህር ሆዷ እየተሟጠጠ ይወጣ ይመስል ረጅም ነው::

« ከዚህ ለምን መጣሽ? » ስል ጠየቅኳት:: አሁን ልጓሙን እንደነገሩ ጨብጫለሁ::

« እንዲሁ ዝም ብዬ »

« አባትሽ ቤት ብትሆኚ ኖሮ ምን ያህል የተሻለ እንደነበር አስቢው እስቲ:: አይበርድሽ፣ በገዛ ጎጆሽ በነፃነት መኖር:: »



t.me/OLDBOOKSPDF

አገባቤን ማሣመር አለብኝ:: ከሷ ጋር ሆድ ማባባስ አይሠራም:: ይህ እንዲሁ ከአእምሮዬ ብልጭ አለ እንጂ ብዙም ሃሣቤን አልለወጠውም:: አሳሰበችኝ:: ሁኔታዋ ልቤን ነክቶት ሳለ ለምልልሱ አእምሮዬ ተስሎ ነበር:: የይምሠልና የዕውን ስሜቶች ያለችግር አብረው ይኖራሉ::

« ማን ያውቃል? » ስል መለስኩ ቶሎ ብዬ:: « በሕይወት ብዙ ነገር ይፈጠራል:: እንደተበደልሽ እርግጠኛ ነኝ:: ታዲያ ጥፋቱ የእነርሱ እንጂ ያንቺ አይደለም:: ታሪክሽን ምንም አላውቅ፤ ቢሆንም አንችን የመሠለች ልጃገረድ በፈቃዷ ከምድር ተነስታ እዚህ አትመጣም . . . . »

« ምን ዓይነት ልጃገረድ ነኝ? » አለች የሹክታ ያህል:: ለማጓጓት::

« ምን መሆኔ ነው? » አልኩኝ በሆዴ:: ይኸኛው አጉል መንገድ ነው:: ግን ማን ያውቃል? ይሠራ ይሆናል:: ሊዛ ዝም ብላለች::

« አየሽ ሊዛ፣ ስለራሴ ልንገርሽ፦ በልጅነቴ ቤተሠብ ቢኖረኝ ኖሮ ሌላ ሰው እሆን ነበር:: ከቤተሰቦችሽ ጋር ሆነሽ፣ ምንም ያህል ነገሮች ቢከፉ እንኳን፣ የምትኖሪው ከወለዱሽ እናትና አባትሽ ጋር እንጂ ከጠላት ወይም ከባዕድ እንዳልሆነ ታውቂያለሽ፤ ቢያንስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢያንስ ባመት አንዴ እንኳን እንደሚወዱሽ ታያለሽ:: ሁሉ ቢቀር የምትኖሪው ከገዛ ቤትሽ ውስጥ መሆኑን ማወቁ ትልቅ ፀጋ ነው:: እኔ ታዲያ ያለ ቤተሠብ በማደጌ ይመሥለኛል እንዲዚህ ልበ-ድድር ሆኜ የቀረሁት::»

እንደገና ዝም ብዬ ጠበቅኩ:: የገባት አይመስለኝም:: ንግግሬ ሳቄን አመጣው::

« አባት ብሆንና ሴት ልጅ ብትኖረኝ፣ ከወንድ ልጆቼ አብልጬ እወዳት ነበር:: » ስል ማጥቃቴን በሌላ አቅጣጫ ጀመርኩ፣ አሳቧን ለመቀየስ ብዬ:: በእፍረት ፊቴ ሲግል ተሠማኝ::

« ለምን? » ብላ ጠየቀችኝ::

አሃ ! እያዳመጠችኝ ነው::

« እኔ እንጃ፣ ሊዛ:: አንድ በጣም ኮስታራና ጥብቅ የሆነ ሰውዬ አውቃለሁ:: ይህ ሰው ታዲያ ለሴት ልጁ ሟች ነው:: ከፊቷ ተንበርክኮ እጅና እግሮቿን እየሳመ አድንቋት አይጠግብም:: አብረው ከድግስ ሂደው፣ ተነስታ ስትደንስ፣ በቆመበት ለሰዓታት በአይኖቹ ይከተላታል:: የሷ ነገር አይሆንለትም:: እንዲህ አይነቱ ፍቅር ይገባኛል:: ረጭ ባለው ሌሊት ከእንቅልፏ ሲነቃ፣ ብድግ ብሎ ሂዶ ከመኝታ ክፍሏ ይገባና፣ በተኛችበት ግንባሯን ሥሞ፣ በፊቷ ላይ አማትቦ፣ ወደአልጋው ይመለሳል:: ለራሱ የረባ ሳይለብስ፣ ለሌሎች ሁሉ የሚነፍገውን ገንዘብ፣ እሷ ስትጠይቀው ኪሱን ገልብጦ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያሻችውን ያደርግላታል:: ውድና ምርጥ ስጦታ ይገዛላትና፣ የሠጣትን ከወደደችለት እንደልጅ ይቦርቃል:: አባት ነው ከእናት ይልቅ ሴት ልጁን የሚወደው:: አንዳንድ ልጃገረዶች ያባታቸውን ቤት ደስታ የሚያክል በምድር አያገኙም! በበኩሌ ሴት ልጄን ለትዳር የምሠጥ አይመሥለኝም:: »

« እንዴት? » አለችኝ

« የምቀና ይመሥለኛል:: እውነቴን ነው:: በምን ልቤ ሌላ ሰው እንድትስም እፈቅዳለሁ? ወይም ከአባቷ አብልጣ ባዕድ እንድትወድ? ማሰቡ ብቻ ይረብሸኛል:: በርግጥ ይህ ሁሉ ቂልነት ነው:: ሁላችንም በመጨረሻ ለህይወት ዕውነታዎች ዓይናችንን መግለጥ ይኖርብናል:: ቢሆንም ግን፣ ለጋብቻ እጇን ከመስጠቴ በፊት በሥጋትና በጭንቀት እንደምሠቃይ አውቃለሁ:: ከፈላጊዋ ሁሉ እንከን እያወጣሁ እቆይና፣ በመጨረሻ የግዴን፣ የወደደችውን ከማግባት አልይዛትም:: ለአባት ደግሞ ልጁ ያፈቀረችው ሰው ነው በተለይ የማይሆናት መሥሎ የሚታየው:: እና እንዲህ ነው፣ ሊዛ:: ብዙ ቤተሰቦች መሃል ችግር የሚፈጠረው ለዚህ ነው:: »

« አንዳንዶቹ ሴት ልጃቸውን በወግ በማዕረግ ከመዳር ይልቅ ቢሸጧት ይወዳሉ » አለችኝ በድንገት::

አሃ! «አየሽ ሊዛ፣ ያን የሚያደርጉ እግዜርን የማያውቁና ፍቅር በቤታቸው የሌለ ቤተሠቦች ናቸው » አልኳት:: « ፍቅር ከሌለ ደግሞ ቀና ኅሊና የለም:: እንዲህ ያሉ ሰዎች መኖራቸውን

t.me/OLDBOOKSPDF

አውቃለሁ፤ የማወራው ግን ስለነሱ አይደለም:: አንችም ምናልባት ቤተሠቦችሽ ፍቅር ነፍገውሽ ይሆናል እንዲህ በምሬት የተናገርሽው:: ዕድልሽ ባይቀና ነው:: ሀም . . . ግን የዚህ ሁሉ ምክንያት ድህነት ነው:: »

« የከበርቴዎቹስ ቤት ምኑ ይሻላል? በድህነት ክብራቸውን ጠብቀው የሚኖሩ ሞልተው የለም? »

« ሀም . . . አዎ ይኖሩ ይሆናል:: ሌላው ነገር ደግሞ፣ ሰዎች ስንባል ስቃያችንን ብቻ እንጂ በህይወታችን ያለውን መልካም ነገር መቁጠር አንወድም:: ሁላችንም ጠንቅቀን ብናስተውል፣ ለእያንዳንዳችን የተሰፈረልን ሲሳይና ደስታ አለ:: በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ በተሣካበት ቤተሠብ ውስጥ ባል ሚስቱን ይወዳል፣ ያከብራታል:: ጥሏት ሊሄድ በጭራሽ አያስብም:: ይህን ለመሠለ ቤተሠብ፣ ሕይወት ምን ያህል ጣዕም አላት! አልፎ አልፎ ችግርና ሃዘን ቢኖርም እንኳን ! አንችም ትዳር ይዘሽ ይህን ራስሽ ታይው ይሆናል:: የምትወጂውን ሰው ካገባሽ በኋላ፣ በተለይ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የሚኖረው ደስታ ይታይሻል? ከባልሽ ጋር የሚፈጠረው ጥል እንኳን የሚያልቀው በፍቅር ነው:: አንዳንድ ሴቶች ፍቅራቸው እጅግ ሲጠና ከባላቸው ጋር በሆነ ባልሆነው መጣላት ያበዛሉ:: እውነቴን ነው:: አንዲት የማውቃት ሴት በየምክንያቱ ባሏን ትነተርከዋለች:: ' በነገር የምጠብስህ እጅግ አድርጌ ስለማፈቅርህ ነው፣ የፍቅሬን መጠን እንድታውቀው ' ትለዋለች:: ከፍቅር የተነሳ ተፈቃሪውን ማሠቃየት አዲስ ነገር አይደለም:: በርግጥ ብዙውን ጊዜ ይህን የሚያደርጉት ሴቶች ናቸው:: ' አሁን ትንሽ ይሠቃይና፣ ኋላ

t.me/OLDBOOKSPDF

በፍቅሬ አጥለቅልቄ፣ እቅፍ አድርጌ እየሣምኩ እከሥዋለሁ ' ብለው ያስባሉ:: ዳምኖ፣ ዘንቦ ሲያባራ፣ ሁሉ ብሩኅ፣ ሠላም፣ ፍቅርና እንደአብሾ የሚያሰክር ደስታ::

«ደግሞ ቀናተኞችም አሉ:: ሌላ የማውቃት ሴትዮ ባሏ ከቤት በወጣ ቁጥር አንዳች ነገር ከቤቷ ነትቶ ያወጣትና፣ በጨለማ ሳትታይ ተከትላው ትከንፋለች:: ከማን ጋር እንደተገናኘ፣ ከማን ቤት ጎራ እንዳለ፣ ከየትኛዋ ሴት ጋር እንደተጫወተ አያለሁ ብላ:: ይህ ፀያፍ ነገር ነው:: መጥፎነቱም ሴትዮዋ ታውቀው ነበር:: ድርጊቱን ስታስበው ታፍርበታለች፣ ይፀፀታታል:: ይሁንና ግን ባሏን ታፈቅረዋለች፤ ይህን ሁሉ የምታደርገውም ከፍቅሯ የተነሣ ነው:: ከጠባቸው በኋላ ሲታረቁ ምንኛ ደስ ይላቸዋል! ጥፋቷን ስታምን፣ ወይም ጥፋቱን ይቅር ስትለው ልቧ በሃሴት ትርገበገባለች:: ሁለቱም፣ ሸክም የወረደላቸው ያህል ቅልል ይላቸውና ገና አዲስ ትዳር ጀምረው ፍቅራቸውም አፍላ የሆነ ይመሥል ይፈነድቃሉ:: ታዲያ በርግጥ የሚዋደዱ ባልና ሚስት መሐል የሚፈጠር ነገርን ማንም ማወቅ የለበትም:: ምንም ጉዳይ ቢያጣላቸው፣ እናታቸውን እንኳን ቢሆን እንድትዳኛቸው መጋበዝ የለባቸውም:: የራሳቸው ዳኞች ራሳቸው ብቻ ናቸው::

«ፍቅር ከአምላክ የተሠጠ ምሥጢር ነውና ምንም ቢሆን ከሌሎች ዓይን ልንጠብቀው ይገባል:: ያኔ ነው የተቀደሰና መልካም የሚሆነው:: ይህ ሲሆን ነው ባልና ሚስት የበለጠ የሚከባበሩት:: አክብሮት ደግሞ የብዙ መልካም ነገር መሠረት ነው:: ፍቅር ካለ፣ የተጋቡትም በውን ተፋቅረው ከሆነ ፍቅራቸው ለምን ይሞታል?

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍቅርን በህይወት ማቆየት ይቻል የለምን? የማይቻልበት ሁኔታ የሚገኝ አይመስለኝም:: በተለይ ባልየው ደግና ቅን ሰው ከሆነ፣ ፍቅሩ ሊሟጠጥ አይችልም:: በርግጥ በትጻራቸው ሊ.ጋነት ዘመን የነበረው ዓይነት ስሜት ያልፍ ይሆናል፤ እሱን የሚተካው ግን አሁንም ፍቅር ነው:: የላቀና የተሻለ ፍቅር:: ባልና ሚስት በመንፈስ ይቀራረባሉ፣ ይጎዳኛሉ፤ የሚያደርጉት ሁሉ የጋራ ጉዳይ ነው፤ በመካከላቸው የሚደብቁት ነገር አይኖርም:: ልጆች መውለድ ሲጀምሩ ደግሞ፣ የችግር ዘመናቸው እንኳን የደስታ ወቅት ነው የሚመስላቸው:: ሥራ እንደቁልቁለት ነው፣ አንዳንዴ ለልጆቻቸው ሲሉ ራሳቸውን ቢነፍጉም እንኳን ደስታቸው አይበረዝም:: ለልጆችሽ የምታደርጊው መልካም ነገር ሁሉ እነርሱ ላንቺ የሚኖራቸውን ፍቅር የሚያሳድግ ስለሆነ ቅር አይልሽም::

« ልጆችሽ ማደግ ሲጀምሩም፣ ያንቺ ሕይወት ምሣሌያቸው እንደሆነ፣ ከሞትሽ ወዲያ እንኳን ያንች ሃሣብና መንፈስ በውስጣቸው እንዳለና፣ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ይዘውት እንደሚኖሩ፣ ያወረስሻቸውን ቅርስ ተረክበው በአምሣልሽ እንደሚያድጉ ታውቂያለሽ:: ስለዚህ ይህ ታላቅ ሃላፊነት ነው:: ታዲያ ይህ እንዲህ ሳለ፣ ባልና ሚስት እያደር አንድ መሆን እንዴት ይሳናቸዋል? አንዳንድ ሰዎች ልጅ ማሣደግ መከራ ነው ይላሉ:: በእውነቱ ግን ከመንግሥተ ሰማያት የመጣ ተድላና ደስታ ነው:: ሕፃናት ትወጃለሽ ሊዛ? እኔ በጣም ነው የምወዳቸው:: እስቲ ይታይሽ የፋፋ እምቡጥ ልጅ ጡትሽን ሲጠባ:: ሚስቱ ልጃቸውን በእቅፏ ይዛ አይቶ፣ ምን ዓይነት ባል ነው በልቡ ከፍቅር በቀር ሌላ ነገር የሚገኝ? አንድ ፍሬ ልጅሽ፣ ለስላሳ ጉንጮቹ ስትነኪያቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

ትምቡክ ትምቡክ እያሉ፣ በጉያሽ ሙቀት ሲፈነድቅ፣ እንደአንኮይ ልስልስ፣ ጥብቅ ያሉ ትናንሽ እጅና እግሮቹ፣ ጥቃቅን ንፁህ ጥፍሮቻቸው በማነሳቸው የሚያስቁ፣ ዓይኖቹ ሁሉን የሚያውቁ ይመሥል ሽቅብ አትኩረው ሲመለከቱሽ:: ሲጠባ ደግሞ ጡትሽን በአንዲት ፍሬ እጁ እየጎተተ ሲጫወት፣ አባቱ ከቤት ሲገባ መጥባቱን ያቆምና ዞር ብሎ ተመልክቶ አስቂኝ ነገር ያየ ይመስል ይፍለቀለቅና መልሶ ጡቱን ይጎርሳል:: ኋላ ጥርስ ማብቀል ሲጀምር ጡትሽን ነክስ ያደርግና አሥልቆ ያይሻል:: እንዲህ እናት፣ አባትና ልጅ፣ ሦስቱም አንድ ላይ ሆነው ያለው ዓይነት ደስታ ከወዴት ይገኛል? ለዚህ ብቻ ሲባል ብዙ በደል ይረሳ የለም? እና ሲዛ፣ ሌሎችን ከመፍረዱና ከመውቀሱ በፊት፣ ሰው ሁሉ ራሱ አኗኗርን መማር ይገባዋል::

«እንዲህ ነው የማገኝሽ! » አልኩኝ በልቤ፣ « ይህን የመሣሠለ ትዕይንት እየፈጠርኩ፣ በምኞት ፈረስ እያስገርኩ! » ለነገሩ ግን የማወቃት ከልቤ ነበር:: ወዲያው በእፍረት ፊቴ ቀላ:: በድንገት ሳቋን ብትለቀው የት እደበቃለሁ? ማሰቡ ብቻ አስቆጣኝ:: ወደመጨረሻ ላይ ወሬዬ ትንሽ ገደብ ጥሶ ነበርና አሁን ቆረቆረኝ:: እሷም፣ እኔም ዝምታ ውጠናል::

ልጎንጣት ሲቃጣኝ.. « ግን እንዲያው . . . » አለችና ሳትጨርሰው አቋረጠች:: ነገሩ ገብቶኛል:: ከድምጿ ውስጥ አዲስ ነገር ተጨምሯል:: እንደመጀመሪያው የሠላና የደረቀ ሳይሆን፣ የሚርበተበት፣ የዓይናፋር ድምፅ ስለነበር በራሴ አፍሬ ፀፀት ተሠማኝ::

t.me/OLDBOOKSPDF

« ምን? » ስል ጠየቅኳት ረጋ ብዬ::

« አንተ . . . »

« ምን? »

« እንዲያው ነገርህ ሁሉ . . . የመፅሐፍ ታሪክ ይመሥላል » አለች:: አሁን ደግሞ ከድምጿ ፌዝ የሠረገበት መሠለኝ:: ንግግሯ ወጋኝ:: የጠበቅኩት አልነበረም:: ሲታወቃት የምታፌዝ ለመምሠል እየሞከረች መሆኑ አልገባኝም:: ውስጣቸው ዓይናፋር የሆነ ልበ ንፁሓን፣ ባለጌዎች ነፍሳቸውን ሊበረብሩ ሲታገሉዋቸው፣ እስከመጨረሻው በኩሩነታቸው የእውነት ምንነታቸውን ላለማሣየት አሻፈረኝ ብለው ይቆዩና፣ ሲታከታቸው የፌዝ ቆብ ጭነው ማምለጥ ይሞክራሉ:: ሊዛ በመጨረሻ የተናገረችውን ለማውጣት ስታምጥ ካየሁባት የፊራ ተባ እንቅስቃሴ ይህን መረዳት እችል ነበር:: ሆኖም ግን አልቻልኩም! ስለዚህም የብቀላ ቁጣ ከውስጤ ተቀጣጠለ:: ቆይ፣ ጠብቂ! አልኩኝ በሆዴ::



« አይደለም፣ ሊዛ:: እኔ ራሴ፣ የዳር ተመልካቹ፣ የሁኔታዎችን አፀያፊነት እያየሁ መፅሐፍን እዚህ ምን አመጣው? ከዳርም ብቻ አይደለም፤ በተለይ አሁን እዚህ ሆኜ በግልፅ አየዋለሁ:: አንችስ ይህን ሳታውቂው ቀርተሽ ነው? ወራዳነቱ፣ ቆሻሻነቱ ሳይገባሽ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀርቶ ነው? ሲደጋገም የማይለመድ ነገር የለም እንጂ:: የማታረጅ ይመሥልሻል? ሁሌ እንዳማረብሽ እዚሁ የምትኖሪ? እዚህ መኖር ከሚመርጡት ባትሆኚም:: ስለአሁኑ አኗኗርሽ ደግሞ ይህን እነግርሻለሁ:- ወጣት ነሽ፣ መልከመልካም፣ አመለሸጋ፤ ስሜትሽ ያልደነዘ፣ ለዛሽ ያልተሟጠጠ:: ታዲያ ቅድም ከእንቅልፌ እንደነቃሁ ምን እንደተሠማኝ ታውቂያለሽ? ካንቺ ጋር በአንድ አልጋ በመተኛቴ ራሴን ተጠየፍኩት:: የሠከረ ብቻ ነው እዚህ የሚመጣው:: ሌላ ቦታ ብትሆኚና ይህን የመሠለ ዓዘቅት ውስጥ ባትገቢ ኖሮ፣ መከተል ብቻ ሳይሆን አፈቅርሽ ነበር:: ካፍሽ በምትወጣ ቃል፣ ካይኖችሽ በማገኘው ተስፋ እየተደሠትኩ፣ በምታልፊበት ቆሜ እጠብቅሽ ነበር:: ከፊትሽ ተንበርክኬ የትዳር ጓደኝነትሽን ስጠይቅ ኩራት ይሠማኝ ነበር:: እንዲት እንኳን ቆሻሻ ነገር ስላንቺ ላስብ አልደፍርም::

« እዚህ ግን፣ እስከፈለኩሽ ድረስ ወደድሽም ጠላሽ መምጣት ግዴታሽ ነው:: ታዛገዬ አንቺ እንጂ፣ እኔ ታዛዥሽ አይደለሁም:: የድሆች መጨረሻ የሆነ ላብአደር ጉልበቱን ሲሸጥ እንኳን መላ ሰውነቱን ለባርነት አሳልፎ አይሠጥም፤ ያገልግሎት ግዴታውም ተወሰነ ጊዜ እንደሆነ ያውቀዋል:: ያንቺ ባርነት ፍፃሜ ግን መች ነው? እስቲ አስቢው:- ስንቱን ነው እርግፍ አድርገሽ እዚህ የገባሽው? ነፍስሽን የምታገኚባት ይመሥል ከሥጋሽ ጋር አቆራኝተሽ ለግዞት የሠጠሻት! ፍቅርሽን ማንም ሠካራም እንዲረጋግጠው አንጥፈሽለት! ፍቅርን የመሠለ ዕንቁ፣ የሴት ልጅ ቅርሷን! የልጃገረድ ፍቅር ይገባው ዘንድ አፍቃሪ ሞትን እንኳን ከመጋፈጥ ወደኋላ አይልም:: አሁን ታዲያ ያንቺ ፍቅር ዋጋው ምን ያህል ነው? ሁለንተናሽ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሽያጭ ቀርቧል:- ከእግር እስከራስሽ:: ያንችን ፍቅር ማን ይፈልጋል አላፊ አግዳሚው ያሻውን ያለፍቅር ማግኘት ሲችል?

«ለሴት ልጅ ከዚህ የከፋ ውርደት የለም:: እዚህ እንደሚያሞላቅቋችሁና ልዩ ወዳጅ ተብዬውን እንድትይዙ እንደሚፈቀድላችሁ ሰምቻለሁ፤ በዚህ ሊሸነግሏችሁ:: ላወቀው ግን ይህ ከንቱ ቀልድ ነው፣ ርጉም ዘበት:: እውነት አይምሠልሽ:: ያስ ወዳጅሽ በውን ያፈቅርሻል? በፍፁም! የፈለገ ሰው መጥቶ፣ አንቺን ከእቅፉ ነጥቆ ያሻውን እንደሚያደርግ ሲያውቀው፣ እንዴት አድርጎ ነው የሚያፈቅርሽ? ያንን ታግሶ አፈቅርሻለሁ ካለሽም ክርፋታም ክብት ነው! ላንቺስ ምን ዓይነት ክብር ይኖረዋል ከዚያ በኋላ? ሁለታችሁን የሚያስተሳስራችሁ ምን ነገር አለ? እያፌዘብሽ ይዘርፍሻል:- ያ ነው የሱ ፍቅር:: አንዳንዴ እየተነሳ ካልደበደበሽም ተመሥገን በይ:: እስቲ እንዲህ ያለ ወዳጅ ካለሽ ያገባሽ እንደሆነ ጠ ይቂው:: ባይተፋብሽና በጥፊ ባይልሽ፣ እፊትሽ አፉን ከፍቶ ይስቅብሻል:: እሱ ራሱ ዋጋ ያለው ሰው ሆኖ አይምሠልሽ ታዲያ:: እና ለምኔ ብለሽ ነው እንዲህ ባለ ህይወት የተጠመድሽው? እዚህ ለሚሠጡሽ ቡናና እንደልብ ለሚቀርብልሽ ምግብ ነው? የሚቀልቡሽ ለምን ይመሥልሻል? የዚህ ቤት ምግብ ለጨዋ ሴት ቢቀርብላት የመጀመሪያው ጉርሻ ከጉሮሮዋ ይሠነቀራል፤ ለምን እንደታሠበላት ታውቀዋለችና:: የቤቱ ባለቤት ዕዳ አለብሽ፤ ያም ታዲያ የዕድሜ ልክ ዕዳ ነው፤ ደንበኞችሽ መራቅ እስኪጀምሩ:: ያ ጊዜ ደግሞ ፈጥኖ ይደርሳል:: በወጣትነትሽ አትመኪ:: እዚህ ሁሉ ነገር በቅፅበት ነው የሚከስመው:: ስትጠወልጊ አውጥተው ይጥሉሻል:: ከማባረራቸው በፊት በሆነ ባልሆነው ነገር ይጀምሩሻል፣ ይሠድቡሻል፣ ይወቅሱሻል፤

t.me/OLDBOOKSPDF

ለእመቤትሽ ጤናሽን፣ ልጅነትሽንና ነፍስሽን አስረክበሽ የተረፈሽ ነገር ያለ ይመሥል፤ ያደኸየሻት፣ የዘረፍሻትና ከቤቷ የነቀልሻት ይመስል።

« ያኔ ማንም ቆሞ ይከራከርልኛል ብለሽ አታስቢ። ሁሉም ይጠሉሻል። እንዳንቺ በግዞት ሠንሠለት የተቸነከሩት ባልደረቦችሽ እንኳን ሳይቀሩ፣ ከቤቱ እመቤት ጋር ለመሥማማት ሲሉ እንደሷ ጠምደው ያጎሳቁሉሻል። በዚህ ህይወት ጥቂት የቆዩት ጎሊናና ርኅራኄ የላቸውም፤ አኗኗራቸውን የመሠለ አዋራጅና እኩይ ተፅዕኖ የለምና። ተራ በተራ ከያንዳንዷ ፀጋሽ ትለያያለሽ፦ ከጤናሽ፣ ከወጣትነትሽ፣ ከውበትሽና ከተስፋሽ። በሃያ ሁለት ዓመትሽ የሠላሳ አምስት ዓመት ሴት መስለሽ ታርፊዋለሽ። እንደዚያም ሆኖ በሽታ ካላደራብሽ እድለኛ ነሽ።

« አሁን ሁሉ ነገር የቀናልሽ፣ ኑሮሽ ውጣ ውረድ የሌለበት ጨዋታ እንደሚመስልሽ ይገባኛል። ብታውቂው ግን ይህን የመሠለ የፍዳ ኑሮ በዓለም ላይ አልነበረም፣ አይኖርምም። ይህ የሚከሰትልሽ ደረጃሽ ዝቅ ማለት ሲጀምር ነው፣ ዋጋሽ ሲወድቅ። ከዚህ ሲያባርሩሽ፣ አንዲት ቃል ሳትተነፍሺ በደለኛዋ ራስሽ እንደሆንሽ ሁሉ አንገትሽን ደፍተሽ ሹልክ ብለሽ ትወጫለሽ። አዎ፣ ከዚህ ወጥተሽ ወደሌላ ቤት፣ ከዚያም ዝቅ ወዳለ ሦስተኛ ቤት ትሄጂና በመጨረሻ ከሴናያ ጎዳና ላይ ካለ ርካሽ ቤት ትገቢያለሽ። እንደገባሽ የሚቀበሉሽ በዱላ ነው። የሴናያ ሴት አዳሪዎች ትርፍ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ከመካከላቸው ደካማዋን እየደበደቡ ነው። ደምበኞቻቸውም ከሁሉ በፊት ቡጢ ይቀናቸዋል። የሴናያ ህይወት

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲህ የሚዘገንን መሆኑን ካላመንሽ አንዴ ሄደሽ በገዛ ዓይንሽ ተመልከቺው:: ባለፈው የአዲስ ዓመት ቀን እዚያ ያየኋት ሴት ትዝ ትለኛለች:: እያለቀሠች ረበሸችን ብለው ብጤዎቿ በጨለማ፣ በዚያ በብርድ አስወጥተው ቆልፈውባታል:: እኔ ሳገኛት ከማታ ሦስት ሰዓት ነበር፤ ጥምብዝ ብላ ሰክራ፣ ፀጉሯ ተንጨፍርሮ፣ ገላዋ ተገላልጦ፣ በቡጢ የበለዘ ፊቷን እሽፍን ብላ የቀባችው ዱቄት ማሥፈራሪያ አስመስሏት:: አንዱ ጋሪ ነጂ ሲነርታት አድሮ ከጥርሷና ካፍንጫዋ ደም ይፈስ ነበር::

« በጁ የአሣ ቋንጣ ይዛ ደረጃው ላይ ተቀምጣ ዕድሏን እየረገመች ትጮሃለች፣ ታላዝናለች:: እየቆየች ደግሞ በያዘችው አሣ የደረጃውን ድንጋይ ትጠበጥባለች:: የሠከሩ ወታደሮችና አውደልዳይ መንገደኞች ከበዋት ይሳለቁባት ነበር:: አንቺ ታዲያ የዚያች ሴት ዕጣ መቼም የሚደርስሽ አይመስልሽም:: እኔም አሁን ያንን መገመት ያቅተኛል:: ግን ማን ያውቃል? ምናልባት ያች ባለአሣዋ ሴትዮ ከስምንት ወይም ከአሥር ዓመታት በፊት ምንም አጉል ነገር የማታውቅ እምቡጥ፣ መናገር የምትፈራ ዓይናፋር፣ ንፁህ ነበረች፣ ካደገችበት ቤት ወጥታ ስትመጣ:: ልክ እንዳንቺ ኩሩ፣ በቀላሉ የምትቆጣ፣ በቤቱ ካሉት ሁሉ የተለየች ንግሥት የመሠለች ሽጋ፣ የሚወዷትንና የምትወደውን ሰው ደስ የምታሠኝ:: ታዲያ መጨረሻዋ ምን እንደሆነ አየሽ? ያኔ እንደዚያ በስካርና በውርጭ ገርጥታ፣ እዚያ ቆሻሻ ደረጃ ላይ የአሣውን ቋንጣ እየቀጠቀጠች ስታለቅስ የቀድሞ ሕይወቷ ትዝ ቢላት ምን ይሠማታል? አባቷ ቤት ሣለች በተማሪነቷ ጊዜ የጎረቤቷ ልጅ መንገድ ላይ ቆሞ እየጠበቃት

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍቅሩን ሲገልፅላትና፣ ኋላም መላ ሕይወታቸውን ላይለያዩ ተማምለው ሲያድጉ ሲጋቡ ቃል ሲገቡ ቢታወሳት ምን ይውጣታል?

«አይምሠልሽ ሊዛ፣ ከዚች ዛሬ ጧት ካየኋት ሴት ዕጣ አንድ የምድር በታች ጨለማ ውስጥ በነቀርሳ መሞት ይሻላል:: ሆስፒታል ትያለሽ? ሆስፒታል ከወሠዱሽ ጥሩ ነው:: ግን እመቤትሽ የማትለቅሽ ቢሆንስ? የሳምባ ነቀርሣ ወባ አይደለም:: እሱ የለከፋቸው ሰዎች እስከመጨረሻው ድረስ ደህና ነን እያሉ ተስፋ ያደርጋሉ:: አንች በሞት አፋፍ ላይ ብትሆኚ ለእመቤትሽ ምን ሊገዳት? ነፍስሽን ሸጠሽላት በገንዘብ ዕዳም ስለያዘችሽ እምቢታን አታስቢያትም:: መልአከ ሞት ሲቀርብሽ ዋጋሽና አትራፊነትሽ እንዳለቀ ስለሚያውቁት ሁሉም እርግፍ አድርገው ይተውሻል:: እንዲያውም በከንቱ ቦታ በማጣበብሽና ቶሎ አልሞት ብለሽ ጣር በማብዛትሽ ይነተርኩሻል:: የምትጠጪው ውሃ እንዲያቀብሉሽ ብትለምኚ አዝኖ የሚሰጥሽ አታገኚም፣ ቢሰጡሽ እንኳን ከርግማን ጋር ነው:- 'እሪ ወዲያ ይዞሽ ይሂድ! ጧት ማታ እያቃሰትሽና እየሳልሽ እንቅልፍ እንደነሳሽን!' እውነቴን ነው:: ሰው ለሰው ይህን መሣይ ርጉም ነገር ሲናገር ሰምቻለሁ:: ፍፃሜሽ ሲቃረብ ከቤቱ ውስጥ አንዱ ጨለማ ስርቻ ውስጥ ይከቱሻል:: ያኔ ታዲያ ብቻሽን ተቆራምተሽ ሞትሽን ስትጠብቂ ምን እንደሚታሰብሽ ላንቺ እተውዋለሁ::

«ከዚያም ስትሞቺ የማያውቅሽ ባይተዋር ነው እያማረረ ጫር ጫር አድርጎ የሚቀብርሽ:: የወዳጅ ዘመድ እጅ ሳይነካሽ፣ አንድ እንኳን ሰው አዝኖ ሳያለቅስልሽ:: ያኔ ሁሉም የሚያስቡት እንዴት

t.me/OLDBOOKSPDF

አድርገው ሬሳሽን በፍጥነት ወዲያ ብለው እንደሚገላገሉ ነው፡፡ ርካሽ የሬሣ ሳጥን ውስጥ በድንሽን ከተው፣ ዛሬ ጧት ያችን ሴት እንደወሰዷት ተሸክመው ይወስዱሽና ከቀበሩሽ በኋላ ለመታሰቢያሽ ሊጠጡ መሸታ ቤት ይሄዳሉ፡፡ መቃብሩ እንደዘወትሩ ውሃ፣ በረዶና ጭቃ ሞልቶት ማነው ላንች በድን የሚጨነቀው? ' በቃ አውርድና ከተቃት፣ እንትና፡፡ ኧረ ወዲያ! እንዲህ ነው እንጂ ሕይወት! እዚህ እንኳ እግሯን አትዘረጋም! አይገርምም? ገመዱን በወጉ ያዘው እንጂ፣ ምን ነካህ! ' ' አይ፣ ይበቃል፡፡ ' ' ምን ማለትህ ነው? እስቲ ተመልከታት በጎኗ እኮ ነው የተጋደመችው! ምንስ ብትሆን ሰው አልነበረችም? ' ' እባክህ ትሁን፣ አፈሩን እንመልስና እንሂድ፡፡ '

«ክርክራቸው ከዚህ አያልፍም፡፡ ተቻኩለው፣ ሳጥኑን በእርጥብ አፈርና ድንጋይ ሸፍነው ወደ መጠጥ ቤት ይሄዳሉ፡፡ የምድር ምንነትሽ፣ ታሪክሽና መታሠቢያሽ በዚህ ይደመደማል፡፡ ሌሎች ሰዎች ከሞቱ በኋላ ልጆች፣ አባቶች፣ ባሎች እየሄዱ መቃብራቸውን ይጎበኛሉ፡፡ በዚህ በሰፊ ዓለም ከሚርመሠመሠው ሕዝብ አንድ እንኳን የሰው ፍጡር ሊያስታውስሽ ከመቃብርሽ የሚሄድ የለም፡፡ እንዳልተወለድሽ፣ እንዳልኖርሽ፣ ስምሽ አብሮሽ ይቀበራል፡፡ በጭቃና በረግረግ ተውጠሽ ብቻሽን ከወደቅሽበት አንድ ሌሊት ተነስተሽ የገነዘሽን ሳጥን ማንኳኳት እስክትመኚ ድረስ! ' እባካችሁ አውጡኝ ሰዎች! አንዲት ቀን እንኳን እንደሰው ኖሬ ልሙት፤ ከመሸታ ቤት በአልኮል በስብሳ የጠፋች ሕይወቴ ዳግም ዕድል ታግኝ፤ እንደገና በወጉ ኖሬ ልሙት . . . '»

t.me/OLDBOOKSPDF

የራሴ አነጋገር ልቤን ነክቶት፣ ከውሥጤ የገነፈለው ሥሜት ጉሮሮዬ ውስጥ እንዳች ነገር ሠነቀረብኝ:: ወዲያው በድንገት ንግግሬን አቋረጥኩና ደንግጬ ከተጋደምኩበት ቀና አልኩና በስጋት አዳመጥኩ:: ያለምክንያት አልነበረም የሠጋሁት:: ነፍሷን እንዳማሠልኩት ቀደም ብዬ ሲገባኝ፣ ይብሱን አጥብቄ ልቀጣት እንዳሰብኩ ትዝ ይለኛል:: የኮረኮረኝ፣ የገፋፋኝ፣ ሰርስሬ ከውስጧ ለመግባት የማደርገው የራሴ ትግል ነበር::

አነጋገሬ ደረቅና ወዝ የሌለው፣ ከመፅሐፍ የሚያነቡት እንደሚመስል አውቄያለሁ:: ከዚህ በተለየ መንገድ መናገር ግን አይቻለኝም ነበር:: ሆኖም ግን እንደምትረዳኝና እንዲያውም ይህ የመፅሐፍ ትረካ የመሠለ ወሬዬ ያሰብኩትን ሊያስፈፅመኝ እንደሚችል ስለገመትኩ አልገደደኝም ነበር:: ታዲያ በመጨረሻ ያሰብኩት ተሳክቶ በድንገት በማየቴ ደነገጥኩ:: የነበረችበትን አይነት ስቃይ አይቼ አላውቅም:: እንደእንጨት ድርቅ ብላ ተኝታ፣ ትራሱን በሁለት እጆቿ ጨምድዳ ፊቷን ቀብራበታለች:: ደረቷ ባመቀችው ሐዘንና ሲቃ ሊሠነጠቅ የደረሰ ይመስላል:: ያ ለጋ ሰውነቷ እየቆየ ይንዘፈዘፋል:: ከውስጧ ልታዳፍነው ትታገለው የነበረው ልቅሶዋ እያነቃት እልፎ እልፎ ፈትልኮ ሲወጣባት ፊቷን አጥብቃ ከትራሱ ትቀብረዋለች:: ስቃይዋና ልቅሶዋ እንዲታይ አልፈለገችም:: ትራሱን መንከሱ አልበቃ ሲላት እጇዋን እስከሚደማ ድረስ ነከሰችው (ኋላ ነበር ደሙን ያየሁት) :: አንዳንዴ ደግሞ ጣቶቿን ከፀጉሯ ውስጥ ትከትና ግትር ብላ፣ ትንፋሿን ውጣ፣ ጥርሷን ነክሳ ትቆያለች:: ቢጨንቀኝ ነገር መለወጥ አሰብኩ፣ ከዚያም ላባብላት ሞከርኩ:: ሁኔታዋ ግን ሁኔታዋ ... 

t.me/OLDBOOKSPDF

ተነስቼ እየተደናበርኩ ልብሶቼን ለቃቀምኩና ለመሄድ ተዘጋጀሁ:: ከጨለማው የተነሳ ልብሴን ቶሎ ማጥለቅ አቅቶኝ ስንጎዳጎድ ቆየሁና ዳብሼ ያገኘሁትን ክብሪት ለኩሼ ሻማውን ሳበራ ሊዛ ካልጋው ዘልላ ብድግ አለችና ተቀመጠች:: በሥቃይ የተገረፈ ፊቷን በፈገግታ ልትሸፍነው ስትሞክር ወፈፍ ያረጋት አስመሰላት:: ከጎኗ ተቀምጬ እጆቿን ስይዝ ሻል አላትና ልታቅፈኝ እንደፈለገች ሁሉ ወደኔ ጠጋ አለች፤ ግን አላቀፈችኝም:: አንገቷን ደፍታ በዝምታ ተቀመጠች::

« ሊዛ ይቅር በይኝ፣ እባክሽ . . . ምን እንደነካኝ እንጃ » ብዬ እንደጀመርኩ እጄን ጥብቅ አድርጋ ጨመቀችው:: የምናገረው አስፈላጊ እንዳልነበር አውቄ ዝም አልኩ::

« ይኸው አድራሻዬን ልስጥሽ ሊዛ፣ እኔ ዘንድ ነይ:: »

« እሺ እመጣለሁ » አለችኝ እንዳቀረቀረች፣ ሳታቅማማ::

« መሄዴ ነው፤ ደህና ሁኚ እስከምንገናኝ ድረስ:: » ስነሳ አብራኝ ብድግ አለች:: ከዚያ በድንገት ፊቷ ቀላና ያንገት ልብሷን አፈፍ አድርጋ ራሷን ሸፋፍና ሽቅብ ተመለከተችኝ:: ሁኔታዋ አንጀቴን ስለበላው ወጥቼ ለመሄድ እየተቻኮልኩ ነበር::

« አንዴ ቆየኝ » ብላ ኮቴን ጎትታ አቆመችኝና ፈጥና ወደ አንድ ክፍል ገባች:: ትዝ ብሏት ልታሳየኝ ያሰበችው ነገር ነበራት:: ስትሄድ ፊቷ በድንገት ብሩህ ሆኖ ዓይኖቿም ፈካ ብለው ነበር:: ምን ይሆን? ቆሜ ጠበቅኋት:: ወዲያው ተመለሠች:: አስተያየቷ ለማላውቀው ጥፋቷ ይቅርታ የምትጠይቀኝ አስመሰሏታል::

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለንተናዋ የቀድሞው አልነበረም:: መጀመሪያ ሳገኛት ለብሳው የነበረው የግዴለሽነት፣ የጥርጣሬና የግትርነት ጥላዋ ተገፍፎ በምትኩ እምነት፣ ገርነትና ዓይናፋርነት ሠፍኖባታል:: ሕፃናት የሚወዱትን ሰው አንድ ነገር ሲጠይቁ ገፅታቸው እንዲህ ይመስላል::

ምንም ሳትነግረኝ፣ ያሰበችውን ሁሉ የማውቅ ልዩ ድንቅ ፍጡር የሆንኩ ይመስል በዝምታ የተጣጠፈ ወረቀት ሰጠችኝ:: በዚያ ወቅት ፊቷ ላይ ወገግ ብሎ የፈካው የኩራት መንፈስ ባደረገው ጥሩ ነገር የተመሠገነ አንድ ፍሬ ልጅ ላይ የሚታየውን ይመስል ነበር:: ወረቀቱን ዘረጋሁት:: አንድ የሕክምና ተማሪ የፃፈላት ደብዳቤ ነበር:: ደብዳቤው በጥራዝ ነጠቅ ቃላት የተሞላ፣ አፃፃፉም መራቀቅ የሚከጅለው ቢሆንም እንኳን፣ ትሕትና የተሞላበት የፍቅር ደብዳቤ ነበር:: ያነበብኩትን በትክክል ባላስታውሰውም፣ ሊያስመስሉት ከማይቻል እውነተኛ የውስጥ ስሜት የፈለቀ እንደነበር ማወቁ ትዝ ይለኛል:: አንብቤ ስጨርስ በዕረፍት ማጣት የሚቁነጠነጡ ዓይኖቿ ለገለፀችልኝ ምሥጢር ምላሽ እንድሰጥ በጉጉት ሲጠብቁኝ አየሁ:: እንዴትና የት እንዳገኘችው አጠር አድርጋ ደስ እያላት ነገረችኝ:: «ከቤተሰብ ቤት፣ ጥሩ ሰዎች፣ ማንም ገና ምንም መጥፎ ነገር ከማያውቅበት » አለችኝ::

«እየሀ እዚህ ገና አዲስ ነኝ:: ብቻ እንትኑን . . . እዚህ እቆያለሁ ብዬ አላስብም:: እሄዳለሁ፣ ዕዳዬን ከፍዬ እንደጨረስኩ:: ከዚያ ለግብዣ ከሄድኩበት ቤት አንድ ተማሪ ነበር:: ከኔ ጋር ስንደንስና ስናወራ አመሸን:: ኋላ በወሬ በወሬ ሪጋ ሳለሁ እንደሚያውቀኝ ነገረኝ:: ሁለታችንም ልጆች ሳለን:: አብረን እንጫወት ነበር:: ድሮ::

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤተሠቦቼንም ያውቃቸዋል:: ስለአሁኑ ኑሮዬ ግን ምንም አያውቅም:: እዚያ አብራኝ ሄዳ በነበረች ጓደኛዬ በኩል በማግስቱ ይህን ደብዳቤ ላከልኝ:: እና . . . እንደዚህ ነው::»

ትረካዋን እንደጨረሰች እንደማፈር ብላ ዓይኗን ሠበረች:: ምሥኪን፣ የዚያን ተማሪ ደብዳቤ ድንቅና ብርቅ ነገር የሆነ ይመስል በጥንቃቄ አስቀምጣዋለች:: እሷም እንደሌሎቹ በእውን ያፈቀራትና በአክብሮት የተመለከታት ሰው መኖሩን ሳላውቅ እንዳልሄድ ስትከንፍ ሄዳ ያንን ደብዳቤ አምጥታ አሳየችኝ:: ምናልባት ደብዳቤው ለፍሬ ሳይበቃ ከሳጥኗ ተቀምጦ ሊያረጅ ተፈርዶበት ይሆናል:: ያ ቢሆንም እንኳን ዕድሜ ልኳን አለኝ የምትለው የአንድ ወቅት ምንነቷን መሥካሪ ቅርሷ አድርጋ እነደምትቆጥረው እርግጠኛ ነኝ:: ምንም አልተናገርኩ:: በዝምታ እጇን አጥብቄ ጨበጥኩና ወጥቼ ሄድኩ:: ለማምለጥ እጅግ ቸኩዬ ነበር . . . በረዶው አሁንም ይወርዳል:: ወደቤቴ መንገዴን በእግሬ ተያያዝኩት:: ደክሞኛል፣ ቅሥሜ ተሠብሯል፣ ግራ ገብቶኛል:: በዚህ ሁሉ መሃል ግን አስቀያሚው እውነት ጭንቅላቱን ብቅ እያደረገ አለሁ ይለኝ ነበር::



ይህን ክስተት ግን በቀላሉ አልተቀበልኩትም:: ለሰዓታት ጭልጥ አድርጎ ከወሰደኝ እንቅልፍ ተላቅቄ ዓይኖቼን እንደገለጥኩ፣ ትናንት የተፈፀመው ሁሉ ትዝ አለኝ:: ለሊዛ ስቀባጥርላት የነበረው ዝባዝንኪና የተረተርኩላት ጉድ ሲታወሰኝ ራሴን ጠላሁት:: ወፈፍ ያረጋት አሮጊት ይመስል ያልጠየቁኝን ስወሻክት:: « አድራሻዬን

t.me/OLDBOOKSPDF

ምን ሲያቀብጠኝ ነው የሰጠኋት? ብትመጣ ምን ሊውጠኝ ነው? እንዲያውም . . . ትምጣ! ምን ቸገረኝ፣ የራሷ ጉዳይ ነው:: አሁን ዋናው ነገር ሌላ ነው:: ትናንት የቀበርኩትን ክብርና ማንነቴን ከሲሞኖቭና ከአዝቤርኮቭ ፊት ሂጄ ለመመለስ መጣደፍ አለብኝ!» እያልኩ ሳስብ የሊዛን ነገር ለጊዜው ረሳሁት::

መጀመሪያ ከሲሞኖቭ ትናንት ማታ የተበደርኩትን ገንዘብ ባስቸኳይ መመለስ ይገባኛል:: ለዚህም ሲጨንቀኝ የፈጠርኩት መላ ከአንቶን አሥራአምስት ብር መበደር ነበር:: ዕድሌ ሲቀና አንቶን የዚያን ቀን ጧት በቀኝ ጎኑ ተነስቶ ኖሮ፣ ብድሩን እንደጠየቅኩት እሺ አለኝ:: በዚህ ባላሰብኩት መልካም አጋጣሚ ተደስቼ የውሉን ወረቀት እየፈረምኩ ሳለሁ፣ ከጓደኞቼ ጋር ፓሪስ ሆቴል እንዳመሸሁ ነገርኩት:: « አንድ ጥሩ ጓደኛዬ፣ አብሮ አደጌን ልንሸኝ:: ተንቀባርሮ ያደገ፣ ብዙ የለመደ ነው ይህ ጓደኛዬ:: ጥሩ ቤተሰቦች አሉት፣ የታወቁ ባለፀጎች:: እሱም ከፍ ያለ ሥራ ነው ያለው:: ብታየው እንዴት አይነት አስተዋይና ተጫዋች መሠለህ:: የቆነጃጅት ነገር ግን አይሆንለትም:: እና እሱን ልንሸኝ ተሰባስበን ከልክ በላይ ጠጣን፣ » ብዬ ሳላፍር ለአንቶን ወሽክትኩለት፤ ሳይከብደኝ፣ በማንነቱ ያልተከፋ ሰው መስዬ:: ከቤቴ እንደደረስኩ ወዲያው ለሲሞኖቭ ደብዳቤ ፃፍኩ:: የዚያ ደብዳቤዬን ለዛና ቅንነት እስካሁን ድረስ በመደነቅ አስታውሰዋለሁ:: ወዲያ ወዲህ ሳልል፣ በኩራት፣ ጥራዝነጠቅ ቃላት ሳልጨምር፣ ለተፈጠረው አጉል ነገር ሁሉ ጥፋተኛው እኔ መሆኔን አመንኩ:: ለጥፋቴ ምክንያትም መጠጥ ያልለመደ አንጎሌ በአልኮል ተመርዞ እንደሆነና፣ ከአሥራአንድ ሰዓት ጀምሮ ይመጣሉ ብዬ ኪፓሪስ ሆቴል ቆሞ ብዬ ስጠብቅ የጠጣኋት የመጀመሪያዋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብርጭቆ ( ፍጥር አድርጌ ) ራሴ ላይ ስለወጣችብኝ መሆኑን ጠቀስኩ:: የይቅርታ ጥያቄዬን በቀጥታ ለሲሞኖቭ አቅርቤ፣ ይህንኑ እሱ ለሌሎቹ እንዲያስተላልፍልኝ አሳሰብኩት፤ በተለይም ለሲሞኖቭ:: ሲሞኖቭን « ሳልዘልፈው እንዳልቀረሁ የሰነበተ ሕልም ያህል ትዝ ይለኛል » ብዬ ፃፍኩ:: ወደ መጨረሻውም ላይ እያንዳንዳቸውን አግኝቼ ይቅርታ ብጠይቃቸው በወደድኩ፤ ሆኖም ግን ራሴን ስላመመኝና ከዚያም በላይ በሥራዬ ስላፈርኩበት ያን ማድረግ እንደማልችል ገለፅኩ:: ከሌላ መንገድና ምክንያት ከመደርደር የተሻለ በመሠለኝ አፃፃፌ ነፃነትና አልፎ አልፎ በሚታይበት ተገቢ ግዴለሽነት ደስ ብሎኝ፣ ያለፈው ምሽት ምንም ሊገረሙበት የማይገባ ተራ ነገር እንደሆነ አስመሰልኩት:: ደብዳቤዬን ሲያነብቡ፣ አስበውት እንደነበረው በተፈጠረው ነገር አፍሬ ጣይዋን ማየት ተስኖኝ የተቀመጥኩ እንዳይመስላቸው፣ የትናንት ማታውን መቃቃር የምመለከተው ማንም ራሱን የሚያከብር ሰው ሊያየው እንደሚገባ አድርጌ መሆኑን እንዲረዱልኝ ስል ደብዳቤዬን ደመደምኩ:: «ጨዋ ሰው አልፎ አልፎ ይሳሳታል » አልኳቸው::

አፃፃፌ የጌትነት ለዛ ያለው መሠለኝ:: እያነበብኩት ሳለሁ ይህን የመሠለ ደብዳቤ መፃፍ የቻልኩት የተማርኩና የሠለጠንኩ ሰው በመሆኔ ነው ስል ራሴን አሞካሸሁት:: ከፊቴ በተጋረጠው አጋጣሚ ሌሎች ቢወድቁ ኖሮ ራሳቸውን እንዲህ በጥበብ ማውጣት ያስቸግራቸው እንደነበር እርግጠኛ ነበርኩ:: ግን ለመሆኑ ትናንት እንደዚያ የሆንኩት በመጠጡ ምክንያት ሳይሆን ይቀራል? ህም . . . አይ አይመስለኝም:: እነሱን ስጠብቅ የቀመስኩት ነገር አልነበረም:: ያንን ምክንያት ሳቀርብ እየዋሸሁ ነበር፣ እፍረቴን ሸጭ

t.me/OLDBOOKSPDF

እየወሻከትኩ:: አሁንም ቢሆን በዚያ አላፍርም:: የሆነ ሆኖ ግን ሁሉም የራሱ ጉዳይ! ዋናው ነገር ከወደቅኩበት ማጥ መውጣቴ ነው::

ከደብዳቤው ጋር ስድስት ብር ጨምሬ አሸግኩና ለሲሞኖቭ እንዲያደርስልኝ ፖስታውን ለአፖሎን ሰጠሁት:: ፖስታውን ገንዘብ እንደያዘ ስነግረው አፖሎን መወጣጠሩን ትቶ ሊያደርስልኝ ፈቀደ:: እኔም ሲመሻሽ አየር ለመቀበል ወጣ አልኩኝ:: ትናንት የሆነው ነገር ሁሉ እስካሁን ጭንቅላቴን እውኮታል:: ምሽቱ እየገፋ ሲሄድና ጨለማው ሲከብድ፣ መንፈሴም መረበሽ ጀመረና ሃሣቤንም አመሠቃቀለው:: አንዳች ነገር ከውስጤ፣ ከኅሊናዬ፣ ከልቤ ጓዳ ተቀምጦ እየተላወሰ እረፍት ነሳኝ፣ አስጨነቀኝ:: ትርምስ በሚበዛበት የገበያ ሠፈር፣ በሜስቻንስካያና በሳዶቫያ ጎዳና፣ እንዲሁም በዩሱፖቭ መናፈሻ ከሰው እየተጋፋሁ አዘግም ጀመር:: ደንገዝገዝ ሲል በእነዚህ ጎዳናዎች መንጎራደድ እጅግ ደስ ያሰኘኝ ነበር፤ ሰው ሁሉ ሲታክት ከዋለበት ደክሞት ወደቤቱ እየገሠገሠ እንደጉንዳን ሲርመሠመስ:: ለነገሩ የምሄደውም ይህንኑ ትርምስምስና መጓነጥ እየፈለግኩ ነበር:: አሁን ግን ይህ ዘወትር የምወደው ሁካታና ጋጋታ በጠበጠኝ:: ራሴን መቆጣጠር ተሳነኝ:: ጭንቀት የፈጠረብኝን ነገር ፈልጌ አጣሁት:: አንዳች ነገር ከውስጤ ገንፍሎ ለመውጣት እየተናነቀኝ ሰላም ነሳኝ:: የፈፀምኩት ትልቅ ወንጀል ያለ ይመስል ተረብሼ ከቤቴ ተመለስኩ::

ሊዛ እኔን ፍለጋ ከቤቴ ልትመጣ እንደምትችል ባሰብኩት ቁጥር የማደርገው ቅጡ ይጠፋብኛል:: ሌላውን ሁሉ ነገር የራሱ ጉዳይ ብዬ ሲመሻሽ ትቼው ነበር፤ ለሲሞኖቭ የፃፍኩት ደብዳቤ አስደስቶኛል:: የሊዛ ነገር ግን ነፍሴን አወካት:: « ብትመጣስ? » እያልኩ እጨነቅ ጀመር:: ታዲያ ምን ይሁን? ትምጣ! ህም . . .

t.me/OLDBOOKSPDF

ብትመጣ ግን ቀሊት ነው . . . እንዴት እንደምኖር ታያለች:: ትናንት እንደዚያ ሁሉ እንደሞላለት ሰው ከፊቷ ስቀናጣ . . . አሁን . . ህም! ራሴን እኮ ችላ ብዬዋለሁ:: የቤቴ ጭልምልምነት፣ የወላለቀች ሶፋዬ ውስጥ አንጀቷ በየቀዳዳው ብቅ ብቅ ብሎ፣ በወገ እርቃኔን የማይሸፍነው የቤት ልብሴ፣ ድሪቶ:: ከመጣች ሁሉንም ታየዋለች:: ያን አፖሎንንም:: እሱ ደግሞ እኔን ያዋረደ መስሎት በነገር ይለከፋት ይሆናል፣ ርጉም ከብት! እኔም ያ ሲሆን በፍርሃት ዱብ እንቅ ማለት እጀምራለሁ፣ በድሪቶዬ ተጠቅልዬ ፈገግ እያልኩ መዋሸት:: ኧረ ወዲያ! አስቀያሚ ነገር! ያ ብቻ አይደለም፣ ከዚያም የባሴ ዘቅዛቃ፣ ወራዳ ነገር አለ:: እንደገና የሽፍጥ ካባዬን መደረቤ ነው . . .

ይህን በማሠቤ ብቻ ቱግ አልኩ:: ምኑ ነው ሽፍጡ? ትናንት ከልቤ ነበር የተናገርኩት:: ከውስጤ የነበረው ነው በቃላት ተጠቅልሎ ከአፌ የወጣው:: ትዝ ይለኛል:: የፈለግኩት የሊዛን ከቡር መንፈስ ከሚያንቀሳቅሱበት መቀስቀስ ነበር:: በዚያ ሳቢያ ጥቂት ብታለቅስም ይበጃታል እንጂ አይጎዳትም:: ሆኖም ግን መረጋጋት ተሣነኝ:: እቤቴ ከተመለስኩ በኋላ፣ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ቀኩል ሆኖ፣ በዚያ ሰዓት ሊዛ እንደማትመጣ እያወቅኩ አእምሮዬ ሊላቀቃት አልቻለም:: ከሷ ጋር ካሳለፍኳቸው ሰዓታት ሁሉ፣ ልሄድ ተነስቼ ሻማ ባበራሁበት ቅፅበት ያየሁት ሁኔታዋ፣ በጭንቀትና በፍርሃት የተገረፈ ፊቷን አደብቅ ብላ ፈገግታ ስትከልስበት፣ ያ ብቻ ነው ቁልጭ ብሎ ከዓይነ፣ኅሊናዬ የተቀረፀው:: ያኔ ታዲያ ከአሥራአምስት ዓመታት በኋላ እንኳን ሊዛን የማስታውሳት በነዚያ ጥቂት ሰኮንዶች እንዳየኋት ብቻ አልመሠለኝም ነበር::

t.me/OLDBOOKSPDF

በማግስቱ ይህን ሁሉ ጭንቀትና ሥጋት እረፍት ያጣ አእምሮ ከልክ በላይ አጋኖ እንደፈጠረው ከንቱ ነገር ቆጥሬ ልረሳው ዝግጁ ነበርኩ፣ ይህን ለመሣሠለ አላስፈላጊ ጭንቀት የሚዳርገኝ በሽታ እንዳለብኝ ስለማውቅ:: « ነገርን መካብ እወዳለሁ፣ ያ ነው ችግሬ » እያልኩ ደጋግሜ ሳነበንብ፣ « ቢሆንም ግን ሊዛ መምጣቷ አይቀርም » ይለኛል ሌላ ድምፅ:: በዚህ እጅግ ከመጨነቁ የተነሳ አልፎ አልፎ ቁጣ ከውስጤ እንደገሞራ ይነዳል:: « ትመጣለች! በጭራሽ አትቀርም! » እያልኩ እጮሃለሁ ቤቴ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እየተንቆራጠጥኩ:: « ዛሬ ባይሆን ነገ እኔን ፈልጋ ከተፍ ትላለች:: የኋን ብጤ የዋህ ቅቤ ልቦች ሃሳብ መች አጥቼው:: » እንዴት እንዲህ በቀላሉ፣ ከየቦታው ለቃቅሜ በገጣጠምኳቸው ጥቂት ቃላትና የይምሠል ተቆርቋሪነቴ የሰውን ነፍስ እንደፈቃዴ ማገላበጥ ተቻለኝ?

እየቆየሁ ራሴ ቀድሜ ከኋ ዘንድ ለመሄድ አሰብኩ፣ ሄጄ እውነቱን ልነግራትና ከቤቴ እንዳትመጣ ላስጠነቅቃት:: ይህን ሳስብ ቃዲያ ብስጭትጭት ያረገኝና ሊዛን ከአጠገቤ ባገኛት የማዋርዳት፣ የምተፋባትና በጥፊ ብዬ የማባርራት ይመስለኛል::

ሳትመጣ ሦስት ቀናት ሲያልፉ ነበር መረጋጋት የጀመርኩት:: በተለይ ሲመሻሽ፣ ቀን ሲያስጨንቀኝ የዋለው የመምጣቷ ሥጋት ይለቅቀኝና ጭራሹን በሕልምና ምኞት ክንፍ እንሣፈፋለሁ:: መጥታ፣ አነጋግሬያት፣ ቀስ በቀስ ከጥፋት ሳድናት አስባለሁ፣ አእምሮዋን ሳበለፅግ፣ ሳስተምራት:: ከዚያም ትወደኛለች:: በነፍስና በሥጋዋ እንደምታፈቅረኝ እያየሁ የማላውቅ ሳስመስል፣ (እኔን ማፍቀሯን የማላውቅ መምሠሉን ለምን እንደተመኘሁት እንጃ፣ ምናልባት እንዲያ ይሆናል የሚያምረው::) በመጨረሻም እያፈረችና ማፈሯ እያማረባት፣ ጉንጮቿ በእንባ ርሠው ከእግሬ ላይ ወድቃ

t.me/OLDBOOKSPDF

አዳኟ መሆኔንና ከምንም በላይ አብልጣ እንደምታፈቅረኝ ትነግረኛለች:: እገረማለሁ:: « ሊዛ » እላታለሁ፣ « እንደምታፈቅሪኝ ያልገባኝ ይመስልሻል? ሁሉን ተረድቻለሁ:: ግን ቀድሜ የኔ ነሽ ብልሽ፣ ውለታ ለመመለስ ብለሽ ፍቅሬን ትቀበይ ይሆናል ብዬ ፈርቼ ነው እንጂ:: በነገሮች ተገድደሽ ከልብሽ ውስጥ የሌለ ስሜትን ለመፍጠር እንዳትሞክሪ ብዬ ነው:: አየሽ፣ ያ እንዲሆን አልፈለግኩም፤ ያ ፍቅር ሳይሆን ፈላጭቆራጭነት ነው፤ ነውር ነገር:: አሁን ግን የኔ ነሽ፣ ኮትኩቼ ያሳደግኩሽ ፅጌረዳ፤ ንፁህ፣ የተዋብሽ ሚስቴ ነሽና ታዝርበት ዘንድ ከጎጆዬ ሰተት ብለሽ ግቢ:: »

ከዚያም ደስታ የሞላበት ትዳር እንመሠርትና አገር ለማየት ባህር ማዶ እንጓዛለን፣ ወዘተ . . . . ወዘተ . . . :: ባጭሩ ይህን በመሠለ የቅዠት ፈረስ በሩቁ ሽምጥጬ ሲወጣልኝ ቋቅ ይለኝና በራሴ ላይ ምላሴን አወጣለሁ::

ሊዛን እመቤቷ የምትለቃት አይመስለኝም:: ብዙ እንዲወጡ አይፈቅዱላቸውም፤ በተለይ በምሽት:: እሷ ግን ነፃነቷን ጠቅልላ እንዳላስረከበች ነግራኛለች:: ገና ያልነፈጓት መብቶች አሏት:: ያ ማለት ትመጣ ይሆናል . . . ህም፣ አትቀርም!

አፖሎን ነበር ከዚህ ሃሳቤ ያላቀቀኝ:: አፖሎን ፈጣሪ ለቅጣት የላከብኝ ርግማኔ ነው:: ለዓመታት ሳናሰልስ ተነታርከናል:: አምርሬ ነው የምጠላው:: እሱን የምጠላውን ያህል ሰው በህይወቴ ጠ ልቼ አላውቅም::

አፖሎን ጠና ያለ ሰው ነው፤ ራሱን እርስዎ ማለት የሚቃጣው የትዕቢት ቋት:: በትርፍ ጊዜው ልብስ መጠቃቀም ይወዳል:: እኔን ታዲያ በማላውቀው ምክንያት እጅግ ይንቀኛል፤ ሊታገሠው በማልችለው ዕብሪት ቁልቁል ይመለከተኛል:: ለነገሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማንንም ይንቃል:: በጥንቃቄ ተከፍሎ የተደለሰ ሉጫ ፀጉሩ የተለጠፈባት ራሱን፣ በተለይ በትጋት የሚያበጥራትና በአትክልት ዘይት የሚያርሳት ከግንባሩ በላይ ያለች ቁንጮውን፣ መጥፎ ነገር ወጥቶት አያውቅ ይመሥል ሁሉን ተጠይፎ የተገጠመ አፉን ቢመለከቱ፣ ስለራሱ ቅንጣት ጥርጣሬ ገብቶት የማያውቅ ሰው መሆኑን ያውቁታል:: በምድር ላይ እሱን የመሠለ ወግ አጥባቂና ራሱን ማክበር ቾል የማይል ሰው ያለ አይመስለኝም:: የልብሱን አዝራሮችና የጣቶቹን ጥፍሮች የሚያደንቅ ግብዝ ሰው ነው:: ጌታዬ እንጂ አገልጋዩ እንዳልሆነ ሁሉ ይበጣጠስብኛል:: ሲናገረኝ ቃላቱን ቆጥቦ ነው:: ሲመለከተኝ ዕብሪትና ንቀት ከፊቱ ላይ አነብና በንዴት እቃጠላለሁ:: የተከፈለበት ሥራውን ሲሰራ ውለታ የሚያደርግልኝ ያስመስለዋል:: ለነገሩ እኮ ምንም ያህል አይሠራልኝም፣ ሊሠራልኝም የሚገደድ አይመስለውም:: የቂሎች ሁሉ ቂል አድርጎ እንደሚቆጥረኝ አውቀዋለሁ:: ጥሎኝ ያልሄደውም በየወሩ ደሞዙን ስለምከፍለው ነበር:: በሱ ምክንያት አምላክ ብዙ ኃጢአቴን ይቅር ይለኛል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: አንዳንዴ ጥላቻዬ እጅግ ከመምረሩ የተነሳ አረማመዱን ብቻ አይቼ ኩሶ እንደጠጣ ሰው ያንገሸግሸኛል:: ከሁሉም በላይ የሚያስጠላኝ ግን መኮላተፉ ነው:: ምላሱ ከልክ በላይ ረዝሞ ስለተፈጠረ ይመሥለኛል ሲናገር እንደትንሽ ልጅ ይኮላተፋል:: ይህ ታዲያ ያማረለትና ልዩ የሚያደርገው እየመሠለው ይኩራራበታል:: ሲናገር ድምፁን ዝቅ አድርጎ፣ እጆቹን ከኋላው አጣምሮ ምድር እያስተዋለ ነው:: በተለይ ከወንበሩ ላይ ተቀምጦ ዳዊት ሲደግም ስሰማው እንዴት እንደሚያናድደኝ መግለፅ ያቅተኛል:: በዚህ ምክንያት ብዙ ጊዜ ብንጣላም በጨለማ ዳዊት መድገሙን አላቆመም:: ድምፁን ከፍ አድርጎ ቃላቱን እየጎተተ፣ ፍትሐተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሙታን የሚያደርስ ይመስል ማዜም እየቃጣው ዳዊት ማንበብ አጥብቆ ይወዳል:: የሚገርመው ታዲያ ዛሬ የተመኘው ደርሶለት ዘመድ የሞተባቸው ሰዎች ዳዊት እንዲደግምላቸው ይቀጥሩታል:: ከዚያም አልፎ አይጥ በማጥፋትና የጫማ ቀለም በመሥራት ተክኖ ባለብዙ ሙያ ሆኗል::

የኔ አገልጋይ ሆኖ ሳለ፣ እንደዚያ እየጠላሁት ሳባርረው ተስኖኝ ነበር፤ ያለሱ መኖር የማልችል ይመስል:: ውጣ ብለውም ኖሮ በምንም መንገድ ሊወጣልኝ የሚስማማ አይመስለኝም:: እኔም ያኔ የተሟላ ቤት ውስጥ ለመኖር አቅሙ አልነበረኝም:: ያች ቤቴ ከሰው ሸሽቼ የምወተፍባት ዋሻዬ ነበረች:: ታዲያ አፖሎንም የቤቴ አካል ሆነና ለሰባት ዓመታት ተቆራኝቶኝ ኖረ::

ደሞዙን ለሁለት ወይም ለሦስት ቀናት ማዘግየት የማይታሰብ ነበር:: ሳልከፍለው አንድ ቀን ሲያልፍ ማድረግ የሚጀምረው ነገር መግቢያ ቀዳዳ እስከማጣ ድረስ ያስቃየኝ ነበር:: ሊዛን ባገኘሁበት ዕለት የተፈፀመው ነገር ሁሉ መንፈሴን መርዞት ስለነበር የአፖሎንን ደሞዝ ለሁለት ሣምንት አዘግይቼ ልቀጣው ወስኜ ነበር:: ይህን ማሠብና ማድረግ ከጀመርኩ ሁለት ዓመት ሆኖኛል፤ እኔ ላይ መጨማለቁን እርግፍ አድርጎ እንዲተው ትምህርት ልሰጠውና ከፈለግኩ ክፍያውን ማቆየት መቻሌን ላሳየው:: ለምን ደሞዙን እንደማልከፍለው ላልገልፅለትና አውቄ ዝግት አድርጌው፣ ኩራቱን ረግጬ እሱ ቀድሞ እንዲጠይቀኝ ላስገድደው:: ከሳጥኔ ሰባት ብር አውጥቼ ገንዘቡ እንደነበረኝ ላሳየውና ብሩ እያለኝ ሳልከፍለው የቀረሁት እንዲሁ ልከፍለው ስላልፈለግኩ፤ ጌታው እንደመሆኔ መጠን ለጊዜው አለመክፈል ስለመረጥኩ፤ ይህን ያደረግኩትም አክብሮት የራቀው ባለጌ በመሆኑና በትህትና እንድከፍለው ቢጠይቀኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምናልባት በድርጊቴ ተፀፅቼ እንደምሠጠው፤ ካልሆነ ግን ሌላ ሁለት፣ ሦስት ወይም አራት ሣምንታት እንደሚጠብቅ ላረጋግጥለት . . .

እንደዚያ አምርሬ ልቀጣው ስሮክር ቆይቼ ድሉ በመጨረሻ የሱ ሆነ:: አራት ቀን ሳይሞላኝ ተሸነፍኩኝ:: ሁሌ ደሞዙ ለጥቂት ቀናት ሲዘገይበት የሚያደርገው ነገር ነበረው፤ ( ይህን ቀድሞ ብዙ ጊዜ ስለሞከርኩት ጠንቅቄ አውቀዋለሁ::) በመጀመሪያ፣ ፊት ለፊት በተገናኘን ቁጥር ተኮሳትሮ ለረጅም ጊዜ ያስተውለኛል:: እንደምንም ብዬ ይህን አስተያየቱን ልብ ያላልኩ ከመሰልኩ፣ ዘዴውን ይለውጥና ያለምክንያት ከክፍሌ ውስጥ በዝግታ እየተራመደ ገብቶ በሩ አጠገብ ይቆምና አንድ እጁን ከኋላው አድርጎ እያነበብኩ ከተቀመጥኩበት፣ ወይም ወዲያ ወዲህ ስንቆራጠጥ በንቀት ይመለከተኛል:: ምን እንደፈለገ ስጠይቀው አይመልስልኝም፤ ተለጉሞ ሲያፈጥብኝ ይቆይና ሲበቃው አፉን ጥብቅ አድርጎ ገጥሞ፣ በርጋታ ወጥቶ ወደክፍሉ ይሄዳል:: ይህን ካደረገ ከሁለት ወይም ሦስት ሰዓት በኋላ እንደገና መጥቶ ከፊቴ ይገተራል:: አንዳንዴ ብስጭት ሲያቃጥለኝ ለምን ከፊቴ እንደቆመ ሳልጠይቀው ጭንቅላቴን በድንገት ወንጭፌ ቀና አደርግና መልሼ አፈጥበታለሁ:: በዚህ አይነት ለሁለት ደቂቃዎች ያህል እንፋጠጥና እሱ ቀድሞ እየተጀነነ ሲወጣልኝ ለጥቂት ሰዓቶች እረፍት አገኛለሁ::

ይህ ድርጊቱ ሃሣቤን ሳይለውጠው ቀርቶ እምቢተኝነቴን ከቀጠልኩ፣ በማፍጠጡ መሐል በረጅሙ መተንፈስ ይጀምራል፤ የነሊናቢስነቴን መጠን ገምግሞ ተስፋ የመቁረጥ ዓይነት ትንፋሽ:: ከዚያም ፀጉሬን ነጭቼና ስሬ እስከሚገታተር ጮሄ፣ ገንዘቡን ወርውሬለት መገላገል እመርጣለሁ::

t.me/OLDBOOKSPDF

አሁን ገና ያን የፍጥጫ ጨዋታውን ሊጀምር ከክፍሌ መሠስ ብሎ ሲገባ ቱግ ብዬ በቁጣ ተቀጣጠልኩ:: እሱ ሳይጨመርብኝም በቋፍ ነበር ያለሁት::

«ቆይ! » ብዬ ጮህኩበት ጉሮሮዬ እስከሚሠነጠቅ፤ እንደልማዱ ከናፍሩን ቆልፎ፣ አንድ እጁን ከቂጡ ላይ አሳርፎ ሊወጣ ሲል::

« ቆይ! ና እዚህ! ተመለስ ነው የምልህ! » ፊቼኹቴ አስደንቆት በመገረም ተመለከተኝ:: አንዲት ቃል አለመተንፈሱ ብስጭቴን አባሰው::

« ፈቃድ ሳትጠይቀኝ ዘው ብለህ ገብተህ ለምንድነው የምታፈጥብኝ? መልስልኝ! »

ፍንክች ሳይል ለግማሽ ደቂቃ ያህል በዝምታ አጥንቶኝ እንደገና ሊወጣ ሲቃጣው:-

« ቆይ እኮ ነው የምልህ! » ብዬ አንጋራሁና ተንደርድሬ ከፊቱ ቆምኩ:: « ከዚች ቦታ እንዳትነቃነቅ! አዎ፣ እዚሁ ቆይ! ብል አሁን መልስልኝ:- ምን እያለሁ ብለህ ነው እዚህ የምትመጣው? »

« የምታዝዘኝ ካለ የኔ ግዴታ መቀበል ነው፣ » አለኝ ጥቂት ቆይቶ:: ድምፁን ለስለስ አድርጎ፣ ፊቱን የምፀት ፈገግታ አልብሶ፣ ቅንድቦቹን ሽቅብ ቀስሮ፣ ራሱን ግራና ቀኝ እየነቀነቀ::

« ያን ማን ጠየቀህ? እሱን መች ጠየቅኩህ አንት አረመኔ!» ብዬ አናፋሁበት ሰውነቴ እየተንቀጠቀጠ:: « የመጣህበትን እኔው እነግርሃለሁ፣ አንት ርኩስ! የምትመላለሰው ደሞዝህን ስላልሰጠሁህ ነው:: እንዳትጠይቀኝ ጥጋብህ ወጥሮ ይዞሃል፤ ለዚህ ነው እዚህ ጥልቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

እያልክ እንደእብድ አፍህን ለጉመህ እያፈጠጥክ ልትቀጣኝ የምትሞክረው!»

አሁንም በፀጥታ ሊወጣ ሲል ክንዱን አፈፍ አድርጌ አቆምኩት:: « ስማ! ገንዘቡ ይኸው፣ አየህ? ሳይኖረኝ ቀርቶ አይደለም » ብዬ ብሩን ከሣጥኔ አውጥቼ አሳየሁት:: « ይኸው ሰባት ብር አስቀምጫለሁ:: ግን አታገኘትም:: ጥፋትህን አምነህ ይቅርታ እስከምትጠይቀኝ ድረስ አልሰጥህም! ሰማኸኝ? »

« ያ በጭራሽ አይሆንም! » አለኝ ቁርጥ አድርጎ

« ይሆናል! ለማየት ያብቃህ:: »

« ይቅርታ የሚያስጠይቅ ጥፋት አልሠራሁም » አለኝ የኔን ጩኸትና ዱብ እንቅ ከጉዳይ ሣይቆጥረው:: « እንዲያውም አንተ ነህ 'ርኩስ' 'አረመኔ' ብለህ የሠደብከኝ:: ከፈለኩ በዚህ ምክንያት ልከስህ እችላለሁ:: »

« ለምን አሁን አትሄድም? ሂድ ክሰሰኝ! አሁኑኑ:: ማን ያዘህ? ከፈለግክ ደግሜ እሰድብሃለሁ:- ርኩስ! አረመኔ! ርኩስ! አረመኔ! » ወፈፍ እንዳረገው ሰው ስለፈልፍ ጥሎኝ ወጥቶ ሄደ::

« የዚህ ሁሉ ምክንያት ሊዛ ነች » አልኩ በልቤ:: ጥቂት ጊዜ በቆምኩበት ቆየሁና ራሴን ሰብሰብ አድርጌ በርጋታ ወደአፖሎን ሄድኩና « አፖሎን፣ ሳትዘገይ ፖሊስጣቢያ ሄደህ ክሰሰኝ » አልኩት ትንፋሽ እያጠረኝ:: ከክፍሉ እንደደረስ ከጠረጴዛው ፊት ለፊት ተቀምጠ፣ መነፅሩን አድርጎ ጨርቅ እየጣፈ ነበር:: ትዕዛዜን ሲሰማ የማንጓጠጥ ሣቅ ሣቀብኝ::

« እውነቴን ነው፣ አሁኑኑ ተነስተህ ሂድ! ካልሄድክ አጉል ነገር ይፈጠራል! »

t.me/OLDBOOKSPDF

« አሁንስ ለይቶልህ አብደሃል » አለ ከጎነበሠበት ቀና ሳይል በመርፌው ዓይን ክር እየጨመረ:: « ሰው ለመከሠስ ሲቸኩል አንተን ብቻ አየሁ:: ለማስፈራራቱ ደግሞ በከንቱ ባትደክም ይሻልሃል፣ ዋጋ የሌለው ነገር ነው:: »

« ሂድ! » ብዬ አናፋሁበት ትክሻውን ይዤ:: ጥቂት ብንቀጥል ኖሮ በጥፊ ሳላላጋው አልቀርም ነበር:: ግን በዚያች ቅፅበት ሰው ከቤቴ ገብቶ ግራ በመጋባት እያስተዋለን ስለነበር ቀና ብዬ ስመለከት በሃፍረት መላ አካሌ ደነዘዘ:: ፈጥኜ ወደክፍሌ ተመለስኩና ፀጉሬን በእጆቼ ጨምድጄ ይዤ፣ ግድግዳውን ተደግፌ በቆምኩበት ደርቄ ቀረሁ::

ወዲያው አፖሎን ዝግ ብሎ ከክፍሌ ገባና « ሰው ይፈልግሃል » አለኝ ፊቱን አኮሳትሮ:: ከበሩ ገለል ብሎ ሊዛን አሳለፋት:: እሷ ከገባች በኋላም ለመውጣት ሳይቻኮል በንቀት ይመለከተን ጀመር::

« ውጣ! ሂድ ከዚህ » አልኩት የምንተእፍረቴን:: ወጣ::

ሊዛ ቃሏን ጠብቃ መጥታለች:: እኔም ተዋርጄ፣ ሃፍረት ተከናንቤ፣ ያኔ ከፍቶኝ ሳስበው እንደነበረው በድሪቶ ተጠቅልዬ፣ ሠቀቀኔን በፈገግታ ልደልሰው እየታገልኩ ከፊቷ ቆሜያለሁ:: ሊዛ ራሷ ሁኔታዬን ተመልክታ ተሳቀቀች::

« ተቀመጭ » አልኳትና ወንበሩን ጎትቼ ከጠረጴዛው አጠገብ አስጠጋሁት:: እኔ ከሶፋው ላይ ተቀመጥኩ:: ተቀምጣ እንዳነጋግራት ትጠብቅ ጀመር:: በዝምታ ምን እንደምላት ለመሥማት መቀመጧ ቢያናድደኝም ራሴን እንደምንም ተቆጣጠርኩት::

t.me/OLDBOOKSPDF

ከቤቴ ያየችው ሁሉ መሆን እንደሚገባው ስለነበር ባይገርማት ይሻል ነበር፤ ነገር ግን . . . ለዚህ ሁሉ ዋጋዋን ጥሩ አድርጌ ሳልከፍላት እንደማልቀር ዛትኩ::

« አጉል ሁኔታ ላይ አገኘሽኝ ሊዛ » አልኳት አፌ እየተሳሰረብኝ:: የዚህን አላግባብነት ወዲያው ተረዳሁት::

« እንደምታስቢው አይደለም፣ ሌላ ነገር አይምሰልሽ! » ብዬ ጮህኩባት ፊቷ ሲቀላ ተመልክቼ:: « በድህነቴ አላፍርበትም . . . እንዲያውም እኮራበታለሁ:: በርግጥ ድሃ ነኝ፣ ግን ክብሬን እጠብቃለሁ:: አየሽ፣ ሰው ድህነቱን ከክብር ጋር መያዝ ይችላል:: በነገራችን ላይ . . . ሻይ ላምጣልሽ? »

« አይ . . . »

« መጣሁ ጠብቂኝ » ብዬ ወደ አፖሎን ዘንድ ሮጥኩ፤ ከፊቷ የምጠፋበት ሠበብ አግኝቼ::

« አፖሎን! » አልኩት ድምፄን ዝቅ አድርጌ፣ እየተርበተበትኩ:: በጭብጤ የነበረውን ሰባት ብር ወረወርኩለት:: «ያውልህ ደሞዝህ:: አየህ? ሰጥቼሃለሁ:: አንተ ደግሞ በምላሹ ተነስና ሱቅ ሂደህ ሻይና ብስኩት ግዛልኝ:: እምቢ እንዳትለኝ፣ አደራ:: ሕይወቴን እንዳታበላሸው:: ምን ዓይነት ሰው እንደሆነች ሳታውቅ ሌላ ነገር አታስብ:: »

አፖሎን እንደተመለሠ መነፅሩን አድርጎ እንደገና ሥራውን ቀጥሎ ነበር:: መጀመሪያ መርፌውን በእጁ እንደያዘ ብሩን በዝምታ ተመለከተው:: ቀጥሎም ከፊቱ ያልቆምኩ ይመስል መልስ ሳይሰጠኝ ስፌቱን ቀጠለ:: እጄን አጣጥፌ ቆሜ ለሦስት ደቂቃ ያህል ጠበቅኩት:: ግንባሬ በላብ ተጠምቋል፤ በጭንቀት እንደገረጣሁ ይታወቀኛል:: አፖሎን በመጨረሻ አዘነልኝ፣ ከተቀመጠበት እየተለጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠ ብድግ ብሎ ወንበሩን አስተካከለና ደሞዙን ቆጥሮ አስቀምጦ ወጥቶ ሄደ:: ወደ ሊዛ እየተመለስኩ ሳለሁ ድሪቶዬን እንደለበስኩ ሾልኬ ጠፍቼ ለመገላገል ተመኘሁ::

ከሶፋው ላይ ተቀመጥኩ:: ሊዛ የምታደርገው ጠፍቷት ትመለከተኛለች:: እኔም፣ እሷም በዝምታ ተውጠናል::

« እገድለዋለሁ! » ብዬ ጮህኩ በድንገት፤ በብልቃጥ ውስጥ የነበረው ቀለም እስከሚረጫጭ ጠረጴዛውን በቡጢ ወግሬ:: « እንዴ፣ ምንድነው የምትለው! » አለች ደንግጣ::« እገድለዋለሁ፣ አልምረውም! » እንደገና አንጓራሁባት ጠረጴዛውን እየነረትኩ:: አእምሮዬን መሣት ቢቃጣኝም የእብደት መሣይ ብስጭቴ አጉልነት ይታወቀኝ ነበር::

« ይህ ርኩስ እንዴት እንደሚያሰቃየኝ አታውቂም ሊዛ:: በኔ ለመጫወት ነው የሚኖረው . . . አሁን ብስኩት ሊገዛ ሄዷል . . . እሱ . . . . »

ሳልጨርሰው እንባ አነቀኝና በድንገት ማልቀስ ጀመርኩ:: ሁኔታዬ ቢያሳፍረኝም እንባዬን መግታት አልቻልኩም::

« ምነው? ምንድነው ምክንያቱ? » አለች ሊዛ በፍራቻ ካጠገቤ ሽርጉድ እያለች::

« ውሃ፣ ውሃ ስጭኝ:: ያውልሽ እዚያ » አልኳኝ በደከመ ድምፅ፣ አቅም ያነሰኝ መስዬ:: ውሃ እንዳላስፈለገኝና ነቃ ብዬ መናገር እንደምችል አውቀው ነበር:: የሰፈረብኝ የብስጭት ጋኔን የእውነት ቢሆንም የታከተኝና የታመምኩ ማስመሠሌ ውርደቴን ቢያቀልልኝ ብዬ ነበር::

ውሃውን አምጥታ ስትሰጠኝ፣ አፖሎን ሻይና ብስኩቱን ይዞ ከተፍ አለ:: አስቀምጦ ሲወጣ ሊዛ በፍርሃት አስተዋለችው::

t.me/OLDBOOKSPDF

« ሊዛ፣ ናቅሺኝ? » ስል ጠየቅኳት አትኩሬ እየተመለከትኳት፤ መልሷን ለመስማት ተንሰፍስፌ::

በጥያቄዬ ግራ ተጋብታ ዝም አለች::

« ሻይውን ጠጪ » አልኳት በቁጣ:: ድርጊቴ አስጠይፎኛል፤ ለቅሌቴ የምትከፍለው ግን እሷ ነች:: ውስጤ በንዴት ተቃጠለ፤ አንቄ ልገድላት የሚያስችለኝ ንዴት:: ከቤቴ ወጥታ እስከምትሄድ ድረስ አንዲት ቃል ሳልተነፍስ ልበቀላት አሰብኩ::

በዝምታ አምስት ደቂቃ ያህል ቆየን:: ሁለታችንም ሻይውን አልነካነውም:: ስላበሳጨችኝ ሻይውን ቀድሜ ባለመቅመስ እንድትጠጣ ላልጋብዛት ወሰንኩ:: በዝምታ እንደተቀመጥኩ አልፎ አልፎ በጭንቀት ታየኝ ነበር:: አፌን ለጉሜ አላናገርኳትም:: የብልግናዬ ልክ ማጣትና የድርጊቴ ከይሲነት ቁልጭ ብሎ እየታየኝ ሳለ ራሴን መመለስ አቃተኝ::

« ከዚያ ቤት . . . ጨርሼ ለቅቄ . . . . ለመውጣት እፈልጋለሁ » ስትል ጀመረች ሊዛ ዝምታውን ለመግፈፍ ብላ:: ምስኪን:: ይህ ማንሳት የሌለባት ነገር እንደነበረ አላወቀችም፤ እንደኔ ላለ ነውረኛ ሰው:: እንደዚያ የከፋት መርዝ ውስጤን አጥለቅልቆት እንኳን ላንጻፍታ አሳዝናኝ ነበር:: ሳይቆይ ግን ሃዘኔ በጭካኔ ተወርሶ፣ መልስ እንዳልሰጣት አፌን ሸብቦ አስቀመጠኝ::

« አስቸገርኩህ እንዴ? » አለችና ፈራ ተባ እያለች ልትነሳ ስትል፣ የረገጥኩባት የራስ ክብሯን ለመሠብሰብ መሞከሯ መሆኑ ገባኝና በቁጣ ሞገድ እንቀጠቀጥ ጀመር::

« እስቲ ንገሪኝ፡- ምን ፈልገሽ ነው የመጣሽው? » አልኳት ትንፋሽ እያጠረኝ:: የተሰማኝን ሁሉ ባንድአፍታ ዘክዝኬባት ብገላገል ደስ ባለኝ ነበር:: ከየትና እንዴት እንደምጀምር ግን አላወቅኩም::

t.me/OLDBOOKSPDF

« ለምን መጣሽ? መልሺልኝ! ለምን እንደመጣሽ ልንገርሽ? ያኔ በለፈለፍኩልሽ ማፈሪያ ነገር ተሞኝተሽ ነው:: ልብሽን ነካክቼው፣ ጨምሬ እንድቀባጥርልሽ:: ያኔ በሆዴ ስስቅብሽ ነበር፣ አሁንም እየሳቅኩብሽ እንደሆነ እወቂ:: ምን ያሳቅቅሻል? እውነቴን ነው፣ መሳቂያዬ ነሽ:: ያኔ አንችን ከማግኘቴ በፊት መጥተው የነበሩት ሰዎች ራት ስንበላ ሰድበውኝና አዋርደውኝ ስለነበር እዚያ የመጣሁት ከመካከላቸው አንደኛውን ልደበድበው ነበር:: አልሆነልኝም፤ ሳልደርስ አመለጡ:: የታመቀ ምሬትና ብሶቴን የማራግፍበት ሰው ስፈልግ አንቺ ተገኘሽ:: እልሄን አንቺ ላይ ልወጣ ወሰንኩና ቀለድኩብሽ:: ተረግጬ ስለነበር እኔም ሰው መርገጥ አምሮኝ ነበር:: እንደውዳቂ ነገር ተቆጥሬ ስለነበር እኔም ሌላ ፍጡር ላይ የበላይነቴን ማሣየት ግዴታዬ ነበር:: ይህ ነው ምክንያቱ:: አንቺ ታዲያ በእርግጥ ከጥፋት አዘቅት ላወጣሽ የተላኩ መሰለሽ፣ አይደል? »

ይህ ንግግሬ ግራ እንደሚያጋባትና አጥርታ ምንነቱን ለማየት እንደሚያቅታት ባስብም፣ የሁኔታዬን አቅጣጫ በደፈናው እንደተረዳችው አውቄያለሁ:: በድንጋጤ ፊቷ አመድ ለበሰ፤ ለመናገር ፈልጋ ከንፈሮቿ ቢላወሱም፣ ካፏ ድምፅ አልወጣም:: ከሥሯ በመጥረቢያ የቆረጧት ይመስል ከወንበሩ ላይ ተመልሳ ዘፍ አለች:: ተቀምጣ ሰውነቷ እየተብረከረከ አፏን ከፍታ ታዳምጠኝ ጀመር::

« ላድንሽ! » ስል ቀጠልኩ ብድግ ብዬ ወዲያ ወዲህ እየተመላለስኩ::

« ከምንድነው የማድንሽ? የራሴ ርግማን ካንቺ ሳይብስ ቀርቶ ይመስልሻል? ያኔ ልምክርሽ ብዬ ስመፃደቅ ለምን ልኬን አትነግሪኝም ነበር? 'አንተ ራስህ ምን ፈልገህ መጣህ? ሥነምግባር ልታስተምረኝ?

t.me/OLDBOOKSPDF

' አትይኝም ነበር? ያኔ የተጠማሁት ፈላጭ ቆራጭነት ስለነበር ነው በነፍስሽ የቀለድኩባት፤ ከተደበቅሽበት አውጥቼ እርቃንሽን ላቆምሽ፣ ላስነባሽ፣ በፀፀት ፀጉርሽን ላስነጭሽ፤ ያን ብቻ ነበር የፈለግኩት:: ምን አቅብጦኝ አድራሻዬን እንደሰጠሁሽ አላውቅም:: ያን በማድረጌም ገና እቤት ሳልደርስ ስረግምሽ ነበር:: ስለዋሸሁሽ አስጠ ላሽኝ:: የሚሳካልኝ ነገር ወሬ ማሳመር፣ በቃላት መጫወትና በምኞት መስከር ብቻ ስለሆነ:: በርግጥ ማን ምን እንደምፈልግ ታውቂያለሽ? ሁላችሁም ከሲያል ወድቃችሁ ማየት! ያንን ነው የምፈልገው:: ሰላም ስጡኝ:: ማንም እንዳይረብሸኝ ስል መላዋን ዓለም ላንድ ሳንቲም ብሸጣት ቅር አይለኝም:: ሻይ መጠጣቴን በመተው የሰውን ዘር ሁሉ ከኩነኔ ማዳን ቢቻለኝ እንኳን ሻይዬን አግኝቼ ፍጡር ገሃነም ሲገባ ማየት እንደምመርጥ ታውቂያለሽ ወይስ አታውቂም?

« ወስላታ፣ ዝቃጭ፣ ራስወዳድ፣ አውደልዳይ፣ ዋጋቢስ መሆኔን አውቃለሁ:: ባለፉት ሦስት ቀናት የመምጣትሽ ሃሣብ ሲያስጨንቀኝ ነበር:: ከሁሉም ይበልጥ የረበሸኝ ታዲያ እንዲያ እንደክቡር ሰው ከፊትሽ ስጀነን ቆይቼ፣ አሁን እንዲህ ድሪቶ ለብሼ በድህነት ከምዋኝበት መጥተሽ ምንነቴን ታያለሽ ብዬ ማሰቤ ነው:: ማፈሬን እወቂልኝ፤ በድህነቴ ከምንም በላይ እንደማፍርበት:: አዎ ግብዝ ነኝ:: በዚች የነተበች ልብሴ ስላየሽኝ ብቻ እንኳን ይቅር እንደማልልሽ አላወቅሽም? እንደአውሬ ቡችላ አፖሎን ላይ ስጮህበት:: ያሸለበ ጎሊና ቀስቃሹ፣ የቀድሞው ታላቅ ሰው፣ እንደመናጢ ውሻ አገልጋዩ ላይ ተንደርድሮ ሲተከልበት፣ አገልጋዩ በንቀት ሲስቅበት! ሆድ የባሳት አሮጊት ይመስል ከፊትሽ ያፈሠስኩት እንባ፤ ያንን እንዴት አድርጌ ይቅር እልሻለሁ? አሁን እንኳን ለምዘከዝክልሽ ገበናዬ ብቻ አልምርሽም:: ለዚህ ሁሉ ተጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያቂዋ አንቺው ነሽ፤ በመምጣትሽ:: እኔ ራሴ የርጉማን ርጉም፣ መሣለቂያ፣ ርካሽ፣ ምድርን ከወረሯት ትላትሎች ሁሉ የከፋሁ ምቀኛ ነኝ:: ሌሎቹ ትሎች ከኔ እምብዛም ባይሻሉም አያፍሩበትም:: ታዲያ ሁልጊዜ ማንም ተባይ እየተነሳ በጥፊ ይለኛል:: እንዲህ ያለሁ ሰው ነኝ:: አሁን የምዘላብደው አንዱም ባይገባሽ ምን ገደደኝ? እዚያ ቤት ተወትፈሽ ወድቀሽ ብትቀሪ ለኔ ምኔ ነው? አሁን እዚህ ሆነሽ ያልኩትን ሁሉ በመስማትሽ ብቻ እምርሬ እንደምጠላሽ አይገባሽም? ሰው ይህን መሣይ ነገር ካፉ የሚወጣው በህይወቱ አንዴ ብቻ ነው፤ አእምሮውን የሚያስት ነገር ሲያገጥመው:: ታዲያ ምንድነው የምትፈልጊው? ከዚህ በኋላ ምን አገኝ ብለሽ ነው ቁጭ ብለሽ የምትጠብቂው? ለምን ታሠቃይኛለሽ? ለምን አትሄጂም? »

ያልጠበቅኩት ነገር ተፈጠረ:: ሁሉም ነገር ይሆናል ብዬ የማስበው ከመፅሐፍ እንዳነበብኩትና ቀድሜ እንዳለምኩት ስለነበር የተከሰተውን ነገር መረዳት ለጊዜው አቅቶኝ ነበር:: ተቀልዶባትና ክብሯ ተረግጦ ሳለች፣ ሊዛ ከገመትኩት በላይ የነገሮችን ምንነት ተገንዝባለች:: ከልቧ የወደደች ሴት ቀድማ ማየት እንደሚቻላት፣ የተከፋሁ መሆኔን አውቃለች::

ፊቷ ላይ ያየሁት ድንጋጤና መከፋት፣ ሃዘን በለበሰ መገረም ተተካ:: ቆይቼ ራሴን መስደብ ስጀምርና ሲተናነቀኝ የቆየው እንባ ገንፍሎ ጉንጮቼን ሲያርሰው፣ የሷም ፊት ይርበተበት ጀመር:: ተነስታ ካጠገቤ ልትመጣ ፈለገች:: እንደዚያ የውስጤን ጉድ ገልጬ እንዳሳይ ያስገደደኝ ስቃይ እንጂ የጠቀለልኩበት መርዝ አልነበረም ያሳሰባት:: ራሷን ከኔ በታች አድርጋ ስለቆጠረች ልትናደድብኝ አልደፈረችም:: ልትቆጣጠረው ባልተቻላት ኃይል ከወንበሩ ተነስታ፣ ሁለንተናዋን ወደኔ ቀስራ ክንዶቿን ዘርግታ ቆመች:: ልቤ ለስለስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲል ተንደርድራ መጥታ አንገቴ ላይ ተጠመጠመችና ማልቀስ ጀመረች:: እኔም በህይወቴ አልቅሼ እንደማላውቀው ተንሰቅስቄ አለቀስኩ::

« በጅ አይሉኝም . . . ጥሩ ሰው ልሆን አልችልም! » አልኩኝ በሲቃ መሃል:: ከሶፋው ላይ በሆዴ ተዘርሬ ፊቴን ቀበርኩና ለረጅም ጊዜ እየተወራጨሁ ተንሰቀሰቅኩ:: ሊዛ እንዳቀፈችኝ ሳትንቀሳቀስ ከጎኔ ተጋድማለች::

ችግሩ ይህ ሁሉ ልቅሶና መወራጨት ሲያልፍ ነበር:: ከዚያም፣ (የምዕፈው ቆሻሻ እውነት ነውና አልደብቀው) ከሶፋው ላይ ተዘርሬ፣ ፊቴን በቆዳ ከተሸፈነው ድልዳል ቀብሬ ሳለሁ፣ በመጀመሪያ ሳልፈቅደው በግዴ፣ እንዲያው እንዲሁ በሩቁ፣ ፊቴን ቀና አድርጌ የሊዛን ዓይኖች የመመልከቱ ሃሳብ አሳፈረኝ:: ምኑ ነበር ያሳፈረኝ? እንጃ፣ ግን አፈርኩበት:: ቀጥሎም፣ አሁን እኔና ሊዛ ቦታ እንደተለዋወጥን፣ እሷ ታዳጊዬ፣ እኔ ደግሞ ያኔ ሳገኛት እንደነበረችው ከትቢያ የወደቅኩ ደካማ ፍጡር:: ይህ ሁሉ ካጠገቧ ፊቴን ከሶፋው ቀብሬ እንደተጋደምኩ በአእምሮዬ ውስጥ አለፈ::

ታዲያ በዚያች ሰዓት እሷን መሆን ተመኝቼ ነበር ይሆን? አላውቅም:: እስካሁን ድረስ የዚህን መልስ አላውቀውም:: የበላይ ሳልሆን፣ በአንዱ ላይ ፈላጭ ቆራጭነቴን ሳላሳይ መኖር እንደማልችል ግን አውቃለሁ::

ቆየም ዘገየም መነሳቴ አይቀርም ነበርና እንደምንም ብዬ ራሴን ቀና አደረግኩ:: ከዚያም፣ በዚህ አሁንም ቢሆን ጥርጥር የለኝም፣ ዓይኖቿን ማየት ስላሳፈረኝ ብቻ እንደገና ልገዛትና ነፍሷን ጠቅልዬ ከእጄ ላስገባ የሚያስመኝ ነገር ከልቤ ውስጥ ሲፍለከለክ ተሰማኝ:: ወዲያው ዓይኖቼ በዕኩይ ስሜት ፈኩና እጆቿን ጥብቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

አድርጌ ያዝኳቸው:: እንደዚያ እየጠላኋት ሳለሁ ከጉያዋ ተወተፍኩ:: መጀመሪያ ከፊቷ ላይ ግራ መጋባትና ፍርሃት ለቅፅበት ታዩኝ:: ወዲያው ግን በሙሉ ልቧ ጥምጥም ብላ አቀፈችኝ::

- 16 -

ከሩብ ሰዓት በኋላ ዕብደት የነካካው ትዕግሥት ማጣት ሠፈረብኝና ከክፍሌ ውስጥ እንቆራጠጥ ጀመር:: እየቆየሁ ከአልጋዬ ዙሪያ ወዳለው መጋረጃ እየሄድኩ መገናኛው ላይ ባለው ስንጥቅ አጮልቅባታለሁ:: ከወለሉ ላይ ተቀምጣ በራሷ አልጋውን ተደግፋለች:: እንዳለቀሰች ያስታውቅባታል:: ሆኖም ግን ቆርጣ አልሄደችም፤ የረበሸኝም ይኸው ግትርነቷ ነበር:: አሁን ሁሉን የተረዳች ይመስለኛል:: የርኩስነቴን መጠን አሳይቻታለሁ:: እና . . . ሌላ ምን እላለሁ? ድንገት ገንፍሎ ከእቅፏ የከተተኝ ሥሜት እሷን ይብሱን ለማጉደፍ የመዘዝኩት መሣሪያ እንደገና፣ የቀድሞው ከዚህ መጣ ልለው ያዳገተኝ ጥላቻዬ አሁን ቅናት ደልቦበት ጭራሹን እንደከፋ ሳይገባት አልቀረም:: ይህን ሁሉ በግልፅ አውቃዋለች ማለት ቢያስቸግርም፣ የተለከፍኩ ልክስክስ ሰው መሆኔንና ላፈቅራት እንደማልችል ተገልጦላታል::

ይህ መናጢነቴ ለማመን የሚያዳግት ነው ይሉኝ ይሆናል፣ የሊዛን ፍቅር መመለስ እንኳን ባይሆን ምንነቱን መረዳት አለመቻል የማይሆን ነገር ይመስልዎታል:: ለምን? በመጀመሪያ፣ በዚያ ወቅት ለኔ ማፍቀር ማለት አንቀጥቅጦ መግዛትና፣ የላቀ መሥሎ በሚታዬኝ የሥነምግባር ደረጃዬ መመፃደቅ ማለት ነበር:: ከዚያ የተለየ ፍቅር ይኖራል ብዬ ስለማልገምት፣ አሁንም ቢሆን አንዳንዴ ፍቅርን

t.me/OLDBOOKSPDF

የማየው ተፈቃሪው በነፍሱ ላይ እንዲታዘዝበት የሚያቀርበው የፈቃዱ ገፀ-በረከት አድርጌ ነው:: በስርቻዬ ሆኜ እንኳን በምዋኝቅበት ቅዠት፣ ፍቅር ትግል እንጂ ሌላ ነገር መስሎኝ አያውቅም:: አፈቀርኩ ባልኩባቸው አጋጣሚዎች በጥላቻ የጀመርኩት ነገር የሞራል ምርኮ ያስከትልና ኋላ ከእጄ የገባችውን ነፍስ ምን እንደማደርጋት ቅጡ ይጠፋብኛል:: አዎ፣ ከህይወት የተፋታሁ ብኩን ነበርኩ:: ሊዛን " በለፈለፍኩልሽ ቃላት ተሞኝተሽ መጣሽ " ስላት የነበርኩበት የነውረኝነት ማጥ ከርፋቱ አልተሠማኝም ነበር:: የመጣችው ወሬዬን ፈልጋ ሳይሆን ልትወደኝ እንደነበር አልገባኝም፤ ፍቅር የሴት ትንሣኤዋ፣ ከጥፋት የሚያወጣት መድኅኗ ነውና::

ወዲያ ወዲህ ስንቆራጠጥና በመጋረጃው እያጮለቅኩ ስመለከታት እንኳን አምርሬ አልጠላኋትም ነበር፤ እንዲያው ካጠገቤ መሆኗ ረበሸኝ እንጂ:: ከፊቴ ብትጠፋ ነበር የፈለግኩት:: 'ሰላም' ናፈቀኝ:: ብቻዬን ከስርቻዬ መንገስ ተመኘሁ:: ያልለመድኩት የዕውን ሕይወትና ግሳንግሱ ነፍሴ ላይ እንደቋጥኝ ተከምሮ አስጨነቀኝ::

ጥቂት ደቂቃዎች አልፈውም ሊዛ ከነበረችበት አልተንቀሳቀሰችም፤ ያለችበትን የማታውቅ ይመስል:: ቆት እንዳለች ላስታውሳት ብዬ ግድግዳውን አንኳኳሁ፤ ያን ለማድረግ ከፋቱ አልቸገረኝም:: ከሠመመኗ በርግጋ ተነሳችና፣ ከኔ አምልጣ ራሷን ለማዳን እንደተቻኮለች ሁሉ ያንገት ልብሷንና ካፖርቷን አፈፍ አደረገች:: ወዲያው ከመጋረጃው ወጥታ አትኩራ ስትመለከተኝ፣ በፈገግታ ሥም አገጠጥኩባትና ዓይኖቼን ሰበርኩ::

t.me/OLDBOOKSPDF

« ደህና ሁን » አለችኝ ወደ በሩ እያመራች። በድንገት ተንደርድሬ እጇን ያዝኩና ፈልቅቄ የሆነ ነገር አስይዥት ወደነበርኩበት ተመልሼ፣ መጨረሻውን ላለማየት ፊቴን አዙሬ ቆምኩ። ልክ አሁን ልዋሽ ነበር:- የማደርገውን ሳላውቅ፣ ሳላስብበት፣ ግራ ተጋብቼ ነው ይህን ያደረግኩት ብዬ ልቅጠፈጠፍ። መዋሸት ስለማልፈልግ የድርጊቴ ምክንያት አረመኔነቴ መሆኑን አምናለሁ። እሷ ከመጋረጃው ኋላ ተቀምጣ፣ እኔ ወዲያ ወዲህ ስንጎራደድ ነበር ሃሣቡ የመጣልኝ። ይህን ግን ሳልጠራጠር እነግርዎታለሁ:- ምንም እንኳን ይህን ቆሻሻ ነገር ያደረግኩት ሲታወቀኝ ቢሆንም፣ የተጠነሰሰው ከልቤ ሳይሆን ከደደብ ጭንቅላቴ ውስጥ ነው። የዚህ ጭካኔዬ የአእምሮ ውላጅነቱ፣ ታስቦ የተደረገ ነገር መሆኑ፣ ከመፅሐፍ የተዋስኩት መምሠሉ ሲገለጥልኝ፣ ለራሴ ዘገነነኝና ሳታመልጠኝ ልደርስባት ሮጥኩ። በሩን ከፍቼ ቁልቁል ደረጃውን ስመለከት አጣኋት። « ሊዛ! ሊዛ !» ስል ተጣራሁ ድምፄን ዝቅ አድርጌ። መልስ አልነበረም። የውጪው በር ተከፍቶ ሲዘጋ ሰማሁ። በትካዜ ወደክፍሌ ተመለስኩ።

ተቀምጣበት ከነበረው ወንበር አጠገብ ቆሜ ጥቂት እንደቆየሁ፣ አንዳች ነገር ሰውነቴን ነዘረኝ። ቅድም ከእጇ ውስጥ ያስቀመጥኩት አምስት ብር ከፊቴ ከወለሉ ላይ ወድቋል። እሱ ራሱ ነው፤ ሌላ የአምሥት ብር ኖት ከቤቴ አልነበረም። አስይዥት ዞሬ እንደቆምኩ ጥላው ሂዳለች።

ሰው ከመናቁ ብዛት፣ በእውን ለሚያጋጥሙኝ ሰዎች አክብሮት ከማጣቴ የተነሳ፣ ሊዛ ይህን ታደርጋለች ብዬ አልጠበቅኩም ነበር። እየተጣደፍኩ ያገኘሁትን አጥልቄ ልደርስባት ወጥቼ ሄድኩ። ከቤቴ ብዙም የራቀች አይመስለኝም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ውጪው ፀጥ ብሏል:: በረዶው እየተዥጎደጎደ ከሠማይ ወርዶ አውራጎዳናውን አልብሶታል:: በመንገድ አንድም ሰው አልነበረም:: ኮሽታ የሌለበት ረጭ ያለ ፀጥታ:: የመንገድ መብራቶች በበረዶ ተወርሰው ብልጭ እልም ይላሉ:: አንድ መቶ ሜትር ያህል ሮጬ ፈለግኳት፤ አላገኘኋትም:: የት ደረሰች? ለምንስ ነው ላገኛት የፈለግኩት?

ለምን? ከፊቷ ተንበርክኬ በፀፀት እያለቀስኩ፣ እግሮቿን እየሳምኩ ይቅር እንድትለኝ ልማፀናት! ይህን ነበር የተመኘሁት፤ ልቤ በቁጭት አለንጋ እየተገረፈ:: እስከዕለተሞቴ ድረስ ያችን ሰዓት የማስታውሳት እንባ እየተናነቀኝ እንደሆነ አውቃለሁ:: « ግን ለምን? » ስል አሰብኩ:: የተመኘሁት ቢሳካልኝ፣ ዛሬ እግሯን በመሳሜ ነገ መልሼ አልጠላትም? እኔ በእርግጥ እሷን ደስ ማሰኘት የሚቻለኝ ሰው ነኝን? የእውን ምንነቴን ለመቶኛ ጊዜ አይቼው የለም? አሰቃይቼ ልገድላት ካልሆነ በቀር ሌላ ምን ልፈይድላት? በረዶ እየወረደብኝ ቆሜ ይህንን አሰብኩ:: « ይህን የለጠፍኩባትን የውርደት ጭቃ ይዛ፣ ዳግም ላታየኝ ብትሄድ አይሻልም? » አልኩኝ ለራሴ፣ ኋላ ከቤቴ እንደተመለስኩ::« ውርደት! ውርደት አይደል በደልን አጥቦ የሚያፀዳ? ከሱም አይደል የሚቆረቁርና የሚቀጣ ኅሊና የሚወለደው? ባትሄድ ኖሮ ነገ ግት ጨምሬ ነፍሷን አጉድፌ አማርራት አልነበረም? ደራርቤ የጫንኩባት ግፍ መቼም ከውስጧ አይጠፉም፤ የተከልኩባት መርዝ ግን ይፈውሳታል፣ ከፍ ያደርጋታል . . . በጥላቻ . . . ህም . . . ምናልባትም በይቅርታ:: ሆኖም ግን፣ ይህ ሁሉ ጣጣዋን ያቀልላት ይሆን?

አሁን ደግሞ ይህንን ጥያቄ አሰላስላለሁ:- የትኛው ይሻላል - ተራ ደስታ ወይስ ክቡር መከራ? የትኛው ይመረጣል?

t.me/OLDBOOKSPDF

ያኔ ማታ፣ ልቤ በሃዘን ቆስሎ በተቀመጥኩበት፣ ይህን የመሣሠለ ሃሳብ ነበር ከአእምሮዬ ውስጥ የሚንጎዳጎደው:: እንደዚያ ምሽት በከፋ ፀፀትና ስቃይ ተቸንክሬ የተቀመጥኩበት ሌላ ጊዜ ትዝ አይለኝም:: ለመሆኑ ልድረስባት ብዬ ከቤቴ ስወጣ፣ ከግማሽ መንገድ እንደምመለስ ጥርጣሬ ነበረኝ?

ሊዛን ከዚያች ቀን በኋላ አላገኘኋትም፤ ወሬዋንም ሰምቼ አላውቅም:: በደል፣ ውርደትና ጥላቻ ስለሚፈጥሩት ጠቀሜታ የወጠንኳትን ሃሣብ በደስታ እያመላለስኩ ሳላምጣት ሰነበትኩ:: ዛሬ እንኳን፣ ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ ይህን ማሰቡ ሰላም ይነሳኛል:: አሁንም ብዙ ትውስታዎች ይረብሹኛል:: ግን ትረካዬን በዚሁ ብደመድመውስ? ባልጀምረው ሳይሻለኝ አይቀርም ነበር:: ሆኖም ግን ይህን ሁሉ ስፅፍ እፍረት ተጠናውቶኝ ነበር:: ስለዚህም ይህ የመታረሚያ ቅጣት እንጂ ስነፅሁፍ አይደለም:: እንዴት ቢሉኝ:- በጠማማ ተፈጥሮዬ ከሰው ተለይቼና ሕይወትን በውል ከሚኖሯት ጋር ሳልቀላቀል፣ በግብዝነት፣ በክፋት፣ ከዋሻዬ ተወትፌ እንዴት ሕይወቴን እንዳባከንኩ መመዝገብ ደስ የሚያሰኝ ነገር አይደለም:: ታሪክ ያለተዋናይ አይፃፍም፤ ይህ ትረካ የታነፀው ግን በይሁንታ በተለቀሙ የኢ-ተዋናይ ድርጊቶች ጥርቅም ነው:: ከዚያም በላይ፣ ሁላችንም ከህይወት የተፋታን፣ አነሰም በዛም ስንኩሎች በመሆናችን ምክንያት፣ ከዚህ መፅሐፍ ውስጥ ያሉት ነገሮች ያስቀይሙናል::

በእውነቱ ለነገሮች ባይተዋር ከመሆናችን የተነሳ በእርግጥ የሚኖር ሕያው ሕይወትን እየተጠየፍን ስለሱ ባያነሱልን እንመርጣለን:: የእውን ሕይወትን ከባርነት ስለምንቆጥረው ነገሩ ሁሉ እንደልቦለድ መፅሐፍ ትረካ ቢሆን በልባችን እንፈቅዳለን:: ታዲያ ምን ያቁነጠንጠናል? ምን ፈልገን ነው ሽርጉድ የምንለው?

t.me/OLDBOOKSPDF

የምንፈልገውን ራሳችን አናውቀውም:: ከንቱ መሻታችን ቢሳካልን ይከፋል እንጂ አይበጅም:: እስቲ የበለጠ ነፃነት ይሰጠን፣ ከእጃችን ላይ ሠንሠለቱ ይውለቅ፣ የማድረግ ችሎታችን ገደብ ይደምሠስ፣ የሕግጋት ማዕቀብ ይነሱልን:: ያኔ፣ ምን አለ ይበሉ፣ እንደገና ቀንበሩ ከጫንቃችን ላይ እንዲቀመጥ ራሳችን እንለምናለን::

ይህን በማለቴ ይናደዱብኝ፣ ይሰድቡኝና ምድሩን በእግርዎ ይወግሩ ይሆናል:: « ስለራስህና ስለስርቻ ጣጣህ ራስህን ወክለህ ተናገር እንጂ እኛን አትጨምር » ይሉኛል:: « እኛ » የምለው ማንነቴን ከሰው ቀላቅዬ ለመደበቅ አይደለም:: በበኩሌ ያደረግኩት ነገር ቢኖር፣ እርስዎ ከግማሽ መንገድ ድረስ ለመግፋት ያልደፈሩትን እኔ በህይወቴ እስከመጨረሻው ማዝለቅ ነው:: የሚገርመው ታዲያ ወኔቢስነትዎን በቅንነት ካባ ሸፋፍነው ራስዎን ከመደለል ሰላም ማግኘት መቻልዎ ነው:: ሆኖም ግን፣ ከእርስዎ ይልቅ እኔ ህያው ሳልሆን አልቀርም:: ልብ ብለው ያስተውሉ:: ሕይወትን አጣጥመው በወጉ የሚኖሩት ሰዎች ዛሬ የት እንዳሉ እንኳን አናውቅም:: አኗኗራችንን የምንዋስበት መፅሐፍ ሳይሠጡን እንዲሁ በሜዳ ቢተውን፣ ወዲያው የነገሩ ሁሉ ራስና ጅራት ይጠፋብናል፤ ከማን እንደምናብር፣ በምን እንደምናምን ምን ጠልተን ምን እንደምንወድ፣ ምኑን አክብረን ምኑን እንደምንንቅ አናውቅም:: ሰብዓዊነታችን ከሸክም እንቆጥረዋለን:: ጨንግፎናል:: ከሰው መወለድ ውቶዋችን ደስ አያሰኘን መጥቷል:: ጥቂት ቆይተን ደግሞ ከፅንሰሃሳብ የምንወለድበትን መንገድ ሳንቀይስ አን[illegible]ም:: ይሁንና ይብቃን:: የስርቻ መጣጥፌ በዚህ ያከትማ[illegible]

///

t.me/OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF